«ከቤት ውጣ» መባል ያስከተለው ፍፃሜ



ገጽ 10

እምቢታ የማያውቀው ባህላችንና እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት

ገጽ 11

አዲስ ዘመን

82ኛ ዓመት ቁጥር 014 መስከረም 14 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# <<ወረራና መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት>>

## - የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የጥናት ውጤት እንደማሳያ

**ሞገስ ተስፋ**

መስፍን፣ ትምክህተኛ፣ ነፍጠኛ፣ የሚሉ ስሞችን ለአማራ ሕዝብ በመስጠት ማዋረድ፣ መጥላት፣ ግድያና ማሳደድ፣ እስራትና ማሰቃየት፣ መሰወር፣ አስገድዶ መድፈርና ማስረገዝ፣ ሕወሓት ከቅድመ ስልጣኑ እስከ ድህረ ስልጣኑ ከዚያም በሽፍትና ዘመኑ በአማራ ህዝብ ላይ የፈጸመው ግፍ ነው፡፡

<<ወረራና መዋቅራዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# <<መንግስት የትህነግ ወንጀለኛ መሪዎችን ለፍርድ ማቅረብ አለበት>>

## - ዶክተር ትሁት አስፋው የኢትዮ-ካናዳውያን ኔትወርክ ለቅስቀሳና ለማህበራዊ ድጋፍ ፕሬዚዳንት

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- መንግስት የትህነግ ወንጀለኛ መሪዎች ለፍርድ ማቅረብ እንደሚገባው የኢትዮ-ካናዳውያን ኔትወርክ ለቅስቀሳና ለማህበራዊ ድጋፍ ፕሬዚዳንት ዶክተር ትሁት አስፋው ገለጹ፡፡

<<መንግስት ... ወደ ገጽ4 ዞሯል

# የትግራይ እናቶች ልጆቻቸውን ከአሸባሪው ትህነግ የሚደብቁበት አጥተው እየተነጠቁ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የትግራይ እናቶች ህፃናት ልጆቻቸውን ከአሸባሪው ትህነግ አደን የሚደብቁበት አጥተው እየተነጠቁ መሆኑን የሽብር ቡድኑ ጋዜጠኛ ፍጹም ጿጋዬ ገለጸ፡፡ አሸባሪው ሕወሓት ራሱ ጦርነቱን እንደጀመረው አጋልጧል፡፡

እጁን ለመከላከያ ሰራዊት የሰጠው የሽብር ቡድኑ ጋዜጠኛ ፍጹም ጿጋዬ እንዳለው፤ አሸባሪው ትህነግ የትግራይን እናቶች እያስለቀሰ አረጋውያንን ያለ ጧሪና ቀባሪ እያስቀራቸው ነው፡፡

ጦርነትና ግጭትን የህልውናው ማራዘሚያ ያደረገው የሽብር ቡድኑ፤ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሶስተኛ ዙር ወረራ በመጀመር የሰላም ጸር መሆኑን አስመስክሯል ብሏል፡፡

የትግራይ ህዝብ ጦርነት ይብቃ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ይፈቱ እያለ ቢወተውትም በቆቦ በኩል ዳግም ጦርነት በመክፈት የትግራይ እናቶችን እረፍት ነስቷቸዋል ብሏል፡፡

የትግራይ እናቶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ጋዜጠኛ ፍጹም ጿጋዬ










ገጽ 2

የአደባባይ በዓላትን ለጸጥታ ስጋት ከሚጥሉ ሙከራዎች በንቃት መከታተል እንደሚገባ ተጠየቀ



# የአደባባይ በዓላትን ለጸጥታ ስጋት ከሚጥሉ ሙከራዎች በንቃት መከታተል እንደሚገባ ተጠየቀ


አቶ ጃንጥራር አባይ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላትን ለጸጥታ ስጋት ከሚጥሉ ሙከራዎች በንቃት መከታተል እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ጃንጥራር አባይ አሳሰቡ፡፡ አስተዳደሩ የመስቀል ደመራ በአል ፍጹም ሰላማዊ ሆኖ እንዲከበር ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር መክሯል፡፡

በምክክር መድረኩ ምክትል ከንቲባው አቶ ጃንጥራር፤ የመስቀል በአል ከሃይማኖታዊ ስርአት ባሻገር የሀገር ሀብት በመሆኑ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበር የንግዱ ማህበረሰብ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ሀገር ለማተራመስ አቅደው ያልተሳካላቸው ኃይሎች በህዝብ አደባባይ በዓላት ለማካካስ የሚሯሯጡ አካላትን መከላከል እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

የአገሪቷን ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ የንግዱ ማህበረሰብ ደጀን ሆኖ ትልቅ ኃላፊነት እየተወጣ ይገኛል ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ ሀገር የማተራመስ እቅዳቸው ያልተሳካላቸው አካላት አደባባዮችን ለግጭት ምክንያት እንዳይጠቀሙባቸው እንደሌላኛው የትግል ግንባር በመቁጠር የንግዱ ማህበረሰብ ሚናቸውን መወጣት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡ መላው ህዝብ ሁሉንም በአላት በጋራ በድምቀት ማክበር እንዳለበትም ተናግረዋል፡፡

በበዓሉ ወቅት ጸብ አጫሪነትን ፈጥረው፣ ልዩ መልዕክት ሰጥተው፣ በገንዘብ አታልለው በተለያየ መንገድ ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት የሚደረጉ ሙከራዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ምክትል ከንቲባው በውይይቱ አንስተዋል፡፡ እስካሁን ባለው ክትትል እኩይ ድርጊት የሚፈጽሙት ላይ እርምጃ እየተወሰደ እንዳለ ጠቅሰዋል፡፡ ህጋዊ በሆነ መንገድ በህገ ወጥ መንገድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ እንዳለም አመላክተዋል፡፡ በህዝብ ውስጥ የሚታዩና የጸጥታ ሀይሉና የመንግስት መዋቅሩ ያላያቸውን ህዝብ እንዲያጋልጣቸውም አሳስበዋል፡፡

በአል በመጣ ወቅት በግብይት ላይ በሚፈጠሩ የዋጋ ንረት የህዝብ ቅሬታዎች እንደሚነሱ የጠቆሙት ምክትል ከንቲባው፤ መጪው የመስቀል በአልን ምክንያት በማድረግ የዋጋ ንረት እንዳይፈጠርና በአሉን በሰላም ለማክበር የንግዱ ማህበረሰብ ሚናውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ በበኩላቸው፤ የአሸባሪው ሕወሓትና ኦነግ ሸኔ ተላላኪዎች በመዲናዋ ሽብር ለመፍጠር የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ እንዳሉና አስተዳደሩ ክትትል በማድረግ እርምጃ እየወሰደባቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የሽብር ቡድኖቹ ተላላኪዎች በተለይም ህትመት ቤቶችን በመጠቀም ህዝብን ከህዝብ ሊያጋጩ የሚችሉ መልእክቶችን ለማስተላለፍ እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ እንደለ ጠቅሰዋል፡፡ የንግዱ ማህበረሰብ ላይ ጫና ለመፍጠርና በአሉ ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዳይከበር ለማድረግ የሚንቀሳቀሱትን የሽብር ቡድኖቹን ተልዕኮ ከማክሸፍ ጀምሮ በአሉን በአብሮነት እሴት ማክበር እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በአሉ በሰላም እንዲከበር ከውጭ የሚመጡትን እንግዶች በሚገባ በመቀበል፤ ጸጉረ ልውጦችን ለጸጥታ ኃይሎች በማጋለጥ፣ የህትመት አይነቶች ላይ ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭ መልዕክት እንዳይሰራጭ ተገቢ ጥንቃቄ በማድረግ፤ በአሉን ተከትሎ አግባብ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ እንዳይደረግ ከጸጥታ ኃይሉ ጋር በመስራት ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡ የመድረኩ ተሳታፊዎች ተናግረዋል፡፡ ጸጥታውን ለማስከበር እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን መንግስት በትኩረት እንደሚመለከተውም ገልጿል፡፡

# ኮርፖሬሽኑ ከቻይናው ላይት ሃውስ ጋርመንት ማኑፋክቸሪንግ ፒኤልሲ ጋር የሼድ ኪራይ ውል ስምምነት ተፈራረመ

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርትን ለማምረት የሚያስችል ሼድ የኪራይ ስምምነት ውል ከቻይናው ላይት ሃውስ ጋርመንት ማኑፋክቸሪንግ ፒኤልሲ ጋር ተፈራረመ፡፡

የሼድ ኪራይ ውል ስምምነት ፊርማውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሺፈራው ሰለሞን እና የቻይናው ላይት ሃውስ ጋርመንት ማኑፋክቸሪንግ ፒኤልሲ ጀኔራል ማናጀር ቺን ዊንቢንግ ተፈራርመዋል፡፡

በፊርማ መርሃ-ግብሩ ላይ የኮርፖሬሽኑ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሺፈራው ሰለሞን እንደተናገሩት፤ ከቻይናው ላይት ሃውስ ጋርመንት ማኑፋክቸሪንግ ፒኤልሲ ጋር የተከናወነው የሼድ ኪራይ ስምምነት በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚተገበር ነው፡፡

ኩባንያው ስራውን ለማከናወን በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በ5,500 ካሬሜትር መሬት ያገኛል ያሉት አቶ ሺፈራው፤ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርትን እንደሚያመርትም ተናግረዋል፡፡ በዚህም ኩባንያው ከ216 ሚሊዮን ብር በላይ መዋዕለ ንዋይ ፈሰስ ያደርጋል ብለዋል፡፡ ኩባንያው 945 ሚሊዮን ብር ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ እንደሚያስገኝና ወደ ስራ ሲገባም በውስጡ ከ600 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩልም ተኪ ምርትን በሀገር ውስጥ በማምረት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲተገበር ኮርፖሬሽኑ የበኩሉን ሚና በመወጣት ላይ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

አሁን ላይ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከ125 በላይ የውጭና የሀገር ወስጥ አምራች ኩባንያዎች ገብተው በመስራት ላይ እንደሚገኙ የተናገሩት አቶ ሺፈራው፤ ከ81 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎችም የስራ እድል መፍጠሩንና ከ931 ሚሊዮን ብር በላይ ትርፍ ማስመዝገብ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

መንግስት አቅም ያላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲሰሩ ለማድረግ በተሰራው ስራም ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ ከስድስት በላይ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለመስራት የሚያስችላቸውን የሼድና የለማ መሬት የሊዝ ኪራይ ተፈራርመው ወደ ስራ ገብተዋል ብለዋል፡፡

የላይት ሃውስ ጋርመንት ማኑፋክቸሪንግ ፒኤልሲ ጀኔራል ማናጀር ቺን ዊንቢንግ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኩባንያው ተኪ ምርትን በማምረት የውጭ ምንዛሪ ወጪን ያስቀራል፡፡ አልባሳትና ጨርቃ ጨርቅን በማምረትም ለሀገር ውስጥ ገበያም ያቀርባል፡፡

በተጨማሪም ኩባንያው በኢትዮጵያ ከሚያመርተው ምርት 30 በመቶ የሚሆነውን ወደ ሲንጋፖር፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ አንጎላና ሌሎች አጎራባች ሀገራት በመላክ የሀገሪቱን የውጪ ንግድ ያሳድጋል ሲሉ ማናጀር ቺን ዊንቢንግ ገልጸዋል፡፡ ይህም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ያስገኛል ብለዋል፡፡

ማናጀር ቺን ዊንቢንግ አክለውም ስምምነቱ አልባሳትና ጨርቃ ጨርቅን ከማምረት በላይ ለ52 ዓመታት የቆየውን የቻይናና የኢትዮጵያን ጠንካራ ግንኙነት ይበልጥ ያጠናክረዋል፡፡


ስምምነቱ አሁን ኢትዮጵያ ባለችበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ የሁለቱን ሀገራት በሁሉም ጉዳዮች አብሮ ለመስራትና ለማደግ ያላቸውን ፍላጎት ያሳያል ሲሉም ማናጀር ቺን ዊንቢንግ ተናግረዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን በአሁኑ ጊዜ በመላ ሀገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች ያሉት ሲሆን 177 ሼዶችን አስገንብቶና ከ540 ሄክታር በላይ የለማ መሬትን በማዘጋጀት የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች እንዲገቡ በማድረግ የስራ እድሎችን እየፈጠረ እንደሚገኝ በስምምነቱ ወቅት ተጠቅሷል፡፡

# ከቱሪዝም የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ የቱሪስት መዳረሻዎችን ማስፋትና ማስተዋወቅ ላይ በትኩረት ይሰራል

## -የዓለም የቱሪዝም ቀን በአሶሳ ከተማ ተከብሯል

**በኃይሉ አበራ**



አሶሳ፡- ከቱሪዝም ዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም በዘላቂነት ለማሳደግ ልማዳዊ አሰራሮችን ማዘመን፤ የቱሪስት መዳረሻዎችን ማስፋትና በነባር መዳረሻዎች ላይ እሴት መጨመር ላይ በትኩረት እንደሚሰራ የቱሪዝም ሚኒስቴር ገለጸ፡፡የዓለም የቱሪዝም ቀን በአገር አቀፍ ደረጃ ለ35ኛ ጊዜ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ ተከብሯል።

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ የቱሪዝም ቀን በአሶሳ ከተማ ትናንት ሲከበር እንዳሉት፤ ቱሪዝም ከገፅታ ግንባታ ባሻገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳው ከፍተኛ ነው።ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም በዘላቂነት ለማሳደግ ልማዳዊ አሰራሮችን ማዘመን፤ የቱሪስት መዳረሻዎችን ማስፋትና ነባር መዳረሻዎች ላይ እሴት መጨመር ላይ በትኩረት መስራት ይገባል፡፡

የቱሪዝም ዕድገት መልካም የአገር ገፅታ ግንባታ ከመፍጠር ባሻገር ለኢኮኖሚያዊ፤ህዝብ ለህዝብ ትስስር እና የባሕል ልውውጥን የሚያሳድግ መሆኑን ገልጸው፤በሀገራችን የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ ባለፉት 50 ዓመታት እየተሰራ ቢሆንም የሚፈለገውን ያህል ውጤት አልተገኘም ብለዋል።

ዘርፉ በኮቪድ እና በጦርነት ከደረሰበት ጉዳት እንዲያገግም የሚያስችል ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ንቅናቄ እንደሚጀመርም ጠቁመው፤ ንቅናቄው የሀገር ውስጥ ጎብኚ ቁጥርን እና ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ በመጨመር ወንድማማችነትን ለማጎልበት ያለመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አሻድሊ ሀሰን በበኩላቸው፤ ከኢትዮጵያዊነት ልዩ መገለጫዎቻችን አንዱ በቱሪዝም ልማት ዘርፍ ያለን ልዩ እና ዕምቅ ሀብት መሆኑን ገልፀዋል። መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ቅርሶቻችን፣ የተፈጥሮ መስህቦቻችን ባህሎቻችን፣ ወግ እና ልማዶቻችን የሚያስደንቁ ናቸውም ብለዋል።

በክልሉ ጉባ ወረዳ እየተገነባ የሚገኘው ታላቁ የህዳሴ ግድብ ጨምሮ በአገራችን እየለሙ የሚገኙ እንደ ወንጪ፣ ጎርጎራ እና ኮይሻ አይነት ፕሮጀክቶች በመጪው የሀገራችን የቱሪዝም ፍሰት አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ መዳረሻዎች እንደሚሆኑና ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም እንደሚያሳድጉ አመልክተዋል።

እንደ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም የታላቁ ህዳሴ ግድብን ፤ የሼህ ሆጀሌ አልሀሰን የችሎት አዳራሽና የመቃብር ስፍራ፣ የደጃዝማች መሀመድ ባንጃው ቤተመንግስት፣ የሸንጋ ፏፏቴ፣ የክልሉ ብሄረሰቦች ባህላዊ እሴቶች እና መሰል የቱሪስት መስህቦች በአግባቡ ማልማትና ማስተዋወቅ ከተቻለም በቱሪዝም ልማት ዘርፍ ብዙ ማትረፍ እንደሚቻል የሚያረጋግጡ መሆናቸውን አስገንዝበዋል።


ኢትዮጵያዊነት በተለያዩ ቀለማት ህብር እንደተሸመነ የጥበብ ሥራ ረቂቅ ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የውበታችንም ሆነ የጥንካሬያችን ምስጢር ከዚህ ረቂቅ ጥበብ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ የቱሪዝም ሀብቶች የክልሉ ከፍተኛ በረከቶች መሆናቸውን አመልክተው፤ ጎብኚዎች አእምሯቸውን የሚያድሱበት አልሚ ባለሀብቶች ትንሽ አውጥተው ብዙ የሚያተርፉበት ክልል በመሆኑ ባለሀብቶች በፈለጉት የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲሰማሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የዓለም የቱሪዝም ቀን “አዲስ እሳቤ ለቱሪዝም” በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ43ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ35 ጊዜ በቢኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ ተከብሯል፡፡ቀኑን ምክንያት በማድረግ ለዕይታ ክፍት በሆነው ዐውደ ርዕይ በክልሉ የሚገኙ የተፈጥሮ፣ ታሪካዊ፣ ሰው ሠራሽና የተለያዩ መገለጫ ሀብቶች ለዕይታ ቀርበው የበዓሉ ታዳሚዎች ጎብኝተዋል፡፡

ዜና

# የመስቀል ደመራ በዓል በሠላም እንዲከበር ምዕመኑ ከፀጥታ አካላት ጋር ተባብሮ መስራት እንዳለበት ተጠየቀ




የባህርዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ስራ አስኪያጅ እና የባህርዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ የደመራ በዓል ስናከብር ሠላምን የምናውጅበትና የተጣላ የሚታረቅበት በመሆኑ ከህፃናት እስከ አዋቂው ከክፋት በመራቅ በዓሉን የሠላምና የፍቅር መሣሪያ አድርገን ማክበር አለብን ብለዋል።

በተለይም በበዓሉ አከባበር ወቅት የበዓሉን ድባብ የሚያበላሽ ምንም አይነት የፀጥታ ችግር እንዳያጋጥም ምዕመኑ ለፀጥታ አካላት በመታዘዝ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ተባብሮ መስራት እንደሚጠበቅበት ብፁዕ አቡነ አብርሃም አሳስበዋል።

የመስቀል ደመራ በዓል ሲከበር ሃይማኖታዊ ስርዓቱን የማይገልጹ ልዩ ልዩ መልእክቶችን ማስተላለፍ ተገቢ እንዳልሆነ ጠቁመው፤ መንፈሳዊነት የተላበሱና አብሮነትን የሚሰብኩ ሊሆኑ እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በዓሉ ያለ ምንም የፀጥታ ችግር እንዲጠናቀቅ ቤተክርስቲያን ከመንግስት የፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት የተለያዩ ስራዎችን እየሠራች መሆኑን ያስታወሱት ብፁዕ አቡነ አብርሃም፤ በበዓሉ ላይ የሚታደሙ የተለያዩ ሀገራት እንግዶች እና ቱሪስቶች በሚኖራቸው ቆይታ እንደ ከዚህ ቀደሙ የኢትዮጵያን መልካም ገፅታ በሚያጎላ መልኩ እንዲሆን ምዕመናን በፍፁም ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በዓሉን ሊያከብሩ ይገባል ብለዋል።

ለመላው የእምነቱ ተከታዮች በዓሉ የሰላምና የፍቅር እንዲሆን ተመኝተዋል።




# ባንኮች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለመቀየር የገጠሩን ማህበረሰብ ታሳቢ ሊያደርጉ እንደሚገባ ተመላከተ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ባንኮች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለመቀየር የገጠሩን ማህበረሰብ ታሳቢ ሊያደርጉ እንደሚገባ ተመላከተ፡፡ ከብድርና ቁጠባ በመነሳት ወደ ባንክነት ያደገው ስንቄ ባንክ የገበሬውን ሕይወትና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለመቀየር የሚሰራ ባንክ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ በስንቄ ባንክ ስራ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ ተገኝተው እንደተናገሩት፤ ባንኮች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለመቀየር የገጠሩን ማህበረሰብ ታሳቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በሀገራችን ያሉት አብዛኞቹ ባንኮች የብድር አገልግሎትን ለከተሜና ለባለሀብቱ የሚያድሉ ናቸው፡፡ የስንቄ ባንክ መሰረቱ እናቶችና ገበሬው በመሆኑ ይህን ችግር በመቅረፍ የገበሬውንና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለመቀየር ወደ ስራ እንደገባም አንስተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ይናገር ገለጻ፤ በሀገራችን ከ80 በመቶ በላይ ማህበረሰብ ገበሬ ነው፡፡ ይህ ቁጥር ያያዘውን የገበሬው ህይወትና ኢኮኖሚ ሳይቀየር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በተዓምር አይቀየርም፡፡ ሁሉም ባንኮች ገጠሬውን ካልቀየሩ ኢኮኖሚውን መቀየር አይችልም፡፡

በኢትዮጵያ ያለውን የባንክ አሰራርና የኢኮኖሚውን እድገት ለማፋጠን በሚያስችል መንገድ የማይክሮ ፋይናንስ አገልግሎትን በማካተት በመላው ኢትዮጵያ የስንቄ ባንክ በአዲስ መለያ የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት መጀመሩንም አብስረዋል።

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ በበኩላቸው፤ የሀገራችን የፋንናንስ ስርዓት ወደ ከተሜውና ባለሀብቱ ያደላ ነው፣ በቀጣይ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለመቀየር ወደ ገጠሩ መሄድና በሰፊው መስራት ይገባል ብለዋል፡፡

ስንቄ ባንክ የገጠሩንና የከተማውን ማህበረሰብ ያማከለ አገልግሎት መስጠት መቻሉ ከሌሎች ባንኮች ልዩ እንደሚያደርገውም ጠቅሰዋል፡፡

ባንኩ የስንቄ ስርዓት መገለጫ ከሆኑት መሰረታዊ ሃሳቦች መካከል አንድነት፣ ፍቅር፣ሰላም፣ እርቅና መተባበረን ያጣመረ ልዩ መለያ ያለው በመሆኑ ለተግባራዊነቱ አመራሮቹና ሰራተኞቹ ይህን ለመወጣት ከባድ ኃላፊነት ይጠበቅባችኋል ብለዋል፡፡

ባንኩ ከማይክሮ ፋይናንስ ወደ ባንክ በማደግ ፈር ቀዳጅ ባንክ መሆኑን የገለጹት የስንቄ ባንክ ፕሬዚዳንት ንዋይ መገርሳ፤ በአሁኑ ወቅት ከአፍሪካ፣ አውሮፓና ዩሮ-ኤዥያ አገራት ባንኮች ጋር ለመስራት የሚያስችለውን ዓለም አቀፋዊ ትስስር በመፍጠር ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ባንኩ ይሰጠው የነበረውን የማይክሮ ፋይናንስ አገልግሎትም ለማስቀጠል ከፍተኛ ዝግጅት ሲያደርግ መቆየቱንም ገልጸዋል።

ባንኩ ለማይክሮ ፋይናንስ አገልግሎት ይጠቀምባቸው የነበሩ 405 ቅርንጫፎች እንዳሉትና ከእነዚህም 250ዎቹ የባንክ አገልግሎት መስጠት የሚያስችላቸውን ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘታቸውንም ፕሬዚዳንቱ ጨምረው ተናግረዋል።

ቀሪዎቹ 155 ቅርንጫፎችም በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ባንክ ቅርንጫፍነት የሚሸጋገሩበት ሥራ በሰፊው እየተሰራ ነው ብለዋል።

የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ቶሎሳ ገደፉ በበኩላቸው፤ ስንቄ ባንክ ዘመኑን የዋጁ የኦምኒ ቻናል ዲጅታል ባንኪንግና ኦራክል ፍሌክስ ኪዩብ ኮር ባንኪንግ ስርዓት የሆኑትን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተጠቅሞ የባንክ አገልግሎትን ለደንበኞቹ ይሰጣል፡፡

በአሁኑ ወቅትም ከ16 ቢሊዮን ብር በላይ ወደ ኢኮኖሚው በብድር መልክ ባንኩ ማሰራጨቱን ገልጸው፤ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥርም ከአንድ ሚሊዮን በላይ ማድረሱን አመላክተዋል። ባንኩ 15 ቢሊየን ብር የተመዘገበና 7.04 ቢሊየን ብር የተከፈለ ካፒታል በመያዝ የኢትዮጵያን የባንክ ኢንዱስትሪ መቀላቀሉን ጠቁመዋል።

ስንቄ ባንክ በይፋዊ የስራ ማስጀመሪያና ብራንድ ማስተዋወቂያ መርሃ-ግብሩ ላይ ኮማንደር አትሌት ደራርቱ ቱሉን የብራንድ አምባሳደር አድርጎ ሾሟል፡፡

# ‹‹በኩታ ገጠም ምርትን እያመረትን ፤ በትብብር የሽብር ቡድኑን እየተፋለምነው እንገኛለን ››

## - የአዲአርቃይ ወረዳ አርሶ አደሮች

**ሙሉቀን ታደገ**



አቶ ብርሃኑ አሬጌ



አቶ ተፈሪ አባሆይ



ወ/ሮ ታፈሱ ፈረደ

አዲአርቃይ፡- በቅንጅት በኩታ ገጠም በማረስ ምርትን ከማሳደግ ጎን ለጎን ከሰራዊቱ ጋር በመተባበር የሽብር ቡድኑን እየተፋለሙት እንደሚገኙ በሰሜን ጎንደር ዞን አዲአርቃይ ወረዳ አርሶ አደሮች ገለጹ፡፡

በሰሜን ጎንደር ዞን አዲአርቃይ ወረዳ የመቃ ዘጠኝ ጭቃ ቀበሌ ሞዴል አርሶ አደር የሆኑት አቶ ተፈሪ አቡሃይ በኩታ ገጠም ያመሩቱትን ምርት በተሞክሮነት ለሌሎች ቀበሌ አርሶ አደሮች ባስጎበኙበት ወቅት እንደተናገሩት፤ የሽብር ቡድኑ ትህነግ በአማራ እና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለሶስተኛ ጊዜ ወረራ ፈጽሟል፡፡ የሽብር ቡድኑ ትህነግ ክረምትን እየጠበቀ ወረራ የሚያደርግበት ዋና ምክንያት አማራው ምርት አምርቶ ራሱን እንዳይችል እና በድህነት ውስጥ እየማቀቀ ከሌሎች እርዳታ በመጠበቅ እንዲኖር ለማድርግ ነው፡፡

ይህንን የሽብር ቡድኑን እኩይ ተልዕኮ የተረዱት የመቃ ዘጠኝ ጭቃ ቀበሌ አርሶ አደሮች በግል ከማምረት ወጥተው በኩታ ገጠም ተባብረው በማረስ ምርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደጋቸውን ይናገራሉ፡፡ አርሶ አደሮች ተባብረው በኩታ ገጠም ማሳቸውን እንዳረሱት ሁሉ ከመከላከያ ሰራዊቱ ጋር በመተባበር የሽብር ቡድኑን እየተፋለሙት እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

ምርታማነትን ማሳደግ አንዱ እና ትልቁ ጠላቶቻችንን የምናሸንፍበት የውጊያ አካል ነው ያሉት አቶ ተፈሪ፤ ይህም የሽብር ቡድኑን ለማጥፋት የሚደረገውን ትግል እንደሚያፋጥነው ተናግረዋል፡፡

በመቃ ዘጠኝ ጭቃ ቀበሌ የሚገኙ አርሶ አደሮች የኩታ ገጠም አስተራረስ ዘዴን በመከተላቸው ከመከላከያ ሰራዊቱ ጎን ሆነው ጠላትን እየተፋለሙ ለሚገኙ ዘማች ሚሊሻዎች እና አርሶ አደሮች ማሳን በቀላሉ ለመንከባከብ እንዳስቻላቸው ተናግረዋል፡፡

የሽብር ቡድኑ ትህነግ ወረራ በመከላከያ ሰራዊቱ በመመከቱ ወደ ውስጥ ዘልቆ መግባት አልቻለም፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሩን እንዳያመርት ለማድረግ ያቀደው እቅዱ መክሸፉን አመላክተዋል፡፡

ይሁን እንጂ አሁንም አርሶ አደሩ ተረጋግቶ እንዳያመርት ለማድረግ እና የመከላከያ ሰራዊቱ ደጀን ህዝብ እንዳይኖረው በማሰብ የሽብር ቡድኑ ትህነግ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰርጎ ገቦችን በማስገባት በህዝቡ ላይ ሽብር ለመፍጠር ተደጋጋሚ ሙከራዎችን አድርጓል፡፡ ነገር ግን ህብረተሰቡ ከጸጥታ ኃይሉ ጋር ተቀናጅቶ በመስራቱ የሽብር ቡድኑ እቅድ ሊሳካ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

በቀበሌዋ የሚገኙት ሌላኛው አርሶአደር አቶ ብርሃኔ አራጌ በበኩላቸው፤ በሽብር ቡድኑ ትህነግ ወረራ ምክንያት በባለፈው ዓመት በመቃ ዘጠኝ ጭቃ ቀበሌ ምንም አይነት ምርት ማምረት አልተቻለም፡፡ የሽብር ቡድኑ ይህን እኩይ ተግባሩን ዘንድሮም መድገም ፈልጎ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ አቶ ብርሃኔ እና ሌሎች የቀበሌዋ ነዋሪዎች በአንድ በኩል ተባብረው በኩታ ገጠም በማረስ በሌላ በኩል መሳሪያቸውን ይዘው ከመከላከያ ሠራዊት ጎን በመሰለፍ የሽብር ቡድኑን እኩይ ዓላማ ማክሸፋቸውን ጠቁመዋል፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሽብር ቡድኑ ይዟቸው በነበሩት ጥቂት በአዲአርቃይ ወረዳ በሚገኙ ቀበሌዎች ዘንድሮም ምርት አልተመረተም ያሉት አቶ ብርሃኔ፤ በቀጣዩ የሽብር ቡድኑን በመደምሰስና የተፈናቀሉ ወገኖችን ወደቀየው በመመለስ በተሟላ ቁመና ምርት ማምረት እንዲችሉ ለማድረግ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጎን በመሰለፍ የሽብር ቡድኑን እየተፋለሙ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

ሌላኛዋ ሞዴል አርሶ አደር ወይዘሮ ታፈሱ ፈረደ እንደተናገሩት፤ የሽብር ቡድኑ ትህነግ ዋና አላማ አማራ ምርት እንዳያመርት በማድረግ በክልሉ ድህነት እንዲስፋፋ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ዓላማውን ባለፈው ዓመት በፈጸመው ወረራ በግልጽ አሳይቷል፡፡

ባለፈው ዓመት በሽብር ቡድኑ ወረራ ምክንያት አብዛኛው አርሶ አደር ቤቱን ጥሎ በመሰደዱ የተዘራው እህል የሚያርመው እና የሚንከባከበው በማጣቱ በአረም ተውጦ ቀርቷል፡፡ በዘንድሮው የምርት ዘመንም የሽብር ቡድኑ እኩይ አላማውን ለመድገም ቢፈልግም የመቃ ዘጠኝ ጭቃ ቀበሌ አርሶ አደሮች በቅንጅት በኩታ ገጠም ከማረስ ባለፈ ለመከላከያ ሰራዊቱ ደጀን መሆን በመቻላቸው የሽብር ቡድኑን እኩይ ዓላማ ማክሸፍ መቻላቸውን አመላክተዋል፡፡

ዜና

## ‹‹መንግስት የትህነግ ወንጀለኛ መሪዎችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዶክተር ትሁት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ የሽብር ቡድኑ አመራሮች መልካቸውንም ሆነ ባህሪያቸውን አልቀየሩም ያሉት ዶክተር ትሁት፤ ስለዚህ ህዝቡ ሰላም ማግኘት የሚችለው የአሸባሪው ትህነግ አመራሮች ተይዘው ለፍርድ መቅረብ ሲችሉ ብቻ ነው። እንዲህ አይነቱ ነገር በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ እንዳይደገም ትምህርት መሆን አለበት ሲሉም ነው ያሳሰቡት።

አንዳንድ የዓለም መንግስታት በጭፍን ትህነግን እየደገፉ እንደሚገኙ በመጠቆም፤ ሕወሓት በምክር ቤትም በአሸባሪነት የተፈረጀ ቡድን ነው። የሚገርመው የአሜሪካ መንግስትም ከዚህ በፊት ‹‹ሽብርተኛ›› ብሎ ፈርጆት የነበረ በመሆኑም አዲስ ነገር አለመሆኑን ተናግረዋል።

ማህበሩ የተሳሳተ መረጃ በማስተካከል፤ ለካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር በመፃፍ፤ በካናዳ ምክር ቤትና በዙምም ቀርበው እውነታውን በማስገንዘብ የሕወሓት ትክክለኛ ማንነት እንዲጋለጥ እየሰሩ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

አሸባሪ ቡድኑ ለትግራይ ህዝብ እንኳን የሚያስብ ባለመሆኑ መንግስት ይህንን ጦርነት እንዲጨርሰው ነው የእኔ ፍላጎት። በየቦታው እየሄዱ እያደረጉ ያሉትን ጥፋት እንዲቀጥሉ የሚፈቀድላቸው ከሆነ የተቸገረውን ሕዝብ ለመደገፍም ያስቸግረናል። ስለዚህ መንግስት የሚከፈለውን ሁሉ ዋጋ ከፍሎ ሰላም ማስከበር አለበት።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን አምባገነንነቱንና ለህዝብ የማያስብ መሆኑን ለአለም አስመስክሯል። ስልጣን ላይ በቆየባቸው ዓመታት ሁሉ ህዝቡ ተገዝቶለት፤ የሚፈልገውን ሁሉ አድርጓል፤ ግን ይህ አልበቃ ብሎት ኢትዮጵያን ለማተራመስ የጥፋት መንገድ ጀምሯል።

የአሸባሪው ሕወሓት ስብስብ እኛ ካልገዛን የሀገሪቱ ህዝብ ሁሉ ይጥፋ የሚል አቋም ይዘው ግፍ እየፈፀሙ ይገኛሉ ያሉት ዶክተር ትሁት፤ ረጃጅም እጆቻቸው ከአማራና ከአፋር ክልል አልፈው በኦሮሚያና ሌሎች ክልሎችም ደርሰዋል። በተለይ ከሸኔ ጋር በፈጠሩት ጥምረትና እያደረጉ ባሉት እንቅስቃሴ ከጥፋት ውጪ ምንም አጀንዳ እንደሌላቸው በግልፅ አሳይተዋል ነው ያሉት።

ከስልጣን ሲወርዱ አመስግነው መደበኛ ህይወታቸውን መቀጠል ይችሉ ነበር፤ ነገር ግን ‹‹እኛ ይህችን ሀገር ካልገዛን መጥፋት አለባት›› በሚል አመለካከት ትግራይ መሽገው የአገር መከላከያ ሰራዊት ላይ ያደረሱት ግፍ ታሪክ አይረሳውም።

ከትግራይ አልፈው አማራና አፋር ክልል ድረስ በሶስት ዙር ጦርነት ከፍተው ያደረጉት ጭፍጨፋ በጣም የሚያሳዝን ነው። በዚህ ሁሉ ምንም ለሰላም ፍላጎት እንደሌላቸው አሳይተዋል።

በስልጣን በቆዩበት ዓመታት የዘረጉት የዘረኝነት አስተሳሰብ ሕዝብ እንዲገዳደል እያደረገ በመሆኑ በጎሳ የተከፋፈለ ህዝብ እንዲገዳደል የሚያደርግ ስርዓት መቅረት አለበት።

ሁሉም ሰው ነፃነቱ እና ሰብአዊነቱ ተከብሮ የትኛውም ክፍለ ሀገር ተንቀሳቅሶ ንብረት አፍርቶ፤ ልጆቹን በፈለገው ቋንቋ አስተምሮ መኖር የሚችልባት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ይገባል። ለዚህም ጎሰኝነት ወይም ማንነት ላይ ያነጣጠረ ፅንፈኝነት ከመሰረቱ ማድረቅ ይገባል።

## የትግራይ እናቶች ልጆቻቸውን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አሸባሪው ሕወሓት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደረሰው በደል አልበቃ ብሎት ጦርነቱን በቆቦ በኩል ራሱ ጀምሮ የትግራይን ህዝብ መንግስት ጦርነት ከፈተብን በማለት እያታለለ መሆኑን ገልጿል፡፡

በመሆኑም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ሆነ የትግራይ ህዝብ በሽብር ቡድኑ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ መደናገር የለበትም ነው ያለው፡፡

በዚህም የትግራይ እናት ልጇን ከአሸባሪው ደብቃ ማስቀረት አትችልም፤ ምክንያቱም ሁሉም ቦታ በሽብር ቡድኑ ኔትወርክ የተሳሰረ በመሆኑ ከዕይታቸው ማምለጥ አይቻልምና ይላል።

በትግራይ ክልል ፈልጎ ለውጊያ የሚሰለፍ ወጣት የለም የሚለው ጋዜጠኛ ፍጹም፤ ከሽብር ቡድኑ ኔትወርክ ለማምለጥ ዞንና ቀበሌ ቀይረው የሚሄዱ ህፃናትና ወጣቶች ባሉበት ታድነው ታስረው ወደ ጦርነት እንደሚገቡ ገልጿል፡፡

በዚህም የትግራይ እናቶች ህፃናት ልጆቻቸውን ከአሸባሪው ሕወሓት አደን የሚደብቁበት አጥተው እየተነጠቁ ለጦርነት እየተማገዱባቸው መሆኑን ተናግሯል።

“የትግራይ ህጻናትና ወጣቶች እየታደኑ ወደ ውጊያ እንዲገቡ ይገደዳሉ፤ ወደ ኋላ እንዳይመለሱም አሸባሪ ቡድኑ ገዳይ ስኳዶችን አዘጋጅቶ በጥይት ይጨፈጭፋቸዋል” ሲልም ነው የተናገረው፡፡

የሚዋጉት ከፊትና ከኋላቸው በጥይት ተከበው ሞትን ብቸኛ አማራጫቸው አድርገው መሆኑን ገልፆ፤ “ወደ ኋላ ሸሽታችኋል” በሚል በሕወሓት አመራሮች የሚገደሉ ወጣቶችን በአይኔ አይቻለሁ ብሏል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ህዝብ ላይ የሚያደርሰው በደል ያሰለቻቸው ወጣቶች “ዓላማ ለሌለው ጦርነት አንዋጋም” በማለታቸው የሽብር ቡድኑ ሰራዊት ተበትኖ እንደነበር ገልጾ፤ በክልሉ በዘረጉት ኔትወርክ አማካኝነት አስገድደው ወደ ውጊያ እንዲገቡ አድርገዋቸዋል፤ እስካሁን የታሰሩ ወጣቶችም አሉ ብሏል፡፡

የትግራይ ህዝብ አሸባሪው በኃይል አፍኖ ይዞት በችግር ላይ ይገኛል የሚለው ጋዜጠኛው፤ ህዝቡ ሃሳቡን እንዳይገልፅ፣ ብሶቱን እንዳያሰማ በጭንቅ ውስጥ ይገኛል ብሏል።

አሸባሪው ሕወሓት የትግራይን ህዝብ ከረሃብ አልታደገውም፤ ከመሞት አላዳነውም፤ አንዳች ጠብ የሚል ነገር አላደረገም ብሏል፡፡

በትግራይ ክልል ሚዲያዎች የሚነገረውና መሬት ላይ ያለው ሀቅ ፍፁም የተለያየ መሆኑን ገልጾ፤ የትግራይ ህዝብ ከዚህ የባሰ ስቃይ ስለማይደርስበት ማንኛውንም መስዋዕትነት ከፍሎ ከሽብር ቡድኑ አፈና መውጣት አለበት ብሏል፡፡

## ‹‹ወረራና መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት››...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ተነግሮና ተዘክሮ የማያልቅ ግፍ የተፈጸመባቸው አድኖ፣ ገሃነም (ግህንብ) /የኢትዮጵያው አሽዊዝ/፣ደጀና፣ ምንምኔ፣ባዶ ስድስት፣ ከፍተኛ እልቂት የተፈጸመባቸው የጅምላ መቃብሮች የሚገኙባቸው ስፍራዎች ሲሆኑ ተርካን (ሁመራ ኤርፖርት) ና ሁመራ ሆስፒታል ስልታዊ ግድያ የሚደረግባቸው ናቸው።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ላለፉት 18 ወራት ሲያስጠና የቆየው ‹‹ ወረራና መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት›› የጥናቱ ዳራ፣ የታሪክና ማንነት ወረራ፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ ወረራና ኢኮኖሚያዊ ምዝበራ፣ በጤናና ትምህርት ላይ የተፈጸመ ግፍ፣ የመገናኛ ብዙኃን አፈና፣ መደምደሚያና ምክረ ሃሳብ የሚሉ ሰባት ምዕራፎች ያሉት ጥናት አድርጓል። የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ላለፉት አራት አስርት አመታት ያሳለፈውን ግፍ፣በደል፣ በሁሉም ረግድ የደረሰበትን የጉዳት መጠን በዋናነት የዘር ጭፍጨፋ፣ የኢኮኖሚ አሻጥር፣ የባህልና ቋንቋ ጥፋቱን በሌሎች ጉዳዮች ያለውን እውነት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማጥናትና በመሰነድ የግፉን ጥልቀትና ልክ የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲገነዘበው ለማድረግ ጥናቱ ተከናውኗል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አስራት አጸደወይን ስለጥናቱ ፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ዋነኛ ተልዕኮ እውነትን መፈለግ፣ ዕውቀትን ማስፋትና ማስረጽ፣ እንዲሁም የህብረተሰቡን መሰረታዊ ችግሮች በጥናትና ምርምር ነቅሶ ማውጣት የመፍትሔ ሃሳቦችን ማመላከት ነው። በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ላይ የተፈጸመውን መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት ጥናት ሲደረግ ከዚህ መሰረታዊ ሃሳብ መነሻ ነው ይላሉ።

የጥናቱ ዋና አላማ የሚፈጸሙ ማንነት ተኮር ወንጀሎችና ጭፍጨፋዎች እየተለመዱ እንዳይመጡ፣ ትውልዱ እንዲማርባቸውና ዳግም እንዳይፈጸሙ በልዩ ሁኔታ መጠናት ስለሚገባው እንደሆነ ዶክተር አስራት አጸደወይን ይናገራሉ።

‹‹ ወረራና መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት›› የሚለው የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ውጤት ሕወሓት ወልቃይት፣ ጠገዴንና ጠለምትን በኃይል ተቆጣጥሮ በነበረበት ዘመን በህዝቡ ላይ ያደረሳቸው ሰብአዊ፣ ታሪካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግፎች ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ሁሉንም የጥናት ስልቶች በመጠቀም ናሙናዎችን በመውሰድ የተሰራ ነው። አጠቃላይ ሕወሓት ባደረሰው ውድመት ዙሪያ ሙሉ ጥናት አልተካሄደም። ስለዚህ ያልተነገሩ፣ ያልተጠቀሱ ተጨማሪ ጥናት የሚጠይቁ ጉዳዮች እንዳሉ በጥናቱ ተመላክቷል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጥናት እንዲካሂድ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት አካባቢ በ1984 ዓ.ም ሕወሓት ወደ ትግራይ ክልል እንዲካለል ማድረጉን ተከትሎ በርካታ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በማህበረሰቡ ሲቀርቡ መቆየታቸው፤ ለአመት የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲፈጸሙ እንደነበርና በሺዎች የሚቆጠሩ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደተፈናቀሉ፣ ማንነቱን ተነጥቆ ሌላ ማንነት ተጭኖበት የኖረ ማህበረሰብ እንደነበር ከመነሻ ምክንያቶች መካከል ናቸው።

ሕወሓት ከማዕከላዊ መንግሥት መነሳቱን ተከትሎ በተፈጠሩ አለመግባባቶች የጦር ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቶ ጥቅምት 24 ቀን 2014 በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት መሰንዘሩና መንግስት የህግ ማስከበር እርምጃ እየወሰደ በነበረበት ወቅት በማይካድራ ከተማ በንጹሃን ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ ማካሄዱ፤ የአካባቢው ተወላጆችና የሕወሓት አባላት ሳይቀሩ የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት እማራዎች ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል መፈጸሙንና በርካታ የጅምላ መቃብሮች መኖራቸውን በየጊዜው ጥቆማ ሲሰጡ መደመጣቸው ለአብነት ይጠቀሳሉ።

ለታላቋ ትግራይ ምስረታ እውን መሆን ለ10 አመታት እንቅስቃሴዎችን ሲያደረግ የቆየው ሕወሓት በተለይም በ1972 ዓ.ም ጀምሮ ከደደቢት በረሃ የጀመረው የመስፋፋት ጉዞ ተከዜን ተሻግሮ ወደ ጎንደር (በጌምድር) ይዞታዎች በመግባት ወልቃይት ጠገዴና ጠለምትን በወረራ በመያዝ በአካባቢው ዋነኛ ባለእርስት የሆኑትን ነባር አማራዎችን በኃይል እያፈናቀለ በምትኩ በአስር ሺ ለሚቆጠሩ በታሪክ ከሚታወቀው ትግራይ ክፍለ ሀገር ከሱዳን በስደት ይኖሩ የነበሩ የትግራይ ተወላጆችን የሕወሓት ቡድን አባላትን በማሰባሰብ በሁመራ፣ በወልቃት፣ በጠገዴ ነባሩን ህዝብ እያፈናቀሉ ወረራቸውን መጀመራቸውን ጥናቱ በዝርዝር ያስረዳል።

ሕወሓት ገና በ1968 ዓ.ም ጀምሮ ሲመሰረት ያወጣው መርህ የጎንደር አካል የሆኑትን ወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምትን የትግራይ አካል እንዲሆኑ ደምድሞ መነሳቱ ነው። በታላቋ ትግራይ ምስረታ እቅድ መሰረት ህገ መንግስቱ ከመጽደቁ በፊት አካባቢዎቹን በኃይል የትግራይ ግዛት አካል እንዲሆኑ አደርጓል። ይህን ተከትሎም የአካባቢው ነባር የአማራ ማህበረሰብ በማንነታቸው ምክንያት ለእስር ተዳርገዋል፣ተሳደዋል፤ ተገድለዋል። በፍኖተ መርሁ ‹‹የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ትግል ዋና አላማ ጻረ አማራ ብሔራዊ ጭቆና›› ብሎ አማራን እንደ ህዝብ ጠላት በማድረግ በሌሎች ኢትዮጵያውያን የተጠላና ሁሉም ጦር የሚመዝበት እንዲሆን አድርጎ መዋቅሩን ዘርግቶ ሰርቷል።

የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት አካባቢዎች በታሪክ ከጥንት ጀምሮ አከላለላቸው በጎንደር ክፍለ ሀገር ስር እንደነበሩ የታሪክ ድርሳናት የሚያሳዩ ሲሆን፤ በአንጻሩ አካባቢዎቹ በትግራይ ስር እንደነበሩ ሊያሳይ የሚችል አንድም እንኳን መረጃ ማግኘት እንዳልተቻለ ጥናቱ ያረጋግጣል።

ሕወሓት ኢትዮጵያን እንደ አገር ከተቆጣጠረ በኋላ በመጀመሪያ ከወሰዳቸው አበይት ስራዎቹ አንዱ ገና ከጅምሩ በማኒፌስቶው ባሰናዳው መሰረት ቀድሞ የነበረው ካርታ መቀየር ነው። በ1983 ዓ.ም ኢትዮጵያን ማስተዳደር እንደጀመረ ከትግራይ ጋር ምንም አይነት፣ የባህል፣ የቋንቋና የታሪክ ግንኙነት የሌላቸውን የወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምትና ራያ ማህበረሰቦች ወደ ትግራይ በኃይል አካለለ። ከዚህ በኋላ በአካባቢው የነበሩ ለተስፋፊነታቸው ራዕይ እንቅፋት ይሆኑብናል ያሏቸውን ታሪክ አዋቂዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ክፍፍልን የሚጠየፉ የማህበረሰቡን የቁርጥ ቀን ጀግኖች በማደን እየመነጠሩ ማጥፋት እንደ ስልት አድርጎ ተጠቅሟል።

በዚህ ሳቢያም የሕወሓትን ከፋፍለህ ግዛ የጠሉ የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ጀግኖች አንቀበልም በማለት ትግል በማድረግ ሲሰው ቀሪዎቹ አገር ለቀው ተሰደዋል። ወልቃይት እና አካባቢው የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች ስያሜ እስከመቀየር የደረሰ ታሪካዊ ወረራ ተፈጽሟል።

የቃብቲያ አዲህአርዲ ከተማ ነዋሪው ህዳር 12 ቀን በ2012 ዓ.ም የሚካኤል በአል በሚያከብሩበት ወቅት በትግርኛ ካልሆነ በአማርኛ እንዳይዘፍኑ የተከለከሉበት አንዱ የባህልና የታሪክ ወረራው ማሳያ ነው።

ወራሪው ሕወሓት የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት አካባቢዎችን በመጡበት ቦታ መሰየም፤ በአማራ ህዝብ ላይ የፈጸመው ወንጀል መከፋፈል፣ ስያሜ መስጠት፣ የሰውነት ባህሪን መግፈፍ፣ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ማድረግ፣ ዝግጅት ማድረግ፣ ማስወገድ፣ ወንጀልን መካድ ከሰራቸው ግፎች መካከል ናቸው።

በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ላይ ዘርፈ ብዙ የሆነ የዘር ማጥፋትና በሰብአዊነት ላይ የተቃጣ ወንጀል ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጽሟል። ለአብነት ግድያ፣ ማሳደድ፣ መሬት መቀማት፣ ከፍተኛ ግብር መጫን፣ በወረራ መሬትን መቆጣጠር፣ የማሸማቀቂያ ቃላትን መጠቀምና ሴቶች ያለፍላጎታቸው እንዲወልዱ ማድረግ ተጠቃሽ ናቸው። ዕድሜ ሳይለይ ከህጻን እስከ መነኩሴ አስገድዶ መድፈር ፈፅሟል። ይህ ሁሉ ማሳደድ የዘር ማጽዳት ወንጀል ከጀርባው የተሸከመው ፖለቲካዊ አጀንዳ የአካባቢውን ህዝብ በማሳደድ አዲስ ማንነት ያለው ማህበረሰብ መፍጠር ሲሆን፤ ጥቃቱ የተናበበና ዘርፈ ብዙ መሆኑን ጥናቱ በስፋት አሳይቷል።

ሕወሓት በአማራ ህዝብ ላይ ሲፈጽማቸው የነበሩ ወንጀሎች ከከፍተኛው እስከ ዝቅተኛው ሲታይ 73 ነጥብ 5 በመቶ የማሳደድ፣ 58 ነጥብ 5 በመቶ የመታሰር፣ 35 ነጥብ 5 በመቶ መፈናቀል፣ 27 ነጥብ 6 በመቶ የሚሆነው ህዝብ ግድያና 23 ነጥብ 1 በመቶው ግርፋት አድርሷል።

በአስር ሺ የሚቆጠሩ የጠለምት ተወላጆችን በግፍ እንዲጨፈጨፉ አድርጓል። በአማራ ህዝብ ላይ የተፈጸሙ የወንጀል አይነቶች በአለማችን ላይ ከታዩት ሁሉ የከፉ ናቸው። ጉድጓድ ቆፍረው አንገቱን ብቻ አስቀርተው ጨው ቀብተው ለከብት ሰጠተውታል። ይህን የሚያይ ሁሉ ትልቅ የስነ ልቦና ስብራት እንዲገጥመው አድርገዋል። ወልቃይት ሕወሓት አማራን ለማጥፋት እንደቤተ ሙከራ ተጠቅሞበታል። ከ1970ቹ ጀምሮ ጥቅምት 2 ቀን 2013 ዓ.ም አካባቢውን ለቆ እስከወጣበት ድረስ በተጠና መንገድ የመግደል ስራ ለአፍታም አላቋረጠም።


በገሃነም 59 ሺ ንጹሃን በግፍ ተገድለዋል። በሁመራ ሆስፒታል፣ ትርካን (ሁመራ ኤርፖርት) ማይካድራ በአደባባይ የዘር ጭፍጨፋ ተደርጎበታል። ሌላው ወረራና ኢኮኖሚያዊ ምዝበራ በግብር አከፋፈል፣ በስራ ምደባ፣ በኢንቨስትመንት፣ በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ማንነትን መሰረት ያደረገ ኢኮኖሚያዊ አድልኦ ተፈጽሟል። ባደረገው የመሬት ነጠቃና ማፈናቀል በ1960ዎቹ የወልቃይት ሰቲት ሁመራ ገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር ሲሰራ መኖሩን በሚጠቀሙበት የሰሊጥ መቀበያ ደረሰኝ ማረጋገጥ ተችሏል። ነገር ግን በ1984 ዓ..ም ይህን የገበሬዎችን ማህበር አፍርሶ የሕወሓት ድርጅት ክንፍ የነበረው ሂወት እርሻ በጉልበት ይዞ እንደነበር ሲታይ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ምዝበራ ማድረሱን የሚያረጋግጥ ነው።

በጤናና ትምህርት ላይ በዘመነ ሕወሓት ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች 88 በመቶ የሚሆኑት የህክምና አገልግሎት እንዳያገኙ አድርጓል። በህክምና ተቋማት ብሄርን መሰረት ያደረገ ስልታዊ ግድያ አካሂዷል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በአስገዳጅ ሁኔታ በትግርኛ እንዲሰጥ መደረጉና አማርኛ ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ እንዲሰጥ መደረጉ ሳይወድ በግድ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ትግርኛ እንዲሆን መደረጉ አንዱ በትምህርት ላይ ታቅዶ የተሰራ መሆኑ በጥናቱ ተለይቷል።

በሌላ በኩልም የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች በመገናኛ ብዙኃን እንዳይዘገቡና እንዳወጡ፣ የግድያ፣ እስር፣ ድበደባ፣ ማንነትን ማንቋሸሽ ማፈናቀልና ማሳደድ ሲደርስ እንዳይዘገብ ለሚዲያ ዝግ አድርጎ ግፍ መፈጸሙን ‹‹ወረራና መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት›› በሚል የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ያጠናው የጥናት ውጤት በስፋት አመላክቷል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሄት




**ኦቲዝም**

ገጽ 8

**ዘመናዊ እና ባህላዊ የመስኖ ዘዴዎች የሚተገበሩበት የወይቦ መስኖ ፕሮጀክት**

ገጽ 14




**‹‹ህዝቡ ሰላም ማግኘት የሚችለው የአሸባሪው ሕወሓት አመራሮች ተይዘው ለፍርድ መቅረብ ሲችሉ ብቻ ነው››**

*- ዶክተር ትሁት አስፋው*

*ኢትዮ-ካናዳውያን ኔትወርክ ለቅስቀሳና ለማህበራዊ ድጋፍ ፕሬዚዳንት*

ገጽ 6



**"ቢያንስ የእኔ መከራ በልጆቼ አይደገም....."**

ገጽ 17

## በውስጥ ገጾች


“የነገይቱ ወረቀት አልባዋ ኢትዮጵያ ¡?” ገጽ 9

እንግዳ ነገር ሲሆን ...! ገጽ 12

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ህዝቡ ሰላም ማግኘት የሚችለው የአሸባሪው ሕወሓት አመራሮች ተይዘው ለፍርድ መቅረብ ሲችሉ ብቻ ነው››

- ዶክተር ትሁት አስፋው
ኢትዮ-ካናዳውያን ኔትወርክ ለቅስቀሳና ለማህበራዊ ድጋፍ ፕሬዚዳንት

ማህሌት አብዱል

ሻሸመኔ ከተማ ውስጥ ነው የተወለዱት፤ ያደጉትና የተማሩት ግን አዲስ አበባ ነው። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ቤተልሄምና አብዮት ቅርስ በተባሉ ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተውም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ አግኝተዋል። እንደተመረቁ ሞርጌጅ ይባል በነበረ ባንክ በተማሩበት ሙያ ተቀጥረው ለሶስት ዓመታት አገለገሉ። በመቀጠልም ሴፍ ዘ ችልድረን ኖርዌይ በተባለ ድርጅት ጅማ ተመድበው ሁለት ዓመት ከሰሩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ኬር ኢትዮጵያ በተባለ ድርጅት ከ10 ዓመት በላይ አገልግለዋል።

በዚሁ ድርጅት አማካኝነት ኖርዌይ ተልከው ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ናቹራል ሪሶርስ ማኔጅመንት ተምረዋል። ከኖርዌ ተመልሰው በላካቸው ተቋም ውስጥ ለሁለት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ደግሞ የውጭ ነፃ ትምህርት እድል ተወዳድረው ካናዳ ለ ስነ ፃታ እና ብዝሃ-ሕይወት ዘርፍ ለአምስት ዓመታት ተምረው የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አገኙ። በሙያቸው እዛው ካናዳ ውስጥ ስራ አግኝተው ቀሩ። ከ21 ዓመታት በላይ በቆዩባት ካናዳ ትልልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የተሳተፉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ማዕድን ቁፋሮ ሲሰሩ በተፈጥሮ ሃብትና በህብረተሰቡ ጤና ላይ ምን አይነት እክል እንደሚፈጥሩ ጥናት በማድረግና ለሚመለከተው አካል ምክረ-ሃሳብና የፖሊሲ ግብዓት በመስጠት ረገድ ከፍተኛ እውቅና የተቸሩ ኢትዮጵያዊ ሴት ናቸው። በተጨማሪም እንደ ኤች. አይ.ቪ እና ቲቢ በተባሉ ተላላፊ በሽታዎች ዙሪያ ብዙ ጥናቶችን አካሂደዋል። በዚያው በሚኖሩበት አገር ውስጥ ሚኒስትሮች የፖሊሲ አማካሪ ሆነው ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል። ካለፉት ሁለት ዓመታ ወዲህ ደግሞ በአገሪቱ ተከስቶ በነበረው ግጭት እንዲሁም ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ለተጎዱና ለተፈናቀሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተጨማሪም ለቆሰሉ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ከዲያስፖራው ማህበረሰብ ገንዘብ በማሰባሰብ ለህዝብና ለአገራቸው ያላቸውን አጋርነት በተግባር አረጋግጠዋል። በተለይም በካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የሚያሳትፍ ህጋዊ ድርጅት እንዲቋቋም እንግዳችን መሰረት ስለመጣላቸው ይነሳል። በዚህ ድርጅት አማካኝነት አሁንም ድረስ ተከታታይነት ያለው የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ስራ በመስራት ላይ ይገኛሉ። በዚህ የድጋፍ ስራቸውና በወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ ዙሪያ ኢትዮ-ካናዳውያን ኔት ወርክ ለቅስቀሳና ለማህበራዊ ድጋፍ ፕሬዚዳንት ዶክተር ትሁት አስፋው ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።


ፎቶ ፡- ፀሐይ ንጉሴ

**አዲስ ዘመን፡- በኦሮሚያ ክልል ጉጂና በአማራ ክልል ዘጌዬ ማህበረሰብ ዙሪያ ስላጠኑት ጥናት በጥቂቱ ይንገሩንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ዶክተር ትሁት፡-** ልክ ነሽ፤ የማስተርስ ዲግሪዬን ጉጂ ማህረሰብ ላይ ነው የሰራሁት። ከአንዲት ፊላንዳዊ አጥኚ ጋር በመሆን ለአራት ወራት ከማህበረሰቡ መሃል በድንኳን ተቀምጠን ያካሄድነው ጥናትና እዚያ የቆየንበት ጊዜ ዛሬ ድረስ የማይጠፋ ደስ የሚል ትዝታ አለኝ። የጉጂ ህዝብ ምን አይነት ጨዋና ሰው አክባሪ መሆኑን በተጨባጭ ማረጋገጥ የቻልኩት በዚያ ጊዜ ነበር። የሚገርምሽ እኛ ድንኳን ውስጥ በምናድርበት ጊዜ የአካባቢው አባቶች ‹‹ልጆቻችን አንድ ነገር ቢሆኑ የእኛ ስም ነው የሚጠፋው›› ብለው አራት ወር ሙሉ ሳይታክቱ ተራ በተራ እየጠበቁን ነበር የሚያድሩት። አሁን ድረስ ሳስበው የማህበረሰቡ ቅንነት ያስገርመኛል።

የጉጂ ማህበረሰብ እንደሚታወቀው አርብቶ አደሮች ናቸው፤ ከአካባቢያቸው ካለው ከጌዲዮ ህዝብ ጋር ብዙ ጊዜ በዚህ በተፈጥሮ ሃብት በግጦሽ መሬት የተነሳ ግጭት አለ። እናም የእኔ ጥናት የግጭት አፈታት ባህላቸው ምን ይመስላል በሚል ነበር ጥናት ስናደርግ የነበረው። አባ ገዳዎችንና ህዝቡን ቁጭ ብለን እናወያይ ነበር። በጥቅሉ የህዝቡን የግጭት አፈታት ማህበራዊ እሴቶች ምን እንደሚመስል ነው ያጠናነው። እግረ መንገዴንም ኦሮምኛ ቋንቋ መልመድ ችዬ ነበር። በነገራችን ላይ አፋርም ላይ ተመሳሳይ ጥናት አጥንቻለሁ።

የዶክትሬት ዲግሬዬን ደግሞ በአማራ ክልል ባህር ዳር ጣና ሃይቅ ላይ ባለችው ዘጌዬ ደሴት ላይ ነው ያጠናሁት። ይህች ደሴት በጣም የሚያስደንቅ የተፈጥሮ ታሪክ ያላት ስትሆን፤ የህብረተሰቡም አመጣጥ አስገራሚ ነው። ጫካው ከየት መጣ? ቡናው እንዴት ሊበቅል ቻለ? የሚል ነበር አንዱ ጥናቴ። የሚገርመው ቡና ከደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ የሚበቅል ቢሆንም ዘጌዬ ጫካ ውስጥ ቡና እና የተለያዩ ፍራፍሬዎች አሉ። በጣም አስደናቂ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት ያለባት ደሴት ናት። ጥናታችን ከደሴቷ የተፈጥሮ ሃብት ባሻገር የሕብረተሰቡ ማህበራዊ ህይወታቸው ዙሪያ በተለይም በሴቶች ላይ የሚደረገው ጫና፤ ኑሯቸውን እንዴት እንደሚገፉ የመሳሰሉት ጉዳዮች ነው ያጠናነው። እዚያም የግጭት አፈታትና የሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ሚና ዙሪያ አጥንቻለሁ። በተማርኩበት ዩኒቨርሲቲ በጣም የተወደደና እውቅና የተቸረው ጥናት ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ዲያስፖራውን በማስተባበር በአገሩ ጉዳይ ተሳታፊ እንዲሆን የማድረጉን ስራ የጀመሩበት አጋጣሚ ምን ነበር ?**

**ዶክተር ትሁት፡-** እንደምታስታውሽው የዛሬ ሁለት ዓመታት ገደማ ሙዚቀኛ ሃጫሉ መገደሉን ተከትሎ በአገሪቱ የተፈጠረውን ቀውስ በተለይ ማንነት ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች በዝተው ነበር። እኛ ካናዳ የምንኖር ኢትዮጵያውያን የችግሩ ተባባሪ ሆነን እንጂ የመፍትሔ አካል ለምን መሆን አልቻልንም? በሚል ውይይት ጀመርን። ለህዝባችን ድምፃችንን ማሰማት አለብን የሚል ድምዳሜ ላይ ደረስን። በመቀጠልም የሰላም ውይይት ማካሄድ አለብን ብለን ዲያስፖራውን የሚያሳትፍ ማህበር አቋቋምን። ይሁንና በኮቪድ ምክንያት ውይይታችንን በዙም ነበር የምናካሂደው የነበረው። እኔ ደግሞ ጉጂ ማህበረሰብ ውስጥም ስለኖርኩኝ እንዲህ አይነቱ የመገፋፋት ባህል ከየት መጣ የሚል ጥያቄ ፈጥሮብኝ ስለነበር እንዲህ አይነቱ ፀያፍ ልምድ ለማስወገድ ማህበረሰቡን የማንቃትና የመፍትሄ ሃሳብ የማፈላለግ ስራ እሰራ ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ‹‹እኔም የወንድሜ ጠባቂ ነኝ›› እንዳሉት እኛም የሚገድለውም ሆነ የሚገደለው ህዝብ የእኛም ወገን በመሆኑ ዝም ማለት የለብንም፤ ለማስቆም የየበኩላችን ለመስራት ወስነን መንቀሳቀስ ጀመርን። በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ባለሙያዎችን እየጋበዝን የውይይት መድረክም እናዘጋጅ ነበር። ከእነዚህም መካከል ‹‹የጥላቻ ንግግሮችና አደጋው›› የሚለውን ነገር ከነሩዋንዳ ከመሳሰሉት አገራት ተሞክሮ በመውሰድና አገራችንንና ህዝባችንን እንዴት መታደግ እንደምንችል እንመክር ነበር። እንደምታውቂው ሩዋንዳ መግደል ከመጀመሩ በፊት አንዱ ሌላውን ህዝብ ‹‹በረሮ›› የሚል ስያሜ ነበር ሲሰጣቸው የነበረው። ሰውን ያህል ፍጡር ‹‹በረሮ›› ብለን ካመንን ለመጨፍለቅም ሆነ ለመግደል አይከብደንም። ስለዚህ ይሄ በጣም ከባድ ነገር ነው ብለን በዚያ ላይ ትምህርት እንዲሰጥ አድርገናል። ሰው ሁሉ ውስጡ በጣም ተጎድቶ ስለነበር እየመጣ ያዳምጣል፤ ይወያያል፤ በአጠቃላይ ብዙ ሰው ነበር የሚሰባሰበው። እዚህም ከሰላም ሚኒስቴር ጋር የግኑኙነት አግባብ ፈጠርንና እየጋበዝናቸው በውይይቱ ላይ ይሳተፉ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን የሰሜኑ ጦርነት ሲነሳ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ባደረገው ጥሪ ከመላው ካናዳ ብዙ ሰዎች ተሰባስበን ሩቅም ብንሆን ለወገኖቻችን ማድረግ በምንችልበት ጉዳይ መከርን። ከዚህ ቀደም አሜሪካ ያሉ ድርጅቶች ጠንካራ ቢሆኑም ካናዳ ግን ብዙ እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴ አልነበረም። ስለሆነም እኛም አንድ ማድረግ አለብን ብለን ተነሳን። በነገራችን ላይ ካናዳ በርካታ ኢትዮጵያዊ ነው የሚኖረው። ስለዚህ ጠንከር ብለን መውጣት አለብን ብለን እንደድርጅት ተቋቋምን። በዚህ መሰረት ኢትዮጵዮ-ካናዳውያን ኔትወርክ ለቅስቀሳና ለማህበራዊ ድጋፍ በሚል ድርጅት አቋቋምን ። እኔም የድርጅቱ ፕሬዚዳንት ሆኜ ተመረጥኩኝ። ሌሎችን ሰዎች አሰባስበን በመላው ካናዳ ll ቅርንጫፍ ከፈትን።

መጀመሪያ ለመከላከያ ሰራዊታችን ድጋፍ እናድርግ ብለን ገንዘብ ሰብስበን ላክን። ከዚያ ለሚቆስሉ የመከላከያ ሰራዊት አካላት የሚሆን የሕክምና መገልገያ ቁሳቁሶችን ለመላክ መዘርዝር አዘጋጅተን ከመላው ካናዳ አሰባሰብን። እስካሁን ጠቅላላ ወደ 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር የሚወጣ የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች ልከናል። ይህንንም ያደረግነው ከጤና ጥበቃ ጋር በቅርበት በመስራት ነው። በቀጣይ ደግሞ ለተፈናቀለው ህዝብ ገንዘብ እየተሰበሰበ በጠቅላላ በሁለት ዓመት ውስጥ ከአምስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ነው ያሰባሰብነው። ያንንም ስናደርግ ደግሞ ለህዝቡ ለራሱ በቦታው እየተገኘን ነው የሰጠነው። የጀመርነው ከአፋር ክልል ነው፤ ክልሉ እንደሚታወቀው በጦርነት በከፍተኛ ደረጃ ከተጎዱ የአገሪቱ አካባቢዎች መካከል እንደመሆኑ ምግብና ልብስን ጨምሮ የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁስ ድጋፍ አድርገንላቸዋል።

በተመሳሳይ አማራ ክልል በወሎ፣ ጎንደር፣ ባህርዳርና ደብረብርሃን በጣም ብዙ ተፈናቃዮች ያሉባቸው አካባቢ ድጋፍ አድርገናል። በመቀጠልም ቁስለኞችን ሆስፒታል ድረስ በመሄድ እየጎበኘን ድጋፍ እናደርግ ነበር። የእኛ አባላቶች እንዳውም ጎንደር ላይ ከመከላከያ ሰራዊት ጋር የገና በዓልን አብረው ነው ያከበሩት። እኛ ደግሞ በደብረብርሃን በኩል ሄደን እዛ ያሉትን ቁስለኞች ስንጎበኝ መተኛ አልጋ አጥተው ሲንከራተቱ ተመለከትን፤ እናም ከአሜሪካ ትራንስፖርት እየከፈልን በሁሉም ሆስፒታል አልጋ እንዲመጣ አድርገናል። ሰራዊታችን በጦርነቱ መጎዳታቸው አንሶ ደግሞ እንዴት መተኛ አልጋና የህክምና መገልገያ ቁሳቁስ ያጣሉ? በሚል ቁጭት በከፍተኛ መናሳሳት ህዝቡ እየተረባረበ እርዳታ ስናደርግ ቆይተናል።

ከዚያ በተጨማሪ ደግሞ የአጣዬን ታሪክ እንደ ሚታወቀው በሸኔ ቡድን ብዙዎቹ ቤታቸው ተቃጥሎ ነበር። ቤቱ እንደተቃጠለ ወዲያውኑ በዙም ስብሰባ ጠራን፤ ሻማ ከማብራትና ከንፈር ከመምጠጥ ባለፈ የተጎዱ ወገኖቻችንን መደገፍ አለብን ብለን ተነሳን። በዚያ መሰረት 160 ሺ ዶላር በአንድ ምሽት ነው ያዋጣነው። የተቃጠለባቸው ወገኖች ‹‹ስምንት ቤት ስሩልን›› ቢሉም በጉልበታቸው ራሳቸው በማገዛቸውና ወጪ መቆጠብ በመቻሉ ለአስር አባወራ ቤት መስራት ተችሏል። በአሁኑ ሰዓት የቤቶቹ ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን በጥቅሉ ቤቱን ለማሰራት በ180 ሺ ዶላር ወጪ አድርገናል።

በሌላ በኩል ከኮምቦልቻ ከ20ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኘው ሃርቡ ከተማ ላይ ከምዕራብ ወለጋ በሁለት ዙር ተፈናቅለው የመጡ 65ሺ ወገኖችን ጎብኝተን ነበር። በአዲስ ዓመት በዓልን ደግሞ 5ሺ500 ተፈናቃዮች በሬ አርደን አብረን አሳልፈናል። እነዚህ ወገኖቻችን መልሰው የሚቋቋሙበትን ስራ እንዲሰራ ከመንግስት ጋር ውይይት ጀምረናል፤ ከአማራ ልማት ማህበርም ጋርም እየተወያየን ነው። በነገራችን ላይ የአጣዬውን ቤት የገነባነው ከዚሁ ማህበር ጋር ሆነን ነው። አሁን ስንመለስ ደግሞ ሪፖርት ለዲያስፖራው አቅርበን በተከታታይ እነዚህ ወገኖቻችን ወደ መደበኛ ህይወታቸው የሚመለሱበት ሁኔታም እገዛ ለማድረግ እንሰራለን።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ሕወሓት በተደጋጋሚ ለሰላም የተዘረጉለቱን እጆች መስበሩ ከምን የመነጨነው ብለው ያምናሉ?**

**ዶክተር ትሁት፡-** እስካሁን እንዳያነው አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ አምባገነንነቱንና ለህዝብ የማያስብ መሆኑን ለአለም ያስመሰከረበት ጊዜ ነው። እኔ በጣም የሚያሳዝነኝ ስልጣን ላይ በቆዩባቸው ዓመታት ሁሉ ህዝቡ ተገዝቶላቸው፤ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ አድርገዋል፤ ግን ይህ አልበቃ ብሏቸው መላአገሪቱ ለማተራመስ የዚን ያህል ርቀት መሄዳቸው ነው። እንዳውም አመስግነው መደበኛ ህይወታቸውን መቀጠል ይችሉ ነበር፤ ምክንያቱም ማንም አልጠየቃቸውም ነበር።

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

ግን «እኛ ይህችን አገር ካልገዛን መጥፋት አለባት» በሚል አመለካከት ትግራይ መሽገው መከላከያ ሰራዊታችን ላይ ያደረሱት ግፍ ታሪክ የማይረሳው ነው። ያም ሆኖ ደግሞ አገሪቱ ሰላም ትሁን፤ ህዝቡ የሰላም አየር ይተንፍስ ተብሎ መከላከያ ከትግራይ ከወጣ በኋላ ከትግራይ አልፈው አማራና አፋር ክልል ድረስ በመውረር ያደረጉት ጭፍጨፋ በጣም የሚያሳዝን ነው።

በዚህ ሁሉ ምንም ለሰላም ፍላጎት እንደሌላቸው አሳይተዋል። እኛ ካልገዛን የአገሪቱ ህዝቡ ሁሉ ይጥፋ የሚል አቋም ነው ይዘው ግፍ የሚፈፅሙት። ረጃጅም እጆቻቸው ከአማራም፤ ከአፋርም ክልል አልፈው በኦሮሚያና ሌሎች ክልሎች ደርሰዋል። በተለይ ከሸኔ ጋር ጥምረት እያደረጉ ባሉት እንቅስቃሴ ከጥፋት ውጭ ምንም አጀንዳ እንደሌላቸው በግልፅ አሳይተዋል። በመሰረቱ ለትግራይ ህዝብ እንኳን ምንም እንደማያስቡ እያየን ለሌላ ለማን ያስባሉ ተብሎ ይገመታል?። እናም መንግስት ይህንን ጦርነት እንዲጨርሰው ነው የእኔ ፍላጎት። ምክንያቱም ተመልሰው በየቦታው እየሄዱ እያደረጉ ያሉትን ጥፋት እንዲቀጥሉ የሚፈቀድላቸው ከሆነ አይደለም ለመንግስት ለእኛ ራሱ ህዝብን እርዱ ለማለት ያስቸግረናል። ስለዚህ መንግስት የሰላም ማስከበር ስራውን የሚከፈለውን ሁሉ ከፍሎ መጨረስ አለበት።

በእርግጥ የውጭ ጫና እንዳለ እናውቃለን፤ ግን ደግሞ የውጭ ተፅዕኖውን ተቋቋሞ ጦርነቱን ዳር ማድረስ ይገባል። የውጭ ጫናውን በሚመለከት እኛም የምንሰራው ስራ አለ። ያለውን የተሳሳተ መረጃ በማስተካከል፤ ካናዳ ላለው ጠቅላይ ሚኒስትር በመፃፍ፤ የካናዳ ምክር ቤት ሁሉ እየቀረብን እውነታውን እንዲገነዘቡ አድርገናል። በዙምም እየቀረብን ስለነባራዊ ሁኔታ እናብራራለን፤ በዚህም የሕወሓት ትክክለኛ ማንነት እንዲጋለጥ አደርገናል። አንዳንድ የዓለም መንግስታት በጭፍን አሸባሪውን ሕወሓትን እየደገፉ መሆኑ ግልፅ ነው። ግን ወያኔዎች አሸባሪ መሆናቸውን በምክር ቤቱም የተረጋጋጠ ነገር ነው። የሚገርመው እኮ የአሜሪካ መንግስትም ከዚህ በፊት «ሽብርተኛ» ብሎ ፈርጆአቸው ነበር፤ አዲስ ነገር አይደለም። መልካቸውንም ሆነ ባህሪያቸውን አልቀየሩም፤ ስለዚህ ህዝቡ ሰላም ማግኘት የሚችለው የሕወሓት አመራሮች ተይዘው ለፍርድ መቅረብ ሲችሉ ብቻ ነው። እንዲህ አይነቱ ነገር በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ እንዳይደገም ትምህርት መሆን አለበት።

ሌላኛው ነገር እነሱ ለ30 ዓመታት የዘረጉት በጎሳ የተከፋፈለ ህዝብ እንዲጋደል ያደረጉት ስርዓት መቅረት አለበት። ይህንን ደግሞ በተደጋጋሚ ለመንግስት አቅርበናል። ወደፊት ማየት የምንፈልጋት ከዚህ በፊት የነበረው አይነት ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሰው በነፃነት የትኛውም ክፍለአገር ማንንም ሳይፈራ የትም ቦታ ንብረት አፍርቶ፤ ልጆቹን በፈለገው ቋንቋ አስተምሮ መኖር የሚችልባት ኢትዮጵያን ነው። ማንኛውም ቋንቋ ቢበዛ በግሌ ችግር የለብኝም፤ ግን ሰው ነፃነቱ ተከብሮ፤ ሰብአዊነቱ ተከብሮ መኖር የሚችልባትን ኢትዮጵያ ለማምጣት በመጀመሪያ ጎሰኝነት ወይም ማንነት ላይ ያነፃፀረ ፅንፈኝነት ከመሰረቱ ወይም ከምንጩ መድረቅ አለበት። ይህን የከፋት ምንጭ ማድረቅ ይገባል። ይህንን ከተደረገ በኋላ ህዝቡ አዕምሮ ላይ መሰራት አለበት። እኛ በውጭ አገራት በስደት እየኖርን ጥቁር ሆነን ከነጮች ጋር መብታችን ተከብሮ ነው ያለው። እነሱ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ተምረን፤ እነሱ የሚሰሩበት መስሪያ ቤት ሰርተን፤ እነሱ የሚያገኙትን ጥቅም እያገኘን ነው የምንኖረው። ስለዚህ እዚህ አገርም የዜግነት መብቱ የሁሉም ሰው በሚኖርበት ቦታ መጠበቅ አለበት።

ይህንን ለማምጣት ደግሞ አጥፊዎች ለህግ መቅረብ አለባቸው፤ ፍትህ መኖር አለበት፤ ያለፍትህ ሰላም አይኖርም። በወለጋ፤ በቤኒሻንጉል ሆነ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በሰዎች ላይ ጥቃት የሚያደርሱ ሰዎች ለህግ መቅረብ አለባቸው። ምክንያቱም አገር እያተራመሰ ያለው ወያኔ ብቻ አይደለም፤ ብዙ የወያኔ አይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አሉ፤ በአጠቃላይ ወያኔ የዘረጋው መዋቅር መፍረስ አለበት። አሁን እኮ እየታጨደ ያለው 30 ዓመት የተዘራው ጥላቻ ነው። ስለዚህ እዚህ ላይ መንግስት ትኩረት አድርጎ፤ ህዝቡም ተረባርቦ ያንን ስርዓት «አንፈልገውም» ማለት አለበት። ጥላቻን አልፈልግም ሊል ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ሕወሓት የሚያደርገውን የሃሰት ፕሮፖጋንዳ የተቀበሉና የተወዛገቡ የአለም መንግስታትን እውነታውን ለማሳየት ምን መሰራት አለበት ብለው ያምናሉ?**

**ዶክተር ትሁት፡-** እስካሁን ባየነው የሌላ አገራት መንግስታት እያደረጉ ያሉት መንግስት ላይ ጫና መፍጠር ብቻ ነው። እኔ እነዚህ መንግስታት የኢትዮጵያን ሁኔታ በትክክል አይረዱም አልልም፤ ብዙ የሚረዱበት መንገድ አለ፤ እያወቁ ግን እነሱን የሚያዩዋቸው እንደተጎዱ እንደተበደሉ ነው። ምክንያቱም የእነሱ ተላላኪዎች በየአለም አደባባዩ የዘር ጭፍጨፋ እንደተደረገባቸው አድርገው ስለሚጮሁ ነው። የመከላከያ ሰራዊታችንን በጨፈጨፉ ማግስት «ትግራይ ጄኖሳይድ» ብለው የጀመሩ ሰዎች ናቸው። እነሱ በውሸት የተካኑ ናቸው። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስት በአቋሙ መቆም አለበት ብዬ ነው የማምነው። ደግሞስ እድል ስንት ጊዜ ነው የሚሰጣቸው? የእርዳታ እህል ዘርፈው ወዲያው ኃይላቸውን አጠናክረው ለውጊያ ነው የወጡት፤ ይህም የአደባባይ ሚስጥር እንደነበር የሚታወስ ነው።

እንዲህ አይነቱን በከፋት የሰለጠነ ቡድን እንዴት አድርጎ ነው ወደ ሰላም ጠረጴዛ ማምጣት የሚቻለው? እስካሁን ድረስ እኮ ለሰላም ውይይት ሳይሆን ለጦርነት ሲዘጋጁና ወረራ ሲያካሂዱ ነው የቆዩት። እናም የሰላም ፍላጎቱ እንደሌላቸው ግልፅ ነው። ለሰላም ድርድር ሰው አዘጋጅተናል ቢሉም እነሱ ከውስጥ ለጦርነት እየተዘጋጁ ነበር። ይህ አልበቃ ብሎ ሰላም እንፈልጋለን ብለው መደራደሪያ ያቀርባሉ። መደራደሪያ እያቀረቡ የሰላም ውይይት እፈልጋለሁ ብሎ ነገር የለም። እናም ሃያላን አገራት ለሚባሉት መንግስት የተደረገውን ጥረት በደንብ እንዲገነዘቡ ማድረግና በአቋሙ መፅናት አለበት። እኛም ደግሞ በውጭ ያለነው በፍፁም ሰላም እየተባለ እንደገና ጦርነት እየለኮሱ ህዝብ የሚያልቅበት ነገር ሊደገም አይገባም የሚል አቋም ነው ያለን።

መንግስት በዚህ ጉዳይ ላይ ፈፅሞ መለሳለስ የለበትም ብለን ነው የምናምነው። ይሄ ጦርነት ማለቅ አለበት፤ ሌላ መንገድ የለውም። ይሄ የወያኔ የሽብርተኛ ቡድን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሰበር አለበት። የትግራይ ህዝብም ነፃ መውጣት አለበት። ምክንያቱም በዋናነት እያለቀ ያለው የትግራይ ወጣት ነው። አሁንም ከህጻን እስከ አዛውንት ለጦርነት ክተት ቅስቀሳ እያደረገ ነው። ስለሆነም ይህ ቡድን ለትግራይ ህዝብም አይጠቅምም፤ ይህ ቡድን ሰላም ያመጣል ብሎ የሚያምን የትግራይ ህዝብ አለ ብዬም አላምንም። በግድ ተገዶ በሃይል ነው የተያዘው። በነገራችን ላይ በታሪክም ብናይ የትግራይ ህዝብ በግድ የተያዘው በወያኔ ብቻ ነው። ባለፉት ዓመታትም ቢሆን የኢትዮጵያ መንግስት ከነጭራሹ አልነበረም፤ እነሱ ናቸው ህዝቡን አንቀው የያዙት። የትግራይ ህዝብም መናገር አለበት። በውጭ ያለው የትግራይ ተወላጆች ስለወያኔ ክፋት መናገር መቻል አለባቸው። ለምንድን ነው የሚሸፋፍኑት? መንግስት ግን ፀንቶ ጦርነቱን አጠናቆ ህግ ለጣሱ፣ ለገደሉ፣ ክፋት ላደረጉ ፍትህ ሊሰጥ ይገባል። የሕግ የበላይነት መከበር አለበት። የእኔ አቋም ይሄ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት በተደጋጋሚ ይሄ ጦርነት የተለፀኮ ጦርነት እንደሆነ ይገልፃል፤ በተለይ የኢትዮጵያን እድገት የማይሹ የታሪካዊ ጠላቶች እጅ እንዳለበት ያነሳል። ስለመሆኑ ከዚህስ አኳያ ምን አይነት የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ይገባል?**

**ዶክተር ትሁት፡-** ይሄ በጣም ግልፅ ነው፤ እንዳነሳሽው የውጭ ሃይሎቹ የሚፈልጓት አገር ደካማ ኢትዮጵያን ነው። በእነሱ ላይ ጥገኛ የሆነች፤ ሁልጊዜ የእርዳታ እህል እየለመነች የምትኖር ኢትዮጵያ ነው የሚፈልጉት። ይህንን ደግሞ በተለያየ መልኩ ግልፅ አድርገውልናል። ስለዚህ ከእነዚህ ሰዎች የምንጠብቀው ነገር የለም። ግብፅ የራሷ ፍላጎትና አጀንዳ አላት። ለዘመናት 80 በመቶ በላይ ውሃ ተጠቅማ በርሃ የሆነ መሬቷን ማልማት ችላለች። ኢትዮጵያ ግን የራስዋን ውሃ እንኳን እንዳትጠቀም ሲያደርጉ ነው የኖሩት። እናም የኢትዮጵያ ህዝብ ሞኝ መሆን አይገባውም። ኢትዮጵያ ምንም አይነት ወዳጅ ከውጭ አገራት አሉኝ ብላ ማመን የለባትም። ለኢትዮጵያ ህዝቧ ነው ያላት። ህዝቡ ደግሞ አንድ ሆኖ መቆም አለበት። አንድ ሆነን ከቆምን ማንኛውንም የውጭ ሃይል መመከት እንችላለን።

ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የ«በቃ» ወይም «No more» እንቅስቃሴው ነው። ይህ እንቅስቃሴ ሲጀመር የሚሳካ አይመስልም ነበር፤ ግን አለም ሁሉ ፀጥ ነው ያለው፤ ይልቁንም ሃያላኑ ወደ ልመና ነው የገቡት። ይህ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ አልፎ አፍሪካን በሙሉ ነው ያነሳሳባቸው። ዲያስፖራው ለአገሩ «ሆ» ብሎ ሲቆም ማንም ሊከላከለው አልቻለም። ምንም እንኳን የሕወሓት ውሸት ከአገር አልፎ አለምን ያዳረሰ ቢሆንም ዘመቻውን ማስቆም አልቻሉም። እና አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያውያን ሌላ ወገን ይደርስልናል ብለን ማሰብ የለብንም፤ ለኢትዮጵያ ያለነው እኛው ነን። በጎሳ፤ በቋንቋ ተለያይተን ብንበታተን ለሌሎች መብል ነው የምንሆነው። ለሌላው መጠቀሚያ ነው የምንሆነው። ለነግብፅ እፎይታ ነው የምንሆነው። ሱዳንም ብትሆን እኛ ብንበታተን ደስታውን አትችለውም። ይህንን ሁላችንም ጠንቅቀን ልናውቅ ይገባል።

ሁልጊዜ እንደምንናገረው ሁላችንም በጎሳ በማባላቱ በእኛ ይብቃ፤ የሚቀጥለው ትውልድ እፎይ ማለት አለብን። ትምህርት ቤት ሄዶ ሳይፈራ በሰላም መመለስ አለበት፤ እናት ልጆቼ በሰላም ይመለሳሉ ወይ ብላ መጨነቅ የለባትም። እኛ ወደዚህ ስንመጣ እንኳ የምኖርበት መንግስት «ኢትዮጵያ ጦርነት ላይ በመሆንዋ አትሂዱ» ብሎን ነበር። ሆኖም አሻፈረን ብለን ለወገኖቻችን አለኝታ መሆናችንን ለማረጋገጥ ነው የመጣነው። በአጠቃላይ የውጭ አገራት መንግስታት ለእኛ ምንም አያደርጉልንም፤ ስንጠነክር ይወዱናል፤ ስንዳከም ደስታቸው ነው። ስለዚህ እጅ ለእጅ ተያይዘን ልዩነቶቻችንን አስወግደን ለህዝባችንና ለአገራችን መቆም አለብን የሚል ጥሪ ማቅረብ እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ሕወሓት ወንጀለኞች መፈታ ታቸውን ተከትሎ መንግስትና አገር ሲደግፉ የነበሩ አንዳንድ የዲያስፖራ አባላት ቅር ተሰኝተው እንደነበር ይታወሳል። ስለመሆኑ በአገር ማኩረፍ ይቻላል? ሁሉንም ዲያስፖራ እንደ «በቃ» ዘመቻው ሁሉ አሁንም በአገሩ ጉዳይ ላይ እንዲሳተፍ ምን መሰራት አለበት ይላሉ?**

**ዶክተር ትሁት፡-** እንዳልሽው አሸባሪው ሕወሓት እስረኞች ሲፈቱ ትንሽ የማይባለው ዲያስፖራ ቅር ተሰኝቶ ነበር፤ ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ ድንገተኛ ነበር፤ በርካታ ዲያስፖራ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጥሪ ተከትሎ በብዙ ደስታ ነበር የመጣው፤ በድንገት እነዚያ ሰዎች ሲፈቱ በጣም አዝነው ተመልሰው የሄዱም አሉ፤ በዚያ ወቅት በቤተ መንግስት እኛ የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ እየሠራን ነበር። ወደ 800 ሺ ዶላር አካባቢ አሰባስበን ነበር፤ ለአንድ እራት አንድ ሺ ዶላር የከፈሉ ነበሩ። እናም ያ ነገር ሲከሰት እኛ ላይ ራሱ ከፍተኛ ቁጣ ነበር የተነሳብን። የማሰባሰቡን ስራ እንድንሰርዘው ሁሉ ተጠይቀን ነበር። ሆኖም «በአገር አይኮረፍም» እያልን ከፍተኛ የማረጋጋት ስራ በመስራት በሂደት የነበረው ቁጣና ኩርፊያ እየቀነሰ ሄዷል።

ዶክተር አብይም ሰብስበውን ማብራሪያ ሰጥተውን ነበር፤ ብዙውን ነገር ተቀብለነዋል። ያልተቀበልነው ነገር ሊኖር ይችላል፤ እሱ ምንም ማለት ግን አይደለም፤ ከዚያ በኋላ ግን አኩርፈን ህዝባችንን አለመደገፍ ትክክለኛ መንገድ ነው ብዬ አላምንም። በእርግጥ ስራችን ቢዳከምብንም እኛ የምንችለውን ያክል እየሰራን ህዝቡንም እየቀሰቀስን ነው ያለነው። አሁን ህዝቡ ህዝባችን ነው። የብዙ ሰው ልብ ያለው እዚህ ነው፤ ዲያስፖራ ማለት ባንዲራ አቅፎ ቁጭ ብሎ የሚያለቅስ ህዝብ ነው። እውነቴን ነው የምልሽ እኔ ራሴ እንዲህ አይነት የአገር ፍቅር እንዳለኝ እዚህ ሆኜ አይገባኝም ነበር። ስትወጪ ነው የባሰ የምትኳጊው፤ እናም ብዙ ዲያስፖራ ህዝቡን አገሩን ይወዳል። አንዳንድ ጊዜ ግን ከራሳችን ነገር መውጣት መቻል አለብን። መንግስትም ቢሆን በህዝብ የተመረጠ ነው፤ ይሄ መንግስት ደግሞ በደንብ አላገለገለንም ሲል ህዝቡ ራሱ ያወርደዋል። ስለዚህ ይህንን ህዝብ በሆነ ባልሆነ ምክንያት ከምንርቀውና ከምንበታትነው ተስፋ ልንሆነው ነው የሚገባው። ይሄ ጊዜ እንደሚያልፍ ተረድተን አብረን እንሁንና ህዝቡን እናበርታው።

በመንግስትም ሆነ በሚዲያ በኩል ትክክለኛው መረጃ ውጭ ላለው ማህበረሰብ የማድረስ ችግር አለ። ችግሮች ሲፈጠሩ ቶሎ ምክንያቱን በማስረዳት ግርታንና ቅሬታን ማስወገድ መቻል አለባችሁ። ይህንን ስታሳውቁ የተቆጣው ህዝብ ምልስ ይላል። ዝም ሲባል ግን ቁጣው እየባሰ ነው የሚሄደው። ያም ቢሆን ግን መፅሓፍ ቅዱስ እንደሚለው «ነብር ዥንጉርጉርነቱን እንደማይቀይር ሁሉ ኢትዮጵያዊም ኢትዮጵያዊነቱን አይቀይርም።» የትም ብንሄድ ለአገራችን ያለን ፍቅር አይቀየርም። አሁንም አብረን እንቆማለን እንጂ ወደኋላ አንመለስም።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥዎት?**

**ዶክተር ትሁት፡-** በዚህ ጦርነት ምክንያት ከየቀየው የተፈናቀለው ህዝብ ጉዳይ ያሳስበኛል። ለዚህ ህዝብ ከምንም በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል የሚል እምነት ነው ያለኝ። አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ጥሩ ነገሮች መሰራታቸው ደስ ይላል፤ ግን እዛ ጋር መሬት ላይ የፈሰሰ ህዝብ ስመለከት ደስታዬ ግማሽ ይሆንብኛል። መንግስት፤ የሁሉም ክልል መሪዎችና ህዝብ ተባብሮ እነዚህን ዜጎች ህይወት መታደግ አለበት። ወደተረጋጋ ኑሮ የሚመለስበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል፤ ለዚህ ደግሞ እናንተ የመገናኛ ብዙሃን አካላት ሃላፊነታችሁን ልትወጡ ይገባል። በዚህ ዓመት ማንም እናት ስታለቅስ፤ ማንም ልጅ ሲሳቀቅ ማየት የለብንም። የእኛም ጉጉት አገራችን ሰላም ሆና፤ ህዝባችን እፎይ ብሎ ማየት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ ሳመሰግን እወዳለሁ።**

**ዶክተር ትሁት፡-** እኔም እድሉን ስለሰጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።




ማህበራዊ

# ማህደረ ጤና

# ኦቲዝም

እፀገነት አክሊሉ



ኦቲዝም የሚለው ቃል የግሪክ ሲሆን ፍቺውም "ብቸኛ" የሚል ነው። ምክንያቱ ደግሞ በኦቲዝም የተያዙ ልጆች ከልጆች ጋር የማይቀላቀሉ የሚረዳቸው ሰው ካላገኙ በቀር ማንም ሊረዳቸው ስለማይችል ብቸኛ ይሆናሉ፡፡ ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች ኦቲስቲክ ይባላሉ፡፡ እነዚህ ልጆች የራሳቸው ዓለም ያላቸው ስለሆኑ የሚረዳቸው ሰው ይፈልጋሉ፡፡ የማያቋርጥ ክትትል ይጠይቃሉ፡፡

በአገራችን በጣም ብዙው ህዝብ ስለ ኦቲዝም ብዙም እውቀት ስለሌለው ብዙዎቹ የዚህ በሽታ ተጠቂዎች ከማህበረሰቡ ይገለላሉ፡፡ አንዳንድ ወላጆች ስለሚያፍሩባቸው ከቤት ስለማያስወጧቸው፤ አንዳንዶቹ ባለ መረዳት መንፈስ ወይም አጋንንት አለባቸው በሚል በማሰር ያሰቃዩአቸዋል፡፡ ኦቲዝም ልክ እንደ ጨጎራ ወይም ኩላሊት ህመም እንጂ በሽታ አይደለም፡፡ የአዕምሮ መዛባት ችግር (Disorder) ነው። ማወቅ ያለብን ነገር ኦቲስቲክ የሆነ ልጅ ማንም ሰው አጭር ወይም ጠይም ሆኖ እንደተፈጠረው ተፈጥሮአዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ማህበረሰብ ያንን መረዳት አለበት፡፡

### ኦቲስቲክ ስለሆኑ ልጆች ምንምን መረዳት አለብን?

ኦቲዝም በሽታ ቢሆንም ኦቲስቲክ ያለባቸውን ልጆች ፍቅር፤ ትዕግስትና ጊዜ ከሰጠናቸው ከሰው ጋር ወደ መግባባት ወደ መሻሻል ይመጣሉ፡፡ ማህበረሰቡ ያንን አውቆ ከታገሰ በየቤታችን፤ በየሰፈራችን በዚህ በሽታ የተያዙ ልጆችን ልንረዳቸውና ልናሽላቸው እንችላለን፡፡ ፍቅር፥ ትዕግሥትና ጊዜ ግን ይፈልጋሉ፡፡

### ኦቲዝምና ዳዎን ሲንድሮን መሐል ያለውን ልዩነት

ሰዎች መረዳት ያለባቸው ነገር ኦቲዝም ክትትል ካገኘ መሻሻልን የሚያመጣ ሲሆን ዳዎን ሲንድሮ ግን የአዕምሮ እድገት ውስንነት ነው፡፡ ይህ ነገር ከ 80 በመቶ በላይ የሚከሰተው ከ40 ዓመት በላይ ከሆናቸው በኋላ እናቶች የተወለዱ ህጻናት ላይ ነው። እነዚህ አይነቶች ብዙም ሳይቆዩ የመሞት እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡

የእንግሊዝና የጣሊያን ተመራማሪዎች በጋራ ባደረጉት ጥናት እንደገለጹት አስቀድሞ የኦቲዝም ተጠቂዎችን ለመለየት የሚያስችል የደምና የሽንት ምርመራ በህጻናት ላይ በማድረግ ለኦቲዝም ህክምና መሥጠት እንደሚቻል ተረጋግጧል፡፡ ህጻናት የኦቲዝም ተጠቂ መሆናቸውን ለማወቅ በደም ውስጥ የሚገኝ የፕሮቲን መጠንን በመለካት ማወቅ እንደሚቻልም ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ የኦቲዝም ተጠቂ የሆኑትንና ያልሆኑትን ህጻናት በማነጻጸር በተደረገው የሽንትና የደም ናሙና ምርመራ በኦቲዝም የተጠቁት ህጻናት ከፍ ያለ የፕሮቲን ጉዳት እንደታየባቸውና በኦቲዝም ያልተጠቁት ደግሞ የተሻለ የፕሮቲን ስብጥር በደማቸው መገኘቱን ገልጸዋል፡፡ ህጻናት በደማቸው አነስተኛ የፕሮቲን ስብጥር በሚኖርበት ጊዜ ለኦቲዝም የመጋለጥ ዕድላቸውን እንዲሰፋ ያደርገዋል፡፡

### ጥናቶች ስለ ኦቲዝም ምን ይላሉ ?

ከዚህ ቀደም በኦቲዝም ላይ የተሠሩት ጥናቶች ህጻናት በኦቲዝም ተጠቂ የሚሆኑት በደማቸው በሚገኘው ፕሮቲን ሲሆን የአሁኑ ጥናት የሚያሳየው ግን በደም ውስጥ የሚገኘው ጉዳት የደረሰበት ፕሮቲን ለኦቲዝም የመጋለጥ ዕድልን እጅግ እንደሚያሰፋ ነው፡ ፡ ኦቲዝም ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነትን በማምጣት በሰው ስነ ባህሪ ላይ ጉዳት በማድረስ በማህበራዊ ህይወት ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል። በዓለም ላይ በሰው ልጅ ላይ ከሚፈጠረው ኦቲዝም በሽታ 30 በመቶ የሚሆነው በዘር የሚተላለፍ እንደሆነ ጥናቶች የሚያረጋግጡ ሲሆን 70 በመቶ የሚሆነው በስነ -ህይወታዊና የአካባቢ ሁኔታዎች ምክንያት የሚከሰት ነው፡፡

### የኦቲዝም የመጀመሪያ ምልክቶች

ኦቲዝም ትልቅ ከረጢት ነው፣ ከቀላል ምልክት እስከ ጥልቅ እና በጣም ከባድ የሆነ የጤና እክል ነው፡፡ በሽታው በአእምሮ ዘገምተኛ ህጻናት እና በደንብ ባደጉ የአካዳሚክ ክህሎት ባላቸው ሰዎች ላይ እንደሚገኝ ኦቲዝምን የሚከታተሉ የህክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ የኦቲዝም ምልክቶች በጣም ቀደም ብለው ይታያሉ፤ ብዙውን ጊዜ ከአስራ ሁለት ወራት በላይ በሆኑ ህጻናት ላይ ይታያሉ፤ እንዲሁም ከ 3 ዓመት በፊት ይታያሉ፤

በተለመደው ቅርጾች, የኦቲዝም ምልክቶች ከ 3 ዓመት በፊት ይታያሉ. በልጅ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ምልክቶች ብዙውን ጊዜ በወላጆች ይታያሉ፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ቀድሞውኑ በጨቅላነታቸው ሕፃኑ በጣም ጨዋ፣ ረጋ ያለ፣ በጩኸት የማይፈነዳ፣ ወደ ዓይኑን ውስጥ በሚገቡ ሰዎች ላይ የማያተኩር፣ እና ሲያነሱት ጠንካራ ነው። በተጨማሪም ህፃኑ በአንድ ነጥብ ላይ ለሰዓታት ይመለከታል፤ ለምሳሌ አይጮኽም ወይም ንግግር አያዳብርም፡፡ በተጨማሪም የልጁ እድገት መጀመሪያ ላይ መደበኛ እና ያልተለመዱ ባህሪያት በድንገት ሊከሰቱ ይችላሉ።

### የኦቲስቲክ ባህሪያት

ኦቲዝም በማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ሁከት ይፈጥራል፡፡ የኦቲዝም ልጆች ብዙውን ጊዜ አይታዩም፣ ለምሳሌ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር የዓይን ንክኪ ወይም በጣም አጭር ጊዜ ነው፡፡እንደ ታመመ ብቻውን ጊዜ ማሳለፍ ይመርጣል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አይታየኝም እና አይሰማኝም የሚል ስሜት ይሰማቸዋል፡፡

የኦቲዝም ልጆችም ግንዛቤ በማጣት ምክንያት ማህበራዊ ህጎችን ለማክበር ይቸገራሉ። ብዙዎቹ ትእዛዞችን አይከተሉም፡፡ በተጨማሪም የጠባይ መታወክ ብዙ ጊዜ ይታያል - ህፃኑ እራሱን በአዲስ እርግጠኛ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ካጋጠመው በተቀነባበረ መልኩ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ መሸሽ ሊፈልግ ይችላል ንዴት ሊይዝ ይችላል አንዳንድ ሀረጎችን ይደግማል ተደጋጋሚ እንቅስቃሴዎችን መድገም፣ መጥራት፣ መነጋገር፣ ወዘተ ሊጀምር ይችላል። የባህሪው ልዩነት በጣም ትልቅ ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ወላጁ አቅመ ቢስ እና ብቃት እንደሌለው ይሰማዋል በውጤቱም፣ ዘመዶቹን እና ጓደኞቹን መጎብኘት ያቆማል፣ እና እስከ ቀኑ መጨረሻ ድረስ ያለ ግርግር በመትረፍ ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ መንገድ ህፃኑ እድገትን የሚወስኑ አንዳንድ ልምዶችን እራሱን ያመጣል በየቀኑ አንድ እና ተመሳሳይ መንገድ በመጓዝ ከተማዋን ለማወቅ መሞከር ነው፡፡

**ሰዎች መረዳት ያለባቸው ነገር ኦቲዝም ክትትል ካገኘ መሻሻልን የሚያመጣ ሲሆን ዳዎን ሲንድሮ ግን የአዕምሮ እድገት ውስንነት ነው**

ኦቲዝም ልጆች ብዙውን ጊዜ በጨዋታዎች ውስጥ ድንገተኛነት ወይም የፈጠራ ችሎታ ማጣት ተለይተው ይታወቃሉ እንቅስቃሴዎችን አያቀርቡም ወይም ጨዋታዎችን አይፈጥሩም፤ ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች ብዙውን ጊዜ በአሻንጉሊት አይጫወቱም፡፡ በክበቦች ውስጥ ይሽከረከራሉ፣ ይወዛወዛሉ፣ መጫወቻዎች ይሰለፋሉ እና መዝናኛቸው ነው፡፡ እንዲሁም በምሳሌያዊ ሁኔታ መጫወት አይችሉም፣

### የኦቲዝም ምርመራ በሁለት ደረጃዎች ይከፈላል

1. **የልጆች እድገት ጥናት**; ስፔሻሊስቱ ህፃኑ ለተወሰነ የህይወት ጊዜ መሰረታዊ ክህሎቶች እንዳሉት ወይም አንዳንድ መዘግየቶች እንዳሉት ለማሳየት ፈተናን ያካሂዳል. በዚህ ምርመራ ወቅት ዶክተሩ ለወላጆቹ ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፤ ለምሳሌ ህፃኑ በደንብ እየተማረ እንደሆነ, እንዴት እንደሚናገር, እንዴት እንደሚሰራ, በደንብ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ይጠይቃል፣

ይህ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም በእነዚህ ቦታዎች ላይ መዘግየት የእድገት ችግሮችን ሊያመለክት ይችላል፤ ወደ ልዩ ባለሙያተኛ የሚላክ እያንዳንዱ ልጅ በ 9፣18 ፣ 24 ወይም 30 ወር እድሜው ውስጥ የእድገት መዘግየት እና የአካል ጉዳተኝነት ምርመራ ይደረግበታል፡፡

በቤተሰቡ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች ኦቲዝም ያለጊዜው መውለድ ወይም ዝቅተኛ የመውለድ ክብደት ስላላቸው አንድ ልጅ ለዕድገት መታወክ ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳለው ሲጠረጠር ተጨማሪ የማጣሪያ ምርመራዎች ይከናወናል በመቆጣጠሪያው ወቅት የማጣሪያ ምርመራዎች ከ 1፣5 ና 2 ዓመት ዕድሜ ላይ ባሉ ልጆች ላይ መደረግ አለበት፡፡

2. **የልጁ አጠቃላይ ግምገማ** - ይህ ሁለተኛው የምርመራ ደረጃ ሲሆን የልጁ ግምገማ የልጁን ባህሪ እና ከወላጆች ጋር ቃለ-መጠይቅ ያካትታል፤ በተጨማሪም የነርቭ እና የጄኔቲክ ምርመራዎች እና ሌሎች የሕክምና ሙከራዎች ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ በተለየ ሁኔታ የልጁ ግምገማ ብዙውን ጊዜ የሚከናወነው የነርቭ ሐኪሞች - የአንጎልንና የነርቮችን ሥራ በመገምገም ነው፡፡

በሌላ በኩልም የሕፃናት እድገት ሐኪሞች የልጁን እድገት የሚገመግሙ ሲሆን የሕፃናት ሳይኮሎጂስቶች ወይም የሥነ-አእምሮ ባለሙያዎች ደግሞ ስለ አእምሮአዊ ጤንነቱ ምርመራ ያደርጋሉ፡፡

### ትኩረት

ልጅዎ በትክክል እያደገ እንዳልሆነ በሚጠራ ጠሩበት ጊዜ ሁሉ ባለሙያን ያነጋግሩ፤ እንዲሁም ለሳይኮሎጂካል ምክክር ቀጠሮ መያዝ ያስፈልጋል። የሕፃናት የሥነ ልቦና ባለሙያዎችን መገኘትም ወቅታዊ ችግሮችን ለመረዳት ያግዛል ፡፡

ኦቲዝምን ስንመረምር፣ ከኦቲዝም ጋር እየተገናኘን እንዳለን፣ የተለመዱ በሽታዎች (የመስማት ወይም የማየት ችግሮች) ወይም ከልማት ዞኖች ውስጥ የአንዱን መታወክ፣ ለምሳሌ ንግግርን መለየት አስፈላጊ ነው። ኦቲዝምን የሚመስሉ አንዳንድ በሽታዎች አሉ, ስለዚህ በተገቢው ምርመራ መወገድ አለበት፡፡ ምርመራ ለማድረግ ልጁን መከታተል እና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር መነጋገር አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። የትምህርት አቅም የሚፈተነው ሁለገብ ቡድን ነው።

### ኦቲዝም - ጠቃሚ ምክሮች ለወላጆች

ልጅዎ የሚከተለው ከሆነ ሐኪምዎን ያማክሩ፤ የንግግር እድገትን መዳከም፤ ከአካባቢው ጋር አለመገናኘት፤ ማህበራዊ ግንኙነቶችን አለማድረግ፤ ሲጠራ መልስ አለመስጠት ካለ በተቻለ ፍጥነት ሕክምናን መጀመር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## «የነገይቱ ወረቀት አልባዋ ኢትዮጵያ¡?»

### የቴክኖሎጂው በረከተ መርገምነት፤

ካሁን ቀደም በዚሁ አንጋፋ ጋዜጣ ላይ ለንባብ ካበቃኋቸው በርካታ ጽሑፎቼ መካከል "ከድምጽ በማይተናነስ ፍጥነት" እየተጣደፈ ስለሚገሰግሰውና እንኳን "ተራ ተጠቃሚ" የሰው ዝርያዎችን ቀርቶ "ራሳቸው የቴክኖሎጂዎቹ ፈላስፎችና ወጣኞች" ሳይቀሩ ከኋላው "ኩስ ኩስ" እያሉ ስለሚከተሉት የዘመኑ ቴክኖሎጂ ባህርያት ደጋግሜ ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ። ዘመኑ የቴክኖሎጂ ስለመሆኑ፣ ከዘመን መኳረፍ ስለማይቻልና ስለማይሞከረም የቴክኖሎጂውን አሰስ ገሰስ ወደንም ይሁን ተገደን ለማጋበስ "አሜን!" ብለን እንደገበርንለትም ማሳያዎችን እያጣቀስኩ ሞግቻለሁ።

የቴክኖሎጂው ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶች ሕይወ ታችንን እንደምን እንዳቀለሉት ጫን ብሎ መዘርዘሩ ግን "ሃሳቡንም ሆነ ሃሳብ አቅራቢውን" ግምት ላይ ስለሚጥል እንዲያው በደፈናው "በረከቱን" ቆጥረን የምንዘልቀው አይደለም፤ ማለቱ ይበጃል። ሁላችንም በቀላል ልንረዳው በምንችለው ማሳያ እናመላክት ከተባለ ግን ሺህ ምንተ ሺህ ጉዳዮችን የምንከውንበት የእጅ ስልካችን (ሞባይል) አገልግሎት ላይ ባልዋለባቸው ዓመታትና ከዚያ በፊት እንዴት እንደኖርን በንጽጽሮሽ ማስተያየቱ በቂ ሊሆን ይችላል። ያውም ሠላሳ ዓመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ።

አይበለውና በሌሊትና በቀን በእጃችን ላይ የምናሽሞነሙናት የእጅ ስልካችን ወይንም ኮምፒው ተሮቻችን አገልግሎታቸው አብቅቶ ይቁሙና ወደ ጥንቱ ሕይወት ተመለሱ ብንባልና ቢፈረድብን ምን እንደምንመልስ ለመተንበይ ያዳግታል። የአብዛኞቻችን መልስ ሊሆን ይችላል ብለን የምንገምተው ግን "የሰይጣን ጆሮ ይደፈን" የሚለው ብርቱ እርግማን ነው።

ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ ከሌጣ እስከ ውስብስብ ጉዳዮችን ለመከወን በምድርና በህዋ ላይ ተልእኮ የተሰጣቸው ዘመን ወለድ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ዓለማችንን ከጠባብ መንደርነት ወደ ጣታችን አንደርድረው አቃርበውልናል። በየዕለቱ "ዓለምና አገራችን እንዴት ሰነበቱ" በማለት አብዛኞቻችን የእጅ ስልካችንን ወይንም ኮምፒውተራችንን በጣታችን ሳንደነቋቁል ከዋልን "ባዶነት ወይንም የውስጥ ርሃብ" እየተሰማን "ሱሱ" ፋታ ስለማይሰጠን ጣታችንን ሰብስበን የማዋል ፈተናውን ለመቋቋም ሳንቸገር የሚቀር አይመስለንም።

የቴክኖሎጂው ጠቀሜታና "በረከት" ከዚህም በላይ ብዙ የሚሰበክለትና የሚዘመርለት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ "በእርግማን" የመሰልናቸው ህፀጾቹም ተነቅሰው ይብራሩ ቢባል ዘርዝሮ ለመጨረስ በእጅጉ ይፈትናል። በአጭሩ ዘመንኛው ቴክኖሎጂ ከግል እስከ ቤተሰብ፣ ከማሕበረሰብ እስከ አገር፣ አልፎም እስከ ዓለም ዳርቻ ሕይወትን ማቅለል ብቻ ሳይሆን ያቀለለውን ሕይወት ለአደጋ አሳልፎ እየሰጠ እንዳለም በብዙ ማሳያዎች ማመላከት ይቻላል።

በዚሁ በቴክኖሎጂ "ትሩፋት" አማካይነት ቤተሰባዊ ሕይወት እየተሸረሸረ በመሄድ ላይ ነው። ማሕበረሰብ በማይረቡ የውሸትና ኢ-ሥነምግባራዊ በሆኑ በኢንፎርሜሽኖችና በገለባ እውቀቶችና ርኩሰቶች ወጀብ እየተላጋና እየተናጠ አሳሩን በመብላት ላይ ይገኛል። በዚሁ በእኛው ቀዬ በውሸት በተፈበረኩ መረጃዎች ሕዝባችን ቁም ስቅሉን ሲያይ መዋሉ አይጠፋንም። በተለይም አገርና ትውልዱ "ከወረቀት ፀጋ" እየራቀ፣ በቴክኖሎጂው ግኝቶች አውሎ ነፋስ እየተላጋ መንሳፈፍን ስለመረጠ በአኗኗራችንና በጋራ ጉዳዮቻችን ሁሉ ለወረቀት አገልግሎት ጥዩፍ ሆነን ቴክኖሎጂውን የሙጥኝ ወደማለቱ ተበረታተናል።

### በቡሃ ላይ ቆረቆር፤

የዘርፉ ባለሙያዎች ጥናት እንደሚጠቁመው በተለይም አብዛኛው የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ እውቀትንና ጥበብን ሲቀዳ የኖረው ከመጻሕፍት ይልቅ በቃል ሲወራረዱ ከመጡ ምንጮች ነው። "ፊርማና ወረቀት ጠፊ ነው ተቀዳጅ፤ መተማመን ብቻ ይበቃል ለወዳጅ" እየተባባልን መኖራችንን ብናስታውስ ሃሳባችንን ይበልጥ ግልጽ ያደርግልናል። ስለዚህም ከሥነ ጽሐፍ ሀብት ይልቅ "የሥነ ቃል" እሴቶቻችን ይበልጥ ዋጋ ነበራቸው ማለቱ ያስማማ ይመስለናል።

በአግባቡና በሚፈለገው ደረጃ ሕዝባችን የንባብ ባህሉ ተጠናክሮ ወላጆችም ሆንን ልጆቻችን አፐታይታችን አድጎ "የወረቀት ፍቅራችን ሳይበረታ" በፊት ቴክኖሎጂው እንደ ማዕበል ከተፍ ስላለብን "ልጓሙን ይዘን" ልንገራው አልቻልንም። የሽምጥ ግልቢያው ከእኛ ሩጫ ስለፈጠነም እነሆ ዛሬ የደረስንበት ግልብ አጠቃቀም ላይ ለመድረስ ግድ ብሎናል።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዘመናዊ እናቶች ሕጻናት ልጆቻቸውን ቀድመው ከማቀፍ ይልቅ ሞባይላቸውን ፈጥነው በማንሳት "እሹሩሩ" ማለትን ሲቀናቸው እያስተዋልን ነው። ጎልማሶችና አረጋውያን አበውና እመውም ሳይቀሩ "የእጅ ስልካቸው" ከአጠገባቸው እንዳይርቅ የሚከታተሉት በዐይነ ቁራኛ እስከመሆን ተደርሷል። የወጣቶቻችን የቴክኖሎጂ ፍቅርና ቁርኝትማ ጦዞ የከረረ ስለመሆኑ ማናችንም የምንመሰክረው ነው።

የኅትመት ውጤቶች የንባብ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ አሽቆልቁሎ "ተረት" ወደ መሆን ደረጃ ላይ እንዳይደርስ ስጋቱ በርትቶብናል። የየቤቶቻችን ታዳጊዎችና ወጣቶች "አንብቡ፣ የመጻሕፍት ፍቅር ይደርባችሁ" ብሎ መምከርም የሚያስደስት ሳይሆን "ከወላጆች ጋር የሚያቃቅር ምክር" እስከ መሆን ደርሷል። ገና የንባብ ጉልበታችን ሳይበረታና ከወረቀት ጋር ያለን ቁርኝት ከዳዴ እንፉቅቅ ሳይላቀቅ ዘመን አመጣሹ ቴክኖሎጂ እያባበለ "እጅ ወደ ላይ" በማለት ማርኮ አስገብሮናል። ስለዚህም ነው "በቡሃ ላይ ቆረቆር" የሚለውን ብሂል ለመጠቀም የተገደድነው።

### ጥናቱን ይስጥሽ አገሬ፤

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ "አሰራራችንን ሙሉ በሙሉ ወረቀት አልባ እናደርጋለን" የሚል መፈክር በብዙ መንግሥታዊና የግል ተቋማት ሲነገር እያደመጥን ነው። ይህንን "አዋጅ" ቀድሞ በማስተጋባት "እዩልኝ! ስሙልኝ!" በማለት ይፋ ያደረገው የአገራችን ኩራት የሆነው አየር መንገዳችን መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ይሆናል። አየር መንገዳችን "ከወረቀት ጋር ተፋትቻለሁ" የሚለውን የጸና አቋሙን ያስተዋወቀው እ.ኤ.አ በ2017 ዓ.ም ነበር። ይህንን አቋሙን በወቅቱ የገለጸበት መንገድ ባያቀያይመንም አስኮርፎን እንደነበር እውነቱን ባንናገር ህሊናችን ይወቅሰናል።

የሚሆንለት ከሆነ "አየር መንገዳችን አሠራሩን ሙሉ በሙሉ ወረቀት አልባ ማድረግ" መብቱም ፈቃዱም መሆኑን አንክድም። በፍጥነት ከሚዘምነው ዓለም ጋር መጎዳኘቱ ግድ ስላለው እንደሆነም አይጠፋንም። ነገር ግን "ወደ ወረቀት አልባ አገልግሎት" መግባቱን በወቅቱ ይፋ ያደረገው የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች አንድ ላይ ተሰብስበው "የወረቀት ክምር በእሳት እያቀጣጠሉ" በማጨብጨብ ጭምር ነበር። "አገሬ ሆይ! ጥናቱን ይስጥሽ!" ብለን ለመቆዘም ምክንያት የሆነን ይሄው ድርጊት ነበር።

ይህንን "ተቀባይነት የሌለው ድርጊት" እንደ ዘርፉ ባለሙያ በቁዘማ ብቻ ማለፉን ስላልወደድን በወቅቱ ሰፊ ሽፋን በነበረው አንድ አገራዊ ጋዜጣ ላይ ስህተት መሆኑን ደፈር ብለን ለሕዝብ አሳውቀናል። ቴክኖሎጂው ለማክበር ሲባልም "ወረቀትን የኃጢያት ማስተሰረያ" ማድረጉ ተገቢነት እንደሌለውም በየሚዲያው ሳንታክት አውግዘን ጮኸናል። አገልግሎታቸውን ሲጨርሱ ለጅብ እንደሚወረወሩት የቢሾፍቱ ፈረሶች "ወረቀትን በእሳት እያቃጠሉ" ቴክኖሎጂን ማሞገስ ምን የሚሉት አመለካከት እንደሆነ ሊገባን አልቻለም ነበር፤ ፈጻሚዎቹ ራሳቸውም ገብቷቸው ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያዳግታል።

"ምንትስ በቀደደው አጥር ምንትስ ይገባል" እንዲል ብሂላችን፤ አየር መንገዳችን በቀደደው መንገድ ብዙ መንግሥታዊ ተቋማት እየተቀባበሉ ወደ "ወረቀት አልባ አገልግሎት" ገብተናል ማለትን ፋሽን አድርገውታል። እ.ኤ.አ በ2020 መስከረም ወር ላይ "ወረቀት አልባ የጉምሩክ አገልግሎት ተጀመረ" ብሎ የተከተለው የገቢዎች ሚኒስቴር መ/ቤት ነበር። "ይህንን የመሰሉ ዝመናዎች በየዘርፉ ተጠናክሮ ይቀጥላል" የሚለው መንግሥታዊ ውሳኔ የተሰማውም "የወረቀት ነባር አገልግሎት ፊት በተነሳበት" በዚያው ዕለት ነበር።

"የመረጃ አስተዳደርና ልውውጥ ሥርዓት በቴክኖሎጂ በመታገዝ ለማዘመን፤ በጉምሩክ ሥርዓት ሂደት ተጠያቂነት እና ግልጸኝነትን በመፍጠር የሰነድ ማጭበርበርን በማስቀረት ፍትሐዊ የንግድ ሥርዓት እንዲሰፍን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ" መታመኑን አንቃወምም። እርግጥ ነው፤ ከዘመን ጋር መዘመን ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር መሆኑ አይጠፋንም። የቴክኖሎጂ ፀር እንደሆነንም መታሰብ አይገባውም።

"አሰራራችንን በቴክኖሎጂ እናዘምናለን" ማለት እየተቻለ "ወረቀትን ማውገዝ" ምን ይባላል? ምንስ ረብ ይኖረዋል? ምኞቱን ይሁን ብለን በአሜኔታ ብንቀበል እንኳን በርግጡ ወረቀትን ሙሉ ለሙሉ ከአገልግሎት ውጭ ለማድረግ ተቋማቱ ተሳክቶላቸው ግባቸውን መትተዋል? አየር መንገዳችንም ሆነ የጉምሩክ ተቋም "ምኞታቸው ግቡን መትቶ" የወረቀት አገልግሎት አሰጣጣቸው ተጠራርጎ ጠፍቶ ከሆነ ቆመን እናጨበጭብላቸዋለን። እንደ ባህል የለመድነውን የኃይል መቆራረጥ ተቋቁመው በአሸናፊነት ተወጥተው ከሆነም በእልልታ እናደንቃቸዋለን።

የእነዚህ ሁለት ተቋማት "የወረቀት አልባ አገልግሎት" ምኞት ገና መሬት መርገጡ ሳይረጋገጥ የተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተከበሩ አፈ ጉባዔው አማካይነት "የምክር ቤቱ ሥራዎች ወረቀት አልባ እንዲሆኑ" መወሰኑን የሰማነው ከቀናት በፊት ነው። ሙግታችንን ደግምን ጠንከር በማድረግ እንጫነውና "ተቋማቸውን በቴክኖሎጂ ማዘመናቸውን" ብቻ መገለጽ እየቻሉ ስለምን በወረቀት ላይ ይፈርዳሉ? የፈለገ ሥልጣኔ ማማ ላይ ደረስኩ እንኳን አሰኝቶ ቢያስፎክር የሰው ልጅ ከወረቀት አገልግሎት "ሙሉ ለሙሉ" አርነት ወጥቶ የቴክኖሎጂው ምርኮኛ መሆን ይቻለዋልን?

ያውም በኢትዮጵያ ዐውድ ገና ከወረቀትና ከንባብ ጋር ተያይዞ ብዙ መሥራት በሚገባው አገር "የወረቀትን ጥንብ እርኩስ" ማውጣት ተገቢ ነው የሚል እምነት ላይ እንዴት ሊደረስ ቻለ? ይህንን መሰል አገራዊ ውሳኔ የሚሰሙ ልጆቻችን ነገ ጠዋት "መጽሐፍ አንብቡ! ጻፉ!" እያልን ስንመክራቸው ምን ሊመልሱ ይችላሉ። "እናንተ ወረቀት አልባ አገልግሎት ለመስጠት እየፎከራችሁ እኛን ለምን ወደ ወረቀት ትገፉናላችሁ?" በማለት አይታዘቡንም፤ በእምቢታቸውስ አያሳፍሩንም? እንዲህ ዓይቱን መግለጫ የሚሰጡን የሕዝብ አገልጋዮችስ ነገ ጠዋት "ሕዝቤ ከንባብ ተፋታ፣ ለኅትመት ውጤቶች ባዕድ ሆነ" ብለው ሮሮ ቢያሰሙ ማን "አባ ከና" ብሎ ያደምጣቸዋል?

ይህ ጸሐፊ የዛሬ 20 ዓመታት ግድም አሜሪካን አገር በትምህርት ላይ በነበረበት ወቅት ልክ እንደ ዛሬው እንደኛ ከአምስት ዓመታት በኋላ በመላው የአሜሪካ ግዛቶች ሙሉ ለሙሉ ወደ "ወረቀት አልባ አገልግሎት" እንደሚገቡ ፎክረውና አስፎክረው ነበር። እንኳን ከአምስት ዓመት በኋላ ቀርቶ ዛሬም ድረስ ከወረቀት ጋር ፍቺ መፈጸም አልቻሉም። አልፎም ተርፎ የቴክኖሎጂው ጥፋት አገራዊ እንግልቱን ስላበረታባቸው "back to paper!" ወደሚል እንቅስቃሴ ለመግባት ሙከራ መደረጉን ጸሐፊው ያስታውሳል።

ይህ ጸሐፊ በፍጹም ከቴክኖሎጂ ጋር ጠብ እንደሌለው አስረግጦ መናገር ይፈልጋል። የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ መልዕክት "ላይሆንልን ብቻ ሳይሆን፤ ቢሆንልን እንኳን የወረቀትን አገልግሎት አናንኳስስ" ካስፈለገ ቴክኖሎጂውን ደመቅ አድርጎ ማሞገሱ ባይከፋም የወረቀትን ዕድሜ ጠገብ አገልግሎትን በፍጹም ልንዘነጋ አይገባም። ትውልዳችን "እንኳንም ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ" እንዲሉ የወረቀትን አገልግሎት እንኳንስ አካኪሴን ቀርቶ "ከኅትመት መጻሕፍት ጋር ተቆራኙ!" እያልን እየወተወትንም ሰሚ እየጠፋ ስለሆነ ጉዳዩ በጥልቅ ይፈተሽ ለማለት ነው።

ወረቀት ከሰው ልጅ ጋር ያለው የወዳጅነት ቁርኝት ጠንካራ መሆኑ ብቻም ሳይሆን የተሸከመው ፋይዳም በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ወረቀትን ከአመራረቱ የጎንዮሽ ጉዳት ጋር እያስተያዩ ወይንም የባዮ ዳይቨርሲቲን መሳሳት እንደ ምክንያት እየቆጠሩ፣ አለያም የካርቦን ዳዮክሳይድን ልቀት ሰበብ እያደረጉ "ወረቀትን ከደን ጭፍጨፋ ጋር በማስተያየት" የወረቀት አገልግሎትን ዐይንህ ላፈር ማለት ተገቢ አይደለም፤ ተመስጋኝም አያደርግም። በቴክኖሎጂ መዘመን ግድ ነው? - አዎን ግድ ነው። የወረቀት አገልግሎትስ መቀጠል አለበት? - አዎን ሊቀጥል ይገባል። እናስ በየተቋማቱ አመለካከታችንን እንዴት እናስተካክል ከተባለ "ወረቀትን በክብሩ፤ ቴክኖሎጂንም በመስመሩ እያሞገሱ" አገልግሎትን መፈጸም ይቻላል። ጉዳዩ "በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ!" እንዳይሆንም አገሬ ልትጠነቀቅ ይገባል። ሰላም ይሁን!

ፖለቲካና ወቅታዊ

## ተናጋሪው ዶሴ

# «ከቤት ውጣ» መባል ያስከተለው ፍፃሜ

አስመረት ብስራት



በሕይወት ጉዞ ውስጥ መውለድ መክበድ፤ ዘር መተካት ያለና ወደፊትም የሚኖር ጉዳይ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ አይነት ቤተሰባዊ ትስስሩ የጠበቀበት አገር ማግባትና መውለድ የሕይወት አንዱ ግብ እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ወጣቶችን ፕሮግራማቸው ባይሆን እንኳን ‹አግቡ አግቡ› የሚለው ጉትጎታ የሚበዛው። የኢትዮጵያውያን ሰርግ በብዙ አጃቢዎች ደምቆ ወደ ሶስት ጉልቻ የሚሸኘው። ጋብቻ በተፈፀመ በዓመቱ ደግሞ ውለዱ እንጂ የሚለው አስተያየት ይከተላል። አንድ ከተወለደ በኋላ ደግሞ ‹ምነው ብቻውን ወይም ብቻዋን አስቀራችሁ ድገሙ ድገሙ እንጂ ልጅ ፀጋ ነው› የሚሉ አስተያየቶች ከዚህም ከዚያም ይወረወራሉ።

በገጠር አካባቢ ደግሞ ‹ልጅ በልጅነት› በሚል ልማድ ገና በአስራዎቹ አጋማሽ ጎጆ ቀልሰው የልጆች እናትና አባት መሆን የሕይወትን መንገድ በአፍላነት መቀላቀል የተለመደ ነው። የዛሬ ባለታሪካችን አፍላነታቸውን በእናትነት ያሳለፉ በልጆቻቸው የተካሱና ድካማቸውን የረሱ አይነት እናት ናቸው። ማረፊዬ ጧሪዬ ባሉት የልጅ ልጃቸው ያላሰቡት ነገር ቢከሰትም ሕይወት ዘመናቸውን በሙሉ በደስታ ያሳለፉ እናት ነበሩ።

ወይዘሮ ልክየለሽ እንግዳ ይባላሉ። ደርበብ ቀላ ሞንደል ያሉ ወይዘሮ ናቸው። ወይዘሮዋ በልጅነታቸው ተድርው አምስት ልጆችን አፍርተዋል። ተወልደው ካደጉባት ብሎም ለወግ ማእረግ ከበቁባት የወሎዋ አማራ ሳይንት በ1977 ዓ.ም ድርቅ የተነሳ ከቤታቸው ወጥተዋል። ከትውልድ ቀያቸው ርቀው አዲስ አበባን ከረገጡባት ቀን አንስቶ ከባለቤታቸው ጋር በመተጋገዝ ሀብት ንብረት አፍርተዋል። ልጆቻቸውን አስተምረው ለወግ ማዕረግ አብቅተዋል። በመከባበርና በመተጋገዝ ያሳለፉትን የትዳር ዘመናቸውን ሲያስታውሱ በደስታና በስስት እንባቸው አይናቸው ላይ ይሞላል። ልጅን በስነ ምግባር ማሳደግ የሚያውቁት ባለቤታቸው ጨዋና በኑሮ የተሳካላቸውን ልጆች ማሳደግ ችለዋል።

በመኖር ሂደት ውስጥ ሞት አይቀሬ ነውና የሚወዷቸውን የልጅነት ባላቸው በሞት ተለዩዋቸው። በጊዜ ልጆቻቸውን ድረው ኩለው ከባለቤታቸው ጋር ብቻ ቀርተው የነበሩት እናት፤ ሀዘኑና ብቸኝነቱ በጣም ጎዳቸው። ያኔ ቤቱ ጭር ሲል ብቸኝነት አፍ አውጥቶ ሊውጣቸው ሲነሳ ከልጆቻቸው ተማክረው አንድ ነገር ይወስናሉ። የመጀመሪያ ልጃቸው ቴዎድሮስ ጫኔ የመጀመሪያ ልጅ የሆነውን ህፃን ሮቤል ቴዎድሮስን ወስደው ለማሳደግ ወሰኑ። ቤታቸውን ከብቸኝነት ድባብ አውጥቶ ዳግም ነፍስ እንዲዘራ ያደረጋቸውን ልጅ ከልባቸው ወደዱት። ልጁም ከአያቱ ጋር በእንክብካቤ ማደግ ጀመረ።

### ቅምጥሉ የአያት ልጅ

ከወለዷቸው ልጆቻቸው በላይ የሚንሰፈሰፉለት ህፃን ሮቤል በአያቱ እጅ ቅብጥ ብሎ አደገ። ትምህርት ቤት ሲወስዱትና ሲመልሱት አዝለውት ነበር። ምንም እንኳን ቢከብዳቸውም የፍቅራቸው ማየል ያንን እንዲያደርጉ ያስገድዳቸው ነበር። አቅሙ ሲጠነክርና እግር ሲያወጣ በላ አለበላ ተጨንቀው፤ የእንቅልፉ መብዛቱ እሳቸውን እንቅልፍ ነስቷቸው፤ ወጥቶ እስኪገባ ልባቸው ደጅ ውሎ ደጅ እያመሸ ለቁም ነገር ይበቃላቸው ዘንድ ተመኙ።

ምኞታቸውንም ለማሳካት ለልጅ ልጃቸው አለ የተባለውን ጥሩ ነገር በሙሉ አደረጉለት። ከፍተኛ ክፍያ የሚከፈልበት ትምህርት ቤት አስተማሩት፤ ውድ የተባለውን ልብስና ጫማ መግዛት ብቻ በአጠቃላይ አንድም ነገር ሳይጎድልበት እንዲማር አደረጉ። ይህ ሁሉ ቢሆንም የልባቸው መሻት ሳይሆን ቀረ።

እርሳቸው ሮቤል ተምሮ ከልጆቻቸው በላይ የሚጦራቸው የአይናቸው ማረፊያ እንዲሆናቸው ቢመኙትም በትምህርቱ ከአስረኛ ክፍል በላይ መቀጠል አልቻለም። ይባስ ብሎ በሱስ ውስጥ ተነከረ። የጫት፤ የመጠጥና የሲጋራ ሱሰኛ ሆነ። ሲወጣ ሲገባ አያቱን ሳንቲም አምጡ በማለት ያስቸግራቸው ያዘ። የለኝም ያሉት ቀንም መቀነታቸውን ሲፈታና ቦርሳቸውንም ሲፈትሽ መገኘቱ የተለመደ ተግባር እየሆነ መጣ።

ወጣቱ የተከፈለለትን ዋጋ ያህል ውጤት ሳያመጣ ከመቅረት አልፎ፤ ባልታሰበ አቅጣጫ ሄዶ አግድም አደገ ተባለ። ምግባረ ብልሹ ከሚባሉት ወጣቶች አንዱ የሆነው ይህ ወጣት ከአያቱ ቁጥጥር ውጭ ሆነ፡፡ የመጀመሪያ ልጃቸው ቴዎድሮስ፤ የሮቤል አባት የልጅ ልጃቸውን እንዲወስድላቸው ተማፀኑ።

### ስልጁ ባእድ የሆነው አባት

ወትሮም ልጁ ተነጥሎት እንዲያድግ ያልፈለገው አባት እናቱን ላለማስቀየም የመጀመሪያ ልጁን መስጠቱ ሁሌም ይቆጨው ነበር። የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ ነገር ሆኖበት የበኩር ልጁ እንደ አይን ሲጠፋበት ዝም ብሎ ከመመልከት ውጭ የሚያደርገው ነገር አጣ። ከስር ከስር ተከታትሎ መንገድ ያላሳየው ልጅ እንዴት ሆኖ ሊገራው እንደሚችል ሲያስብ ግራ ገብቶታል።

እናቱም ማንም ስለልጄ አያገባውም በማለት አሞላቀው ቅጣትን ሳያውቅ፤ የለም አይቻልምን ሳይለምድ ያሳደጉትን የልጅ ልጃቸውን ከመስመር ሲወጣ አባቱ እንዲወስድላቸው መጠየቃቸው ቢያሳዝነውም የወለደ አይጥልም ሆኖበት ልጁን ወደ ቤቱ ወስዶ ከተቀሩት ልጆቹ ጋር እንዲኖር ለማድረግ ሞከረ።

ወጣት ሮቤል ግን ስርአት አልበኝነቱ በስርአት የሚተዳደረው ቤተሰብ ውስጥ እንዲኖር አላስቻለውም። ወላጅ እናቱም ሆኑ እህት ወንድሞቹ ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲገባ ለሳምንታት ከታገሉ በኋላ በገዛ ፈቃዱ ከአባቱ ቤት ወጥቶ አያቱ ጋር ተመለሰ።

### ጭቅጭቅ ነገሰ

ለሁለት ሳምንታት አረፍ ያለው የአያቱ ቤት ዳግም በሮቤል መምጣት መበጥበጥ ጀመረ። ሲወጣ ሲገባ አያቱን መገላመጥ ብሎም ያልተገባ ቃላትን መሰንዘር ጀመረ። አልፎ ተርፎ “ከዚህ ቤት ውጣ ካልሽኝ አጠፋሻለሁ” በማለት ዛተ ማስፈራራትን ያዘ።

ወይዘሮ ልክየለሽ በእጃቸው ያደገ ልጅ የከፋ ነገር ያደርስብኛል ብለው ባያስቡም እሳቸውን በድፍረት መናገሩ ራሱ አንጀታቸውን ያቆስለው ጀመር። የጎሪጥ የሚተያዩት አያትና የልጅ ልጅ ግንኙነታቸው ከቀን ወደ ቀን እየተበላሸ የነበራቸው ፍቅር ጠፍቶ በጠላትነት ይተያዩ ጀመር።

የሰባ ዘጠኝ ዓመት የእድሜ ባለፀጋ የሆኑት ወይዘሮ ብቸኝነታቸውን ያስረሳቸው ዘንድ ያሳደጉት የልጅ ልጃቸው ቤታቸውን ሲኦል ሲያደርገው ከማዘን በቀር ምንም ማድረግ አልቻሉም ነበር። ልጃቸው ቴዎድሮስም “አግድም አደግ አድርገሽ ያሳደገሽውን ልጅ እንዴት ላቃናው?” በማለት ችላ ብሏቸዋል። ምንም ቢሆን ግን ባህሪው የሆነ ቀን ሊቀየር ይችላል ከማለት በስተቀር አያቱ ላይ ክፉ ነገር ያደርጋል ብሎ ያሰበ አንድም የቤተሰቡ አባል አልነበረም።

### ክፉ ቀን

ነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም ወጣት ሮቤል ቴዎድሮስ አያቱ መኝታ ቤት በመግባት ከቤት ኪራይ ያገኙትን ገንዘብ ይዞ ወጣ። ከጓደኞቹ ጋር ሲዝናናበት አምሽቶ እኩለ ሌሊት ላይ ወደ ቤት ተመለሰ። ጤፍ እገዛበታለሁ ብለው ያስቀመጡትን ብር ከቦታው ያጡት ወይዘሮ ልክየለሽ በጣም ተናደው የልጅ ልጃቸውን ሲጠብቁ ይወላሉ። እስከ ውድቅት ድረስ ቢጠብቁትም ባለመመለሱ አዝነው ይተኛሉ። በጠዋት ጥሩ ስራ እንደሰራ ሰው ቁርስ እያለ ሲደነፋ ንዴታቸውን መቆጣጠር ይሳናቸውና ከቤታቸው እንዲወጣ በሃይለ ቃል ይናገሩታል። ያኔ ዙሪያ ገባውን ቃኝቶ ምቹ ሁኔታን ስላላገኘ ቂም ይዞ ከቤት ወጣ።

ከዛ ግን አድብቶ እና አስልቶ ማንም ሰው ይሆናል ብሎ ያልጠበቀው ወንጀል ፈፀመ። የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ልዩ ቦታው ቀጠና 5 ወጣት ማዕከል አካባቢ ነበር፡፡ ተከሳሽ ሮቤል ቴዎድሮስ የ79 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ከአባቱ እናት ጋር ይኖር ነበር። በልጁ ያልተገባ ባህሪ ምክንያት ቤታቸውን ጥሎላቸው እንዲወጣ የተናገሩት ሲሆን "ከቤት ውጣ ብላኛለች" በሚል ምክንያት ከወትሮው በቀነሰ መጠን መጠጥ ቀማምሶ ከምሽቱ 2፡30 ሰዓት ወደ ቤት መጣ።

እንደመጣ አያቱን በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ቁጭ ብለው አገኛቸው። ከጠዋት ጀምሮ ማድረግ ያለበትን ሲያስብ የዋለው ወጣት ወይዘሮ ልክየለሽን በተቀመጡበት ጭንቅላታቸውን በመዶሻ ደጋግሞ በመምታት ሕይወታቸው እንዲያልፍ አደረገ።

በእጃቸው በልቶ በእጃቸው ጠጥቶ ጀርባቸውን ተፈናጦ በአያት እጅ በቅንጦት ያደገው ወጣት የበላበትን ወጪት ሰበረ። ለጥሩ ብለው ያሞላቀቁት ልጅ አጥፊያቸው ሆነ። አድጎ ይጦረኛል ያሉት፤ የማታ ምርኩዜ ብለው የሚጠሩት የልጅ ልጃቸው መጥፊያቸው ይሆናል ብሎ አንድም ቀን ያሰበ ሰው አልነበረም። ግን ያልታሰበው ሆነ። እሱም አልወጣም ካለው ቤት በፖሊስ ተይዞ ወጣ። እርሳቸውም ሰላም ካጡበት ቤታቸው ወደ ዘለዓለም ማረፊያቸው ተሸኙ። ዳግም ላይመለሰ ሁለም ነገር በቅፅበት ተጠናቀቀ፡፡

### የፖሊስ ምርመራ

የወይዘሮ ልክየለሽን የድረሱልኝ ጩኸት ሰምተው የመጡት ተከራዮች ፖሊስ በመጥራት ልጁ በቁጥጥር ስር እንዲውል አደረጉ። ፖሊስም ቀድሞ የነበረውን የልጁና የአያቱን ግንኙነት፤ ወንጀሉ የተፈፀመበት ወቅት የነበረውን ሁኔታ በሚመለከት ከአይን ምስክሮች ቃል ተቀበለ። በመቀጠል ክስ ለመመስረት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የቴክኒክና የታክቲክ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ የምርመራ መዝገቡን ለአቃቤ ህግ ልኮ ክስ እንዲመሰረትበት አደረገ፡፡

### ውሳኔ

አቃቤ ህግ ያቀረበውን ጉዳይ ሲመለከት የቆየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ከባድ ውንብድና እና ግድያ ወንጀል ችሎት መረጃዎችን ሲመረምር ቆይቶ በተከሳሹ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለማሳለፍ በቀነ ቀጠሮ ተገኝቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል ተከሳሹ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ የክስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ዕድል ሰጥቷል፡፡ “ከቤት ውጣ ስትለኝ ተናድጄ ነው” ከማለት በስተቀር ተከሳሹም ወንጀሉ ፈጽሞ አላስተባበለም።

የተከሳሽ ሮቤል ቴዎድሮስን ጉዳይ ሲመለከት የቆየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ከባድ ውንብድና እና ግድያ ወንጀል ችሎት ግለሰቡ በበቀል ሰሜት ተነሳስቶ፤ የአያቱን ነፍስ ለማጥፋት አቅዶና ተዘጋጅቶ ወንጀሉን በመፈፀሙ ጥፋተኛ መሆኑን ተረጋግጧል። ለዚህም ወጣቱ ከጥፋቱ እንዲታረም ሲል በ16 ዓመት ከ6 ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## እምቢታ የማያውቀው ባህላችንና እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት

ይበል ካሳ

ድህነትና የኑሮ ውድነት ዓለማቀፋዊ ችግሮች ቢሆኑም በእኛ አገር እየተስተዋለ የሚገኘው የኑሮ ውድነት ግን በዓይነቱ ለየት ያለ ነው። ከሌሎች አገራት የሚለይበት ዋነኛ መገለጫ ባህሪውም አንዴ ወረድ ሌላ ጊዜ ከፍ የሚል አለመሆኑ ነው። ሁሌም መጨመር እንጂ መቀነስ የሚባል ነገር አያውቅም። ወያኔ አገር ይገዛ በነበረበት ጊዜ በሥራ ምክንያት ወደ አንድ የአገራችን አካባቢ በሄድኩበት አጋጣሚ በተወሰኑ ኪሎ ሜትሮች ርቀት በየመንገድ ዳሩ ተሰቅለው እንዳየኋቸው የማስታወቂያ ሰሌዳ መፈክሮች "ሁሌም በዕድገት ጎዳና" መሆኑ ነው የእኛን አገር የኑሮ ውድነት ከሌላው የሚለየው።

በዚህች አገር በአሁኑ ወቅት ያልጨመረ ነገር የለም። ከምግብ እስከ መድሃኒት፣ ከትንሿ መርፌ እስከ ትልልቆቹ የግንባታ መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች ሁሉም ዋጋቸው ጣሪያ ነክቷል። ምላጭ እንኳን በአቅሟ አምስት ብር ገብታለች። መቶ ሃምሳ ግራም ለማይሞላ ዳቦ ከአምስት እስከ አስራ ሁለት ብር እንደየ ጥራት ደረጃው ይከፈላል። በተዓምር ካልሆነ በስተቀር ከምጣዱ ላይ እንዴት እንደተላቀቀ ለማወቅ የሚያዳግት፣ እፍ ቢሉት አርባ ክንድ የሚበር፣ ህጻን ልጅ የማያጠግብ አንድ እንጀራ ከአስር ብር ካለፈ ሰነባብቷል። እርሱም ጀሶ ወይም ሰጋቱራ ያልተቀላቀለበት ከሆነ ነው። አባቶቻችን በጦር ሜዳ ሳይቀር እንደልብ እየቆረጡ ጣሊያንን ያሸበሩበት ሥጋማ ዋጋው የማይቀመስ ከመሆኑ የተነሳ ለብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን የቅንጦት ምግብ ከሆነ ዓመታት ተቆጠሩ። የታባቱና! ካደጉ አይቀር እንደ እኛ ነው እንጅ ዕድገት¡

እናም በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የኑሮ ውድነቱ እጅጉን እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት ሕዝቡን በከፍተኛ ደረጃ እየፈተነው ይገኛል። በተለይም ደግሞ በዓለም አቀፉ መመዘኛ መሰረት ከ፤ ነጥብ 25 ዶላር በታች በሆነ የቀን ገቢ የሚተዳደረውንና ከድህነት ወለል በታች ሚኖረው ድሃ ሕዝብ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዲገባና የሰቀቀን ኑሮ እንዲመራ አስገድዶታል። በአጠቃላይ ሕዝቡ የኑሮ ውድነቱ ከአቅሙ በላይ ሆኖበታል። ብሶቱንና እሮሮውንም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ እየገለጸ ይገኛል። በተለይም በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ደግሞ የኑሮ ውድነቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ነዋሪዎች ይናገራሉ። ለተለያዩ መገናኛ ብዙኃን አስተያየታቸውን የሰጡ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች "ፍጹም የማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፤ ከአቅማችን በላይ ሆኗል። መብላት እንኳን የማንችልበት ደረጃ እየደረስን ነው፤ ጉዳዩ አሳሳቢ ነው" እያሉ ሲናገሩ መስማት የተለመደ ሆኗል።

አንድ የመዲናዋ ነዋሪ የሆነ ግለሰብ፤ "ከአስር ለሚልቁ ዓመታት በሚኒባስ ታክሲ ሾፌርነት ቤተሰቤን ሳስተዳድር ኖሬያለሁ። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን የኑሮ መወደድ ከአቅሜ በላይ ሆኖ እያንገዳገደኝ ነው" ሲሉ አጫውተውኛል። "በዋጋ ላይ ያለውን ለውጥ ከቀን ወደ ቀን እያየሁት የመጣሁት ጉዳይ ነው፤ በእኔ ህይወት እንኳን ታክሲ ሠርቼ ብሩን ይዤ ብገባም ምንም የሚገዛው ነገር የለም። የልጆች ትምህርት ቤት፣ የእህሉ ውድነት፣ እንዲያውም ተስፋ ወደማስቆረጥ ደረጃ እየደረሰ ያለ ይመስለኛል። የትምህርት መማሪያ ቁሳቁስ፣ የአልባሳት፣ የምግብ ወጪዎች ሲደመሩበት "ናላን የሚያዞር" ሆኗል። በዚህ ላይ የቤት ኪራይ ወጪ ይታከልበታል። ህይወታችንን ለማቆየት እየሰራን ነው እንጅ እየኖርን ነው ብዬ አላወራውም" በማለት ምሬታቸውን የሚገልጹ ጥቂት አይደሉም። ይህ ምሬት የብዙሃኑን አዲስ አበቤ ብሎም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ያለበትን የኑሮ ሁኔታን የሚያመላክት መሆኑንም በገሃድ እያየነው ያለ ሃቅ ነው።

ይህን ለመሰለው መረን የለቀቀ የዋጋ ንረትና በህብረተሰቡ ላይ ለተፈጠረው የከፋ የኑሮ ውድነት በርካታ ምክንያቶች የሚጠቀሱ ቢሆንም ዋነኛው ምክንያት ግን የአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን መሆኑን መንግሥት በጉዳዩ ላይ በሚሰጣቸው መግለጫዎች ሲያስረዳ እናያለን። ከዚህ በተጨማሪ በንግድ ሰንሰለቱ ውስጥ በርካታ ህገ ወጥ ደላሎች መኖራቸውና ምክንያት አልባ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ስግብግብ ነጋዴዎች መበራከታቸው የኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ ዓይነተኛ ምክንያት መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል።

በሕብረተሰቡ ውስጥ "መንግሥት በህገ ወጦች ላይ ተገቢውን እርምጃ እየወሰደ አይደለም" የሚል ከፍተኛ ቅሬታና ወቀሳ ቢኖርም መንግሥት በበኩሉ ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተለ በሕገ ወጦች ላይም የእርምት እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ሲናገር ይደመጣል። የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት መንግሥት መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦችን እንደሚያቀርብና ጥብቅ የፊስካል ፖሊሲ በመከተል ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ እየሠራ መሆኑንም በየጊዜው ሲገልጽ ይሰማል። ሆኖም ችግሩ ተባብሶ ሲቀጥል እንጂ ሲቀንስ አልተመለከትንም።

ታዲያ አገሩን እንደሚወድና የሰው ልጆች ሁሉ መልካም ነገር እንጂ ችግርና ስቃይ ሲደርስባቸው ማየት እንደማይፈልግ አንድ ሰው ጉዳዩን በቅርበት ከመረመርነው ኢኮኖሚያዊ ምክንያቱ እንዳለ ሆኖ ለኑሮ ውድነቱ መባባስ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ የሚገኝ አንድ ሌላ ያልተነቃበት መንስኤ መኖሩን መታዘብ አይቀርም። እንደሚታወቀው በምጣኔ ሃብት ሳይንሱ በመሰረታዊነት የዋጋ ንረት የሚፈጠረው በህብረተሰቡ የፍጆታ ፍላጎትና በአምራቹ የምርት አቅርቦት መካከል አለመመጣጠን ሲኖር ነው። አሁን ላይ በእኛ አገር እየተከሰተ ያለው የዋጋ ንረትና ይህንን ተከትሎ የተፈጠረውን ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ስንመለከተው ግን ከዚህም ያለፈ መሆኑን እንታዘባለን። ምክንያቱም አቅርቦት ቢኖርም ባይኖርም ምርትና አገልግሎቶች የሚሸጡት በውድ ዋጋ ነው። አቅርቦቱ ሙሉ በሆነበት ወቅትም የዋጋ ንረት አለ፤ ሁሌም የኑሮ ውድነት አለ። ለምን ?

ለምን ለሚለው ጥያቄ በግሌ የደረስኩበት ድምዳሜ "በአገሪቱ ውስጥ አምራች፣ ነጋዴ ወይም ሻጭ ሁል ጊዜ ተጠቃሚ፤ ሸማችና ገዥ ደግሞ ሁልጊዜ ተጎጅ ለመሆን የተስማሙበት ያልተጻፈ ህግ አለ" የሚል ነው። ይሕም ለዘመናት በሕዝቡ ልቡና ውስጥ ሰርጾ የኖረ እምቢ ማለትን የማያውቅ፣ ጭቆናን የተላመደ፣ ተገዥነትን የሚያወድስ መጥፎ ባህል መሆኑን በበኩሌ በጥናት ጭምር አረጋግጫለሁ! ይህን ለማለት ያስቻለኝን መሞገቻ አመክንዮ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ እስኪ። ልብ በሉ፤ በእኛ አገር ሻጩ ወይም ነጋዴው በምክንያትም ያለምክንያትም በየጊዜው እንደፈለገ ዋጋ መጨመር ይችላል።

ምክንያቱም የገንዘብ እንጅ የወገን ፍቅር የሌላቸው ስግብግብ ነጋዴዎች የአስር ብሩን ዕቃ በአስራ አምስት ብር ሲሸጡልን ዝም እንላለን፣ ትንሽ ቆይተው ሃያ ብር ሲያደርጉትም ዝም ብለን እንገዛቸዋለን። በዚህ የልብ ልብ የተሰማቸው ሻጮቻችንም ከቀናት ልዩነት በኋላ "መቶ ብር ገብቷል፣ ከገዛህ ግዛ ካልፈለክ ተወው" ማለት ይጀምራሉ። እነርሱ ምን ያድርጉ፣ ዝም ብሎ የሚገዛ(ላ)ቸው ሲያገኙ እንዴት እንደፈለጉ አይሆኑ? ምክንያቱም የፈለገውን ቢያደርግ "እምቢ" የሚለው ገዥ የለማ! ይህ ነው ከጊዜ ወደ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተባባሰ ከመጣው ከአሳሳቢው የኑሮ ውድነት ጀርባ ያለው ያልተነቃበት መንስኤ።

በበኩሌ በኢትዮጵያውነቴ አብዝቼ የምደሰትና የምኮራ ሰው ነኝ። ነገር ግን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነታችን ከመውደድ ባሻገር ያሉብን መጥፎ ልማዶችና ባህሎች ማሻሻልና መቅረፍም እጅጉን አስፈላጊና ለአገራችንና ለራሳችን የበለጠ ጠቃሚ መሆኑንም አጥብቄ አምናለሁ። ኢትዮጵያውያን ካሉብን ድክመቶችና ተሃድሶ ከሚያስፈልጋቸው ባህሎቻችን ውስጥም አንዱና ዋነኛው ይኸው ሰዎች እንደፈለጉ እንዲሆኑብን የመፍቀድ አባዜ ነው። ይህም ከፖለቲካው አልፎ በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ ኑሯችን ውስጥም ስር ሰዶ ከባድ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል።

ስለሆነም በከፊልም ቢሆን ራሱ የፈጠረውንና እያባባሰው የሚገኘውን የኑሮ ውድነት ለማቃለል ሕብረተሰቡ ከዚህ ጭቆና ታጋሽነትና አንባገነን ፈልፋይነት ልማዱ ተላቆ የአስተሳሰብና የባህል ለውጥ ማምጣትና የባህል አብዮት ማካሄድ ችግሩን ለመፍታት ዓይነተኛ መንገድ መሆኑ ይሰማኛል። አለበለዚያ "እሽ ይበልጣል ከሺ" የሚለው አባባል ለእግዜሩ ታዞ ገነት ለመግባት እንጂ ዳቦ ይዞ ቤት ለመግባት አያስችልምና እሽን እንጂ እምቢን የማያውቀው የህዝባችን ባህል ባለበት የሚቀጥል ከሆነ እኛው ራሳችን በምንፈጥራቸው የነጋዴ ፈርኦኖች ከዚህም የባሰ የኑሮ ውድነት መጋፈጣችን የማይቀር ይሆናል።

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ እና ዩክሬን የሰላም ድርድር እንዲያደርጉ ቻይና ጥሪ አቀረበች

ሩሲያ እና ዩክሬን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሰላም ድርድር እንዲያደርጉ የቻይናው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋንግ ዪ ጥሪ አቀረቡ። ሚኒስትሩ እየተካሄደ ባለው 77ኛው የተመድ ጉባኤ ላይ ትኩረቱን በዩክሬን ላይ ባደረገው የፀጥታው ምክር ቤት ስብሰባ ላይ አገራቱ ለሰላም ቅድሚያ እንዲሰጡ ጠይቀዋል።

በዚህ ወቅትም የእያንዳንዱን አገር ሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት መከበር እንዳለበት እና የሁሉም ወገኖች የደህንነት ስጋቶች በትኩረት ሊታይ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

ከግጭት መውጫ ብቸኛው መንገድም ውይይት እና ድርድር ነው ያሉት ሚኒስትሩ፥ ቻይና ችግሩን ለመፍታት የሚረዱ ሁሉንም ጥረቶች ለመደገፍ ዝግጁ መሆኗንም መግለጻቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል፡፡

በዚህ ወር ወደ ዩክሬን ዛፖሮዢያ ኒውክሌር ጣቢያ ልዑክ የላከውን የዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኃይል ኤጀንሲ አወንታዊ ሚና ያወደሱት ሚኒስትሩ፤ የኒውክሌር ተቋማት ደህንነትን በተመለከተ ለሙከራ እና ለስህተት



ምንም ቦታ የለም ብለዋል፡፡ ዩክሬን የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን ጦር ወይም ኔቶን እቀላቀላለሁ ማለቷን ተከትሎ ሩሲያ የጀመረችው "ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ" ስድስት ወራት አልፎታል፡፡

መሬት ላይ ሁለቱ አገራት ጦርነት ቢጀምሩም ከዚህ ጦርነት ጀርባ ግን የተለያዩ ግልጽ እና ስውር አሰላለፎች ይዘዋል፡፡ ጦርነቱ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ የተከሰቱ የዓለም ኢኮኖሚ፣ ዲፕሎማሲ፣ ፖለቲካ እና ሌሎች ለውጦችን በማየት ጦርነቱ በዩክሬን መሬት ላይ ይካሄድ እንጂ የዓለም ጦርነት ነው የሚሉ አስተያየቶች ይደመጣሉ፡፡

ይህ የባለብዙ ወገን ጦርነት ለተጨማሪ ጊዜ የሚቀጥል ከሆነ አይገመቴ ክስተቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ግምቶች እየወጡ ሲሆን ተፋላሚዎች ጦርነቱን በድል ለማጠናቀቅ ይጠቅመናል ያሏቸውን የዲፕሎማሲ እና የጦር መሳሪያ ሽመታው እንደቀጠለ ነው፡፡ ይህ ጦርነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዓለምን እየጎዳ በመሆኑ ጦርነቱ የማይመለከተው አገር እና ተቋም የለም፡፡ ለዚህም ነው ከጦርነቱ እንዲቀጥል የሚፈልጉ አገራት እንዳሉ ሁሉ ሰላም እንዲፈጠር የሚሹ አገራትም ብዙ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ቻይና ሁለቱ አገራት ወደ ሰላም እንዲመጡ እየወተወተች የምትገኘው፡፡

## ኢራን ውስጥ በተቀሰቀሰ ተቃውሞ ቢያንስ 17 ሰዎች ተገደሉ

በኢራን ባለፉት ዓመታት ከታዩት ከፍተኛ ነው በተባለለት የአደባባይ ተቃውሞ ምክንያት ቢያንስ 17 ሰዎች መገደላቸው ተገለጸ። ተቃውሞው የተቀሰቀሰው ሒጃብ አልለበሸም በሚል ፀጥታ ኃይሎች ድብደባ ተፈጽሞባት ለሞት በቅታለች በተባለችው ማህሳ አማኒ ምክንያት ነው። ይህን ከፍተኛ ተቃውሞ ተከትሎ ፕሬዚዳንት ኢብራሂም ራይሲ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እያለች ሕይወቷ ያለፈው ሴት ጉዳይ መመርመር አለበት ብለዋል።

በኒውዮርክ እየተካሄደ ባለው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ንግግር ያደረጉት ፕሬዚዳንቱ በማህሳ አማኒ ህልፈተ ሕይወት ዙሪያ ምዕራባውያን ግብዝነት አሳይተዋል ብለዋል። አማኒ የሥነ ምግባር ደንብ አስከባሪ ፖሊሶች ሂጃብ ባለመልበስ ሕግን ጥሳለች በሚል በቁጥጥር ስር ካዋሏት ከሰዓታት በኋላ ሕይወቷ አልፏል።

ይህን ተከትሎ በተከሰተው ተቃውሞ እና አለመረጋጋት ነው የሰዎች ሕይወት የተቀጠፈው። በሰሜን ምዕራብ በምትገኘው የሳቄዝ ከተማ ነዋሪ የሆነችው ኩርዳዊቷ አማኒ ራሷን ስታ ህክምና በምትከታተልበት የቴህራን ሆስፒታል ከሦስት ቀናት በኋላ ሕይወቷ አልፏል።

ወጣቷ እንዳልተደበደበች ራይሲ በድጋሚ አስታውቀዋል። የኢራን ፖሊስ "ድንገተኛ የልብ ድካም" አጋጥሟታል ነው ያለው። ተቃዋሚዎች ግን ፖሊስ የአማኒን ጭንቅላት በዱላ ከመደብደቡም ባለፈ ከመኪና ጋር አጋጭተዋታል በሚል ሪፖርቱን ውድቅ ያደርጋሉ። ፕሬዚዳንቱ የተቃዋሚዎቹን "ግርግር" ተቀባይነት የለውም ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

በዩናይትድ ኪንግደም እና በአሜሪካ በፖሊስ የተፈጸሙ ግድያዎችን በመጥቀስም የምዕራባውያን አገራትን እኛን ከመክሰሳችሁ በፊት ራሳችሁን ተመልከቱ ብለዋል።

ተቃውሞው ወደ 80 የሚጠጉ ከተሞችና መንደሮች ደርሷል። አንድ ግለሰብ ለቢቢሲ ፐርሺያን እንደተናገረችው ሰፈሯ የጦር ሜዳ መስሏል። የአማኒ አባት የሆኑት አምጃድ ከቢቢሲ ፐርሺያን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ፊቷ እና እግሮቿን ከማየት ውጪ ሙሉ አካሏን በመገነዙ ለማየት በባለሥልጣናት እንዳልተፈቀደላቸው ተናግረዋል።

"እግሮቿ ላይ ቁስሎች ነበሩ" ያሉት አባት ዶክተሮች እንዲመረምሯቸው ቢጠይቁም ምላሽ አለማግኘቱን ተናግሯል። ልጃቸው ቀደም ሲል የነበረ የጤና ችግሮች ነበረባት ሲሉ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ እና የቴህራን የፎረንሲክ ህክምና ዳይሬክተር ያቀረቡትን ውጤትም ውድቅ አድርገዋል።"ውሸታሞች



ናቸው። ባለፉት 22 ዓመታት ውስጥ ከጉንፋን ጋር ከተያያዙ ጥቂት ህመሞች በስተቀር ሆስፒታል ሄዳ አታውቅም" ብለዋል።

ተቃውሞው በፍጥነት በመላ አገሪቱ መስፋፋት ከመጀመሩ በፊት በቴህራን በሚገኙ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ተመሳሳይ ሰልፎች መካሄዳ ቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# እንግዳ ነገር ሲሆን ...!

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

የምናብ ታሪካችን ወደ አንድ ትልቅ መኖሪያ ጊቢ ይወስደናል። የጊቤው ባለቤቶች እና ተከራዮች የፈጠሩት አነስተኛ ቀበሌ። እኒህን በአንድ ጊቤ ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦችን በምናባችን እያሰብን ከመካከላቸው እንገኝ። ከጊቢው ትልቅነት የተነሳ ተከራዮቹ አይደለም እርስ በእርሳቸው በቤቱ ባለቤቶች በሙሉ እንኳን በወል አይተዋወቁም። ከብዛታቸው የተነሳ። ብዙ ተከራይ፤ ብዙ የቤተሰብ አባላት፤ ምናልባት ድሮ ድሮ ቢሆን አንድ ቀበሌ ነዋሪን ያክሉም ይሆናል።

በዚህ ትልቅ ጊቢ ውስጥ አንድ ቀን ማምሻው ላይ አንድ ነገር ሆነ፤ አስደንጋጭ ነገር። ሰው ሁሉ ከአዋቂነት ወደ ልጅነት ተቀያይሮ የሚታይበት ቀን። አንዱ ሰው ሌላውን ሰው የሚያየው የልጅ መልክ ሆኖ የሚታይበት ቀን።

ባልና ሚስት ሲተያዩ ሁለቱም የሚታያቸው በእድሜ የገፋ የትዳር አጋራቸው ሳይሆን የትዳር አጋራቸውን አለባበስ የለበሰ፤ አረማመድ የሚራመድ፤ ተመሳሳይ መልክ ያለው ነገር ግን እድሜው ልጅ የሆነ ሰው። በተከራዮቹም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ። የቤት ኪራዩን ሊከፍል ወደ አከራዮቹ ቤት ጎራ ያለ ሰው አከራዮቹን አጥቶ የሚገጥመው አከራዮችን መሳይ ልጆች የሆነበት ቀን። ብሩን የሚቀበለው ሲያጣ ለልጆች ልክፈል አልክፈል ብሎ ተከራይ ግርታ ውስጥ የሚሆንበት ማምሻ። አከራዩ ደግሞ ተከራዩን የሚመስል ሰው ሲያይ "እንዴት እራሱ መጥቶ ኪራዩን አይከፍለኝም፤ ምኑን ልጅ ነው የላከብኝ" ብሎ የሚጠይቅበት ቅጽበት።

ባል "ቁጭ ሚስቴን የምትመስል ልጅ" ይላል፤ ሚስትም "ቁጭ ባሌን የሚመስል ልጅ" ትላለች፤ ሁሉም እርስ በእርሱ እንደ እዚያ ይተያያል። ተመልካቹ አዋቂ፤ የሚመለከታቸው በሙሉ ልጆች። በግርታ ውስጥ የሚተራመስ ጊቢ፤ በጥያቄ ውስጥ የተሞሉ የጊቢው ነዋሪዎች። መልስ መስጠት የሚችል ሰው የሌለበት የእውር ድንብር ጉዞ። በሬዲዮ የሚነገረው፤ በቲቪ የሚሰራጨው፤ በሞባይል የሚታየው ሁሉም ባለበት ነው። የእይታው ድንግርታ ያለው እርስ በእርስ ባለው መተያየት ውስጥ ነው።

ይህን የመሰለ እንግዳ ነገር ሲሆን ግርታ መፈጠሩ አይቀሬ ነው። ግርታው እንዴት ሊፈታ ይችላል? አንባቢው ራሱን ሊጠይቀው የሚገባ ጥያቄ ነው። ግርታው ሲፈታ ምን ሊሆን ይችላል? ደስታ ወይንስ ሃዘን። ወይንስ እንዲሁ መገረም፤ የስሜት መዘበራረቅ።

የጊቢው አባላት ግርታ ውስጥ ቢሆኑም የግርታውን ምንጭ መረዳት ያልቻሉበት ምክንያት መረዳት ቀላል ነው፤ ምክንያቱም ተመልካቹ ራሱን እንደ አዋቂ የመመልከቱ ምስል አብሮት ያለ መሆኑ ነው። ሁሉም ሰው አዋቂ መሆኑን የራሱን ምስል ያውቀዋል፤ ችግሩ ሌሎችን ሲያይ የሚይበት መንገድ ነው። በሌላው ሰው ዘንድ እንደ ልጅ ቢታይም ራሱን የሚያየው ግን እንደ አዋቂ ነውና ጉዳዩ ለመረዳት አስቸጋሪ ሆነ። በሬዲዮ የሚነገረው፤ በቲቪ የሚሰራጨው፤ በሞባይል የሚታየው ሁሉም ባለበት መሆኑ ግርታውን ለመመርመር እድል የማይሰጥ ሆነ።

"ውይ አባወራውን የሚመስል ልጅ" ስትል እናት አባወራው ደግሞ "አንቺ ምን ሆነሻል ቁርጥ ሚስቴን የምትመስይ" ይላል፤ ሁሉም ሊግባባ አልቻለም። በሁሉም ውስጥ ግን መጠበቅ አለ፤ ልጁን የሚመስለው እውነተኛው ሰው እንዲመጣ መጠበቅ። ጥበቃው እየገፋ ሲሄድ አዲስ ነገር አልገለጥ ማለቱ ነው ችግሩ። አባት ስለ ሚስቱ ሲያስብ "ምናልባት ወደ ጎረቤት ሄዳ ነው ስትመጣ እርሷን የምትመስላውን ልጅ ከየት እንደመጣች ታስተዋውቀኛለች" ብሎ ይጠብቃል፤ ሚስትም እንደእዚያው። ሁሉም እየጠበቀ ሰዓቱ ነጎደ። የታሰበው ለውጥ ግን አልነበረም።

እንዲህ ባለ ጊቢ ውስጥ አንድ ሁኔታውን በአግባቡ የተረዳና የጊቢውን ነዋሪዎች ከግርታ ሊያወጣ የሚችል ሰው ወደ ጊቢው ቢገባ ሊል የሚችለውን መገመት ጥሩ ነው። ይህም ሰው "እይታችሁ ላይ ችግር አለ፤ ሌላ የሚመጣ ሰው የለም ሁላችሁም ችግራችሁ እይታችሁ ላይ ነው" ቢል ሊያምኑት ይችሉ ይሆን? አይመስልም። ቀኑ እየጨመረ ሲመጣ ሊግባቡ አለመቻላቸውን ሲያውቁ የግለሰቡን አስተያየት እያመኑ ይመጡ ይሆናል። የበለጠ የሚያምኑት ከመካከላቸው እይታው የተቀየረለት ሰው ምስክርነት መስጠት ቢችል ነው። ግለሰቡን የሚያዩት በልጅነት ሳይሆን በአዋቂነት ከሆነ። በሂደትም የሁሉም እይታ እየተቀየረ ሲመጣ "ምንድን ነበር የሆነው!" የሚለው የመገረም ጥያቄ የሁሉም ጥያቄ ይሆናል። እዚያው ድረስ ግን አንዱ ሌላውን እንደ ህጻን ወይንም እንደ ልጅ እየተመለከተ በግርታ ውስጥ ይኖራል። ወደ ትክክለኛው እይታ ለመመለስ የሚመጣውን አንድ ሰው እስኪያገኝ ድረስ። ድንግርታው ሳያደናግረው እንደ እብድ እየተቆጠረም ቢሆን ወደ እይታ መቀየር ሌሎችን የሚመራው ሰው። እንግዳ ነገር ሲሆን፤ ...

እንግዳ ነገር በሃዘንም ሆነ በደስታ እንዲሁም በአጠቃላይ ድንግርታ ውስጥ ሊገለጽ ይችላል። ድንግርታውን ለምደነው መደበኛ ሕይወታችን አካል እስካለደርግነው ድረስ በእንግዳ ስሜት ውስጥ እንኖራለን። በህዘን እና ደስታ የእንግዳ ወቅት ማሳያዎች አልፈን ግርታ ሲያጋጥም እንዴት ልንወጣው እንደሚገባ ወደሚያሳስበው ነጥቦች እናምራ።

አንዱ ድንግርታ ወደ ሌላ ድንግርታ፤ አንዱ የስሜት ትርጉም ለሌላው እያቀበለ በስሜት ማእበል ውስጥ እየተላጋ የሰው ልጅ በምድር ላይ እየኖረ አለ። በእውቁ ገጣሚ ኦስካር ዊልድ አባባል መሰረት አንድ ስሜት ፈጽሞውኑ ሊደገም የማይችል ነው፤ ሌላኛው ስሜት ይከተል ይሆናል እንጂ። ጥያቄው በድንግርታ ውስጥ ስንገኝ ወይንም እንግዳ ነገር ሲገጥመን እንዴት ተቀብለን እናስተናግደዋለን ነው፤ የምናተርፍበት ወይንም የምንከስርበት የሚሆንበት አግባብ።

### ሀዘን

አንባቢው በሃዘን ስሜት ውስጥ ይገኝ ይሆን? በምን አይነት ሃዘን? በጥልቅ ወይንስ በመለስተኛ? እንግዳ ነገር ከሚፈጠርባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ሃዘን ነው። ሀዘን ሰዎች ጠብቀውትም ሆነ ሳጠብቁት የሚገጥም ነገር ነው። ሃዘን እንደ ሃዘኑ አጠባበቃችን ክብደቱን ቅለቱ ይወሰናል። ለረጅም ጊዜ በህክምና ሲረዳ የቆየ ሰው ከህክምናው ሁኔታ ተነስቶ ሊገጥመው የሚችለውን የከፋ ነገር ልንገምት እንችላለን። ታማሚው እየደከመ በሄደ ቁጥር አስታማሚው ቤተሰብ ለሃዘን እየተዘጋጀ ሲቆይ የህዘን ስሜቱ እየቀለለ ይሄዳል። እንዲህ በመሰለ መንገድ የሚመጣ ሃዘን እየተጠበቀ ሊመጣ ስለሚችል እምብዛም ድንገተኛ ላይሆን ይችላልና እንግዳ ነገር ላይሆን ይችላል። ከእዚያ በተቃራኒ ግን የሚገጥም የሃዘን አይነት አለ፤ ፍጹም ድንገተኛ የሆነ የሃዘን አይነት ነው። ጠዋት ተሰናብቶን ወደ ስራ የሄደ ሰው መንገድ ላይ የመኪና አደጋ ገጥሞት ሕይወቱን ቢያጣ የሚሰማን ስሜት እጅግ አሳዛኝና እጅግም ድንገተኛ ነው። በሕይወታችን ላይ የሚፈጥረው ግርታ ሊገባን እስካይችል ድረስም ይደርሳል፤ ነገሮች በሙሉ ጨለማ ሆነው የሚታዩበት ድባብ።

እንዲህ አይነት ድንገተኛና ሀዘንን የምንቀበልበት መንገድና ሌሎችን የምንቀበልበት አንድ ሊሆን አይችልም። እንዲህ አይነት ሃዘን ሲገጥመን ምን እናደርጋለን? ምናልባት ዛሬ ላይ ማሰብ አንፈልግም ይሆናል። በተጨባጭ ግን በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚደርስ መሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም። ድንገተኛ ሃዘን የሚፈጥረው እንግዳ ነገር ሕይወታችንን ወደ ምን አቅጣጫ ይወስደው ይሆን? የሚያምኑት ሰው ድንገት እምነት አጉድሎ ሲገኝስ፤ መቀበል አቅቶን የምንወስደው እርምጃ ላይስ ምን እናስባለን? የቅርብ የምናውቃው የትዳር አጋሩን የገደለ ምናልባትም ራሱንም የገደለ ሰው ወደ አእምሮችን ይመጣስ ይሆን? እንግዳ ነገር ሲሆን ሰው ፈጽሞ እገኝበታለሁ ብሎ ባላሰበው መንደር ውስጥ ሊገኝ ይችላል፤ ግርታው መርቶ የሚያደርሰው ቦታ። በሃዘን ስሜት የሚገለጽ እንግዳ ነገር ደግሞ ከሌላው የተለየ ነው። ከባድ ስሜት፤ የውስጥ ጥንካሬን የሚፈትን፤ ውስጥን እንደ አለት አጠንክሮ መጓዝን የግድ የሚል።

የህዘን ተቃራኒው ደስታ ሌላው የግርታ ስሜት ውስጥ የሚጨምር ነው፤ ከቀላል እስከ ውስብስብ ግርታ፤ የሕይወትን አቅጣጫ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ሊያስኬድ የሚችል።

### ደስታ

ያልተጠበቀ ሃዘን እንዳለ ሁሉ ያልተጠበቀም ደስታ አለ። ሎተሪ የቆረጠ ሰው ሎተሪው ለምን አልደረሰኝም ብሎ የማዘን እድሉ አነስተኛ ነው። ምክንያቱም ሎተሪ የመድረስ እድሉ ፈጽሞ ዜሮ በሚባል ደረጃ ስለሆነ ብዙም የሚጠብቀው ስላልሆነ። ነገር ግን አንድ ሰራተኛ የወር ደመወዝ እንደማይከፈለው ቢነገረው የሚሰማው ስሜት ቀላል አይሆንም፤ ትልቅ ግርታ። ምክንያቱም የሰራው ስራ እንዲከፈለው የሚጠብቀው በመሆኑ። ለሎተሪ የከፈለ ቢሆንም ሎተሪ የወጣለት ሰው ደስታው እንግዳ ሆኖ የሚገለጽ ነው፤ ያልጠበቀው ስለሚሆን። ከሎተሪም በላይ ፈጽሞ ድንገተኛ የሆነ የደስታ አይነትም አለ፤ ያልጠበቁት ሲሆን የሚፈጠር ደስታ። ለምሳሌ በውትድርና ላይ የተሰማራ የቤተሰብ አባል ሕይወቱን የማለፉ መርዶ ከተሰማ እና ቤተሰብም እርሙን ካወጣ በኋላ ሞቷል የተባለው ግለሰብ በአካል ሲመጣ የሚፈጥረው ስሜት ከባድ ነው። ኢትዮጵያ ለዓለም እግር ኳስ ዋንጫ አለፈች ቢባል ወይንም የዓለም እግር ኳስ ዋንጫን ብታነሳ ስሜቱ ፈጽሞ ለማንም ሰው ቀላል ሊሆን የሚችል ስሜት አይደለም፤ ፍጹም እንግዳ ነገር እንጂ። ለረጅም አመታት ልጅ እምቢ ብሏቸው የቆዩ ጥንዶች ልጅ ሲያገኙ የሚሰማቸው ስሜት ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲሁ መገመት የእንግዳው ነገርን ትርጉም መረዳት ያስችላል። ያልታሰበ ደስታ ነውና ትርጉሙ ብዙ ነው።

በህዘንም ሆነ በደስታ የሚገለጽ ልዩ ትኩረትን የሚስቡ ነገሮች በርካታ ናቸው። ከበርካታ ነገሮቹም መካከል አንባቢው የሚቆጥረው የራሱ ክስተት ይኖረዋል። ሕይወት እንዲህ ባለወቅት ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ ወቅቱን ተቆጣጥሮ ማለፍ መቻል እርሱ ብልሃት ነው። አንዳንድ ሰሞን ካልጠበቅነው ሁኔታ ጋር አገናኝቶን ሊሆን ይችላል፤ ፈጽሞ ካልጠበቅነው። ጥያቄው ሁኔታው ወዴት እንደመራን የሚጠይቅ ነው። ወደ እድገት ወይንስ ወደ ቁልቁለት።

በሁለቱም የእንግዳ ነገር ማሳያዎች ውስጥ የጋራው ነገር፤ ስሜት ነው። ስሜት በደስታም በሃዘንም ጊዜ ትርጉም አለው። የአንድ ሰው ብስለቱም ሆነ ጥንካሬው የሚታየው ስሜቱን በማረቅ ውስጥ እንደሆነ የዘርፉ አጥኚዎች ይገልጻሉ። በውሳኔዎቻችን ውስጥ ስሜት ያለው ቦታ ትልቅ ነው። በተረጋጋ ስሜት ውስጥ ስንሆን ልንሰራ የምንችለው ውጤታማን ስራ ታሳቢ በማድረግ ለስሜት እድገት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንዳለብን እንረዳለን።

ስሜትን መግራት ማለት የስሜት መዋዠቅ በሚያጋጥም ጊዜ አዎንታዊ እርምጃ/positive action/ እንድንወስድ የሚረዳን ተግባር ነው። ለሕይወት ጠቀሜታ ያለውን አዎንታዊ እርምጃ መውሰድ ባለብን ጊዜ መውሰድ በመቻል ውስጥ አትራፊነት አለ። በሕይወት ጉዞ ውስጥ ትርፋማ ለመሆን ስሜትን መግራት ያለውን ቦታ በሚገባ መረዳት አስፈላጊ ነው።

አልበርት አንስታይን የመጀመሪያው የመቻልን አቅም የሚሰጠን ስሜት ከመንፈሳዊነት የሚቀዳው ስሜት እንደሆነ ያምናል። በመንፈሳዊነት ውስጥ አዎንታዊነት፤ ቀናዊነት፤ ስለሌሎች ማሰብ፤ ከምድር ስሌት ውጭ በሆነ ነገር ውስጥ የውስጠኛው አካላችንን እርካታ ማግኘት አለ። ሰዎች ሲሞቱ በቀብር ስነስርዓቱ ላይ የሚነበበው የሕይወት ታሪክ የአንድን ሰው የሕይወት ዘመኑን መንፈሳዊ ስሜትን



የሚያንጸባርቁ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህ ስሜት ከውስጥ ወደ ውጭ የሆነ ስሜት ነው፤ ፈጽሞ በውጫዊው ነገር ላይ ያልተመሰረተ ስሜት፤ ከልብ ውስጥ የሚገኝ። ሔለን ኬለር "የዓለማችን ምርጡና ውብ የሆነው ነገር በአይን የሚታይ እንዲሁም የሚዳሰስ አይደለም ነገር ግን በውስጥ ልብ የሚሰማን ነው" ያለችውን ማስታወስ ይገባል። ዋጋቸው ውድ የሆኑ በእጅ የሚዳሰሱ፤ በአይን የሚታዩ፤ በምላሳችን የምናጣጥማቸው ወዘተ በርካታ ነገሮች አሉ፤ ገበያው የሞላው፤ ብዙ ብር የሚጠይቁን። ነገር ግን ከእዚህ ሁሉ ዋነኛው ከውስጥ የሆነ ነው፤ ከልብ ውስጥ።

የልብ እና የስሜት ቁርኝት ቀጥተኛ በመሆኑ ልብን የሰበረው ነገር ጉዟችንን ይሰብራል፤ ልብን የሚያሞቀው እርምጃችንን ያሞቃል፤ እንግዳው ነገርም ከእዚህ አንጻር የሚታይ ነው። እንግዳ ነገር እንዲገጥመን አስበን የምናደርገው ነገር የለም፤ እንግዳው ነገር ስሜትን በግልጽ አካል ለብሶ እንዲታይ የሚያደርግ በመሆኑ ጠቀስነው።

ከእንግዳ ነገር በተጨማሪም አቅደን ማከናወን በቻልናቸው ነገሮች እንዲሁ ልባችን ውስጥ የሚተከል ነገር አለ። ድርጅት መስርቶ ውጤታማ ማድረግን አቅዶ እርምጃ የጀመረና በተግባርም ማድረግ የቻል ሰው በተጨባጭ ወደፊት እንዲራመድ ያሳካው ነገር ምክንያት ይሆነዋል። ማሳካት ያልቻለው ነገር ደግሞ ስሜቱን ተቆጣጥሮ ወደ ነገው ለመሻገር ይቸገረዋል።

ዛሬ አቅደን በምንተገብረው ነገር ውስጥ የልብን አቅም መገንባት እንድንችል ከትንሽ ጀምረን አቅዶ የመተግበርን ባህል ማዳበር ያስፈልጋል። ይህ እንግዳን ነገር ሳይሆን በተፈጥሮ ሰው የመሆናችንን አቅም ተጠቅመን ልናደርገው የሚገባውን የሚያሳይ ነው። እንግዳ ነገር ግን ከእዚህ ተቃራኒ ነው። በደስታም ሆነ በሀዘን ውስጥ ምእራፉ የሚጀመር ልብን የመግራት፤ ስሜትን የመግራት አቅም ላይ ካልሆንን ደስታውም ሀዘኑም አሉታዊ ሆነው ሊመጡብን እንዲችሉ የሚያደርግ።

ጠንካራ ሰዎች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፉ የሚፈጥሩት ነገር ለሌሎች ነገርን ማቅለል የሚችሉበት ምእራፍ ውስጥ መድረስ ነው፤ ነገሮች በቀለለበት መንገድ ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች ደግሞ ወደ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የመግባት እድላቸው ሰፊ ነው። ይህ ምልልስ በሕይወት ውስጥ በብዙ ግለሰቦች ሆነ ቤተሰብ ውስጥ የሚታይ ነው። ስሜትን በመግራት፤ ልብን በአግባቡ በመያዝ በድምር ውጤቱ ሕይወትን በትክክለኛው መንገድ ውስጥ የማድረግን አስፈላጊነት የሚያሳይ። ድህነትን ታግሎ ያለፈ አባት ለልጆች በቀላል መንገድ ውስጥ ማለፍን ሲያጎናጽፍ እነርሱ በቀላሉ መንገድ ውስጥ አልፈው ጠንካራ ከመሆን ፈንታ በተቃራኒው እንዲገኙ የሚያደርግ ምልልስ ነው። በማግኘት ምክንያት ማጣት፤ በደስታ ምክንያት ሃዘን፤ በገንዘብ ምክንያት ድህነት፤ ወዘተ ማለት ነው።

ግርታ ሲፈጠር፤ ያልተጠበቀው ሲሆን፤ በስሜት ተነድቶ ከመሄድ እየሆነ ያለውን በአንክሮ በመመዘን ወደ ልባችን የመመለስ ጥበብ። በተጨባጭ ሊበዛልን የተገባው፤ ለዛሬ፤ለነገም።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## በፈተና ያልተገታ፤ በጽናት የተገኘ የትጉሃን ስኬት

**አንተነህ ቸሬ**

ከትንሽ ደረጃ ተነስቶ፤ በፈተናዎች ውስጥ አልፎ እውን የሆነ የስኬት ተሞክሮ፣ ከአስደናቂነቱ ባሻገር ለሌሎች ሰዎች የሚፈጥረው መነሳሳትና ሞራል ከፍ ያለ ዋጋ አለው። እንዲህ ዓይነቶቹ የስኬት ታሪኮች ፅናትን፣ ተስፋ አለመቁረጥንና የታላቅ ዓላማ ባለቤትነትን አጉልተው የሚያሳዩ እንደሆኑ ከብዙ ስኬታማ ሰዎች ታሪክ መገንዘብ ይቻላል።

በመሰል የስኬት መንገድ ያለፉ ስኬታማ ሰዎች ለገጠሟቸው ችግሮች አልተንበረከኩም፤ ባገኟቸው ውጤቶችም ተኩራርተው ጉዟቸውን አላቆሙም። ችግሮችን እንደጥንካሬ መመዘኛ ተመልክተው፣ መሰናክሎችን ድል እያደረጉ ከስኬት ወደ ስኬት የተሸጋገሩም ናቸው። የዛሬው የ‹‹ስኬት›› አምድ ባለታሪክም በዚህ ዓይነት የሕይወት ተሞክሮ ያለፈ ባለተሞክሮ ነው።


ዋልተንጉሥ መጨጊያው ይባላል። የ‹‹ማኅበረ ትጉሃን የእንጨትና ብረታ ብረትና ኮንስትራክሽን ስራ ድርጅት›› መስራችና ስራ አስኪያጅ ነው። በ1972 ዓ.ም የተወለደው ይህ ዋልተንጉሥ፣ ተወልዶ ያደገውም ሰሜን ሸዋ፣ ደራ ወረዳ አካባቢ ነው።

በጎልማሳነት እድሜ ላይ የሚገኘውን ዋልተንጉሥን በሥራ ስኬቱና በእድሜው የአንቱታ ከበሬታ የሚገባው ቢሆንም አንተ ብለን ማውጋቱን ወደናል። ዋልተንጉሥ የሕይወት ፈተናን ማየት የጀመረው በለጋነቱ ነበር። በመጀመሪያ እናቱን ቀጥሎም አባቱን በሞት የተነጠቀው ዋልተንጉሥ፣ በ13 አመቱ ታናናሾቹን የመርዳት ኃላፊነቱን መቀበል ግድ ሆነበት። ለመሥራት ደግሞ ወደ ከተማ መውጣት ነበረበት። ሥራን ሀ ብሎ የጀመረው ጫማ በማሳመር (በመጥረግ) ነው። ጫማ አሳምሮ በሚያገኘው ገቢ፣ እንጀራ እየጋገረ ታናናሾቹን አሳድጓል። ራሱን በትምህርት ለማብቃት ባደረገው ጥረት ስምንተኛ ክፍል ደርሷል።

በዚህ መንገድ ኑሮውን እየገፋ ሳለ ነበር ‹‹ሰዎች ለሰዎች›› (Menschen für Menschen) ከተሰኘው ምግባረ ሰናይ ድርጅት ጋር በ1992 ዓ.ም የመተዋወቅ ዕድሉን ያገኘው። ድርጅቱም የአናፂነትንና የግንባታ ሙያ ክህሎት እንዲያገኝ እገዛ አደረገለት። ድርጅቱ በቀን 25 ብር እየከፈለው ነበር የሙያ ባለቤት ያደረገው። ‹‹ለማደግና ለመለወጥ ያስቻለኝ ‹ሰዎች ለሰዎች ድርጅት› ነው። እዚያ ገብቼ ሙያ መልመዴ ለዚህ አብቅቶኛል›› የሚለው ዋልተንጉሥ፣ ዛሬ ለደረሰበት ስኬት ያበቃውን ድርጅት ውለታም አልዘነጋውም።

ድርጅቱ ውስጥ ሆኖ በቀሰመው እውቀት ሲሰራ ባጠራቀማት ሦስት ሺ ብር በጉንደመስቀል ከተማ፣ ‹‹ማኅበረ ትጉሃን የእንጨት፣ ብረታ ብረት እና ኮንስትራክሽን ስራ ድርጅት››ን በ1995 ዓ.ም በማቋቋም ከእህቱ እመቤት መጨጊያው ጋር በመሆን የእንጨት ስራ ጀመረ። በሂደትም ወንድሞቹን ወደዚሁ ስራ በማስገባት አብረው መሥራቱን ተያያዙት። ወደ ግል ሥራ ከገባ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ነበር ትዳር የመሠረተው። በአካባቢው ላይ በግል በጀመረው የእንጨት ስራ የቆየው ለስምንት ዓመታት ብቻ ነበር። በ2003 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጣ።

ዋልተንጉሥ ወደ አዲስ አበባ የመጣበት ውሳኔው የቆራጥነት፣ የተስፋና የጽናት መገለጫ ተደርጎ የሚቆጠር ነው። ‹‹የቤተ መንግሥት አስተዳደር የሰንበሌጥ ሳር በጨረታ አወዳድሮ መግዛት እንደሚፈልግ የሚገልፅ የጨረታ ማስታወቂያ ‹አዲስ ዘመን› ጋዜጣ ላይ አነበብኩ። ጨረታውን እንደተመለከትኩ ለናሙና የሚሆን ሰንበሌጥ ሳር ይዤ ከደራ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። ‹የሥራ ዘርፍህ የእንጨትና የብረታ ብረት ስራ ስለሆነ፣ ያቀረብከው ለጨረታው ብቁ አይሆንም› ተብዬ የጨረታው ጉዳይ ሳይሳካ ቀረ። ሳር ተሸክሜ ቤተ መንግሥት አካባቢ ስዘዋወር የተመለከቱኝ የቤተ መንግሥቱ ጥበቃ አባላት ይገረሙ ነበር። ጨረታው ባይሳካም እዚሁ ሆኜ ስራ እሰራለሁ እንጂ ወደ ደራ አልመለስም ብዬ በአዲስ አበባ ስራ ለመጀመር ጥረቴን ቀጠልኩ›› በማለት ወደ አዲስ አበባ የመጣበትን አጋጣሚ ያስታውሳል።



**ዋልተንጉሥ መጨጊያው፤**

አዲስ አበባ ስራ ለመጀመር የቆረጠው ዋልተንጉሥ፣ አዲሱ ገበያ ተብሎ የሚታወቀው አካባቢ ቤት ተከራይቶ ስራ ጀመረ። የመስሪያ እቃዎችን በዱቤ እያፈላለገና በጓደኞቹ ድጋፍና ምክር እየተበረታታ ስራውን በብርታትና በተስፋ ጀመረ። ከተቀጣሪነት ይልቅ የራሱን ስራ በመፍጠር እሳቤ ሦስት ሰራተኞችን በመቅጠር የጀመረው ስራ፤ መልክ እየያዘለትና ስኬት እያገኘበት መጣ።

ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ የእቃ መደርደሪያና ማስቀመጫ (ሎከር) እና ሌሎች የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስን እያመረተ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ለትላልቅ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ጭምር ማቅረቡን ቀጠለበት። ስራውን በተገቢው ጥራትና ከተሰጠው ጊዜ ቀደም ብሎ ማስረከብንም መለያው አደረገ።

ይህ ታታሪነቱ ደግሞ ከተቋማቱ አመኔታን አትርፎለት። ከ40 በላይ ትላልቅ ተቋማት ለስራው ጥረትና ቅልጥፍና ማረጋገጫ የሚሆን የምስክር ወረቀት ሰጥተውታል። ከእነዚህ መካከል አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ሐረማያ፣ ዋቸሞ፣ ደብረ ታቦር፣ አምቦ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ዲላ፣ ደብረ ብርሃን፣ ድሬዳዋ፣ ባሕር ዳር፣ ሚዛን ቴፒ፣ ሰመራ፣ መቱ እና የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲዎች ይጠቀሳሉ። የዳግማዊ ምኒልክ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን እና የትምህርት ጽሕፈት ቤት፣ የዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የደራ ወረዳ አስተዳደር፣ የፍቼ ከተማ አስተዳደር፣ አጋርፋ ግብርናና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ እና ኢካፍኮ አክሲዮን ማኅበር ሌሎች የምስክር ወረቀት የሰጡት ተጠቃሽ ተቋማት ናቸው።

የእንጨትና ብረታብረት ስራው ጥሩ መስመር እየያዘለትና ስኬት እያገኘበት ሲመጣ ቤተሰቦቹን አዲስ አበባ በማምጣት ከባለቤቱና ከልጆቹ እንዲሁም ከወንድሞቹ ጋር እየኖረ ስራውን ቀጠለ። ብዙ ደንበኞችን እያፈራ፣ በስራውም የበለጠ ልምድ እያገኘ መጣ።

‹‹ማኅበረ ትጉሃን የእንጨትና ብረታ ብረትና ኮንስትራክሽን ስራ ድርጅት›› በአሁኑ ወቅት ለ40 ሰዎች የስራ እድል የፈጠረና 40 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያለው ምስጉን አምራች ተቋም መሆን ችሏል።

ዋልተንጉሥ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ጉዞው ቀላል እንዳልነበር ያስረዳል። የአሁኑ ስኬቱ በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፎና ጫናዎችን ተቋቁሞ የተገኘ ድል ነው። ያሳለፉቸውን ጊዜያት ዛሬ ላይ ሆኖ ሲያስታውሳቸው የዛሬው ስኬቱ በቀላሉ እንዳልተገኘ ይገነዘባል። ‹‹ስኬታማ ለመሆን ተግቶ መስራት ያስፈልጋል። እሰራለሁ ብሎ ቃል የገቡትን ስራ በጊዜና በጥራት ለማጠናቀቅ መትጋት ይገባል። ስራን በጥራትና በፍጥነት አጠናቅቆ ማስረከብ የደንበኞችን እምነት ያስገኛል። እኔም ሁልጊዜም ቢሆን በዚህ መርህ እየተመራሁ ይህን መርህ ለመተግበር እጥራለሁ›› በማለት ይገልፃል።

በስራ ሕይወቱ አስፈሪና አስደንጋጭ የሆኑ አጋጣሚዎችንም አልፏል። ለአብነትም ደራ በነበረበት ወቅት ያጋጠመውን እንዲህ ሲል ያስታውሳል። ‹‹ደራ በነበርኩበት ጊዜ ለእንጨት ስራ ግብዓት የሚሆን ዋንዛ የምናመጣው ከገጠር ተሸክመን ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ዋንዛ ለማምጣት ከጓደኞቼ ጋር ዋንዛው ወደሚገኝበት ስፍራ በሌሊት ሄድን። እንጨቱ የሚገኝበት ቦታ ደግሞ ገደላማ ነበር። በዕለቱ በነበረው ኃይለኛ ነጎድጓድ (መብረቅ) ምክንያት እኔና ጓደኞቼ ገደል ልንገባ እግዚአብሔር ነው ያተረፈን›› በማለት ይህ ክስተት እስካሁን ድረስ በጣም ከሚያስገርሙት አጋጣሚዎቹ መካከል አንዱ እንደሆነ ይናገራል።

ለስራው የሚያስፈልጉ የአንዳንድ ግብዓቶች እጥረት፣ የቦታ ጥበት እና በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ብድር ማግኘት አለመቻል በስራ ሂደት ላይ ካጋጠሙት ችግሮች መካከል ዋነኞቹ እንደሆኑ የሚናገረው ዋልተንጉሥ፤ ‹‹ለትልልቅ ተቋማት ብዙ ምርቶችን በፍጥነትና በጥራት ለማቅረብ ሰፊ የመስሪያ ቦታ ይፈልጋል። ምርቶቻችንን ለብዙ ተቋማት እንደምናቀርብና በስራውም ጥሩ ውጤት እያገኘን እንደሆነ በመረዳት መንግሥት የቦታና የብድር አቅርቦት ቢያመቻችልን ከዚህ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንችላለን›› በማለት መንግሥት ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ይጠይቃል።

ዋልተንጉሥ ችግሮችን የምሬትና መሰናክል ምንጭ አድርጎ ከማየት ይልቅ የጥንካሬ መመዘኛና የብቃት መፈተኛ አድርጎም ይመለከታቸዋል። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ‹‹ብዙ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ዋናው ቁም ነገር ለችግሮችና ለፈተናዎች አለመበገርና በፅናት ታግሎ ማሸነፍ ነው›› ብሎ የሚናገረው።

ዋልተንጉሥ ከስራውም ባሻገር በሌላው የሕይወት ዘርፉም በአርዓያነት የሚጠቀስ ስኬት አለው። ባለትዳርና የአራት ልጆች (አንድ ወንድና ሦስት ሴቶች) አባት ነው። ከቤተሰቡ፣ ከጎረቤቶቹ፣ ከስራ ባልደረቦቹ ጋር እጅግ ሰላማዊ የሆነ ግንኙነትና ትብብር አለው። በማኅበራዊ ሕይወቱም ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል።

ዋልተንጉሥ የመገልገያ መሳሪያዎችን እየሰራ አቅም ለሌላቸው ተቋማት፣ በተለይም ለትምህርት ቤቶች፣ ያበረክታል። ‹‹እኔ በችግር ውስጥ ስላለፍኩ ሌላውንም መርዳት ተገቢ ነው። ሁሉንም የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። የተቸገረ ሰው ድጋፍ ቢደረግለት ለውጥ እንደሚያመጣ ስለማውቅና የቻልኩትን ያህል ባደርግ ለኅሊናዬ ደስታን ስለሚሰጠኝ የአቅሜን ያህል በመደገፍ እሳተፋለሁ። ያደረግኩትን ሁሉ ዘርዝሬ መናገር ግን አያስፈልግም›› በማለት መስጠትና ሌሎችን ማገዝ ‹‹እንዲህ አድርጌያለሁ›› ብሎ ከመናገር ይልቅ በትህትና መታጀብ እንዳለበት ምርጫው መሆኑን ጠቁሟል።

ስራዎቹን በፍጥነትና በጥራት ለደንበኞቹ በማቅረቡ ካገኛቸው ምስጋናዎችና እውቅናዎች በተጨማሪ የሚጠበቅበትን ግብር በአግባቡ ለመንግሥት የሚከፍል በመሆኑም የገቢዎች መስሪያ ቤት የምስክር ወረቀት ሰጥቶታል።

የ‹‹ማኅበረ ትጉሃን የእንጨት፣ ብረታ ብረትና ኮንስትራክሽን ስራ ድርጅት›› ስራዎች ለደንበኞች ጥራት ያላቸውን ምርቶች በፍጥነት ከማቅረብ ባሻገር፣ ከውጭ ይገቡ የነበሩ የቢሮ እቃዎች በአጭር ጊዜና በተመጣጣኝ ዋጋ በአገር ውስጥ ተመርተው የውጭ ምንዛሬን በማዳን ለአገር ትልቅ ፋይዳ እያበረከቱም ነው። በዚህ ረገድ ዋልተንጉሥ ‹‹ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከውጭ ያስገባቸው የነበሩትን እቃዎች እኛ እዚሁ አገር ውስጥ በጥሩ ሁኔታ በመስራት አቅርበንለታል። ኦዳ ቡልቱ ዩኒቨርሲቲም ከውጭ ሊያስመጣው የነበረውን ምርት እኛ እዚሁ በመስራታችን ተቀባይነት አግኝቷል›› በማለት የድርጅቶቹ ምርቶች ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካት አቅም እንዳላቸው ማስመስከራቸውን ያስረዳል።

‹‹ዓላማ ያለው ሰው ትኩረቱን ስራው ላይ ብቻ ያደርጋል›› የሚለው ዋልተንጉሥ፣ ወጣቶች ማድረግ ስለሚገባቸውም ይመክራል። ‹‹ወጣቶች የሚያገኙትን ገንዘብ ማባከን የለባቸውም። ‹ይቺ ምን ታደርግልኛለች?› ከማለት ይልቅ መቆጠብና ለተሻለ ዓላማ ማዋል ይገባቸዋል። ደራ በነበርኩበት ጊዜ ጓደኞቼ ‹ይቺን ገንዘብ መኪና እንግዛባት› ሲሉ እኔ ግን ገንዘቡን እንዳያጠፉትና ቆጥበነው ሌላ ስራ ሰርተን እንደምንለወጥለበት እነግራቸው ነበር። በተጨማሪም ወጣቶች አልባሌ ቦታ መዋል የለባቸውም። የሰው ልጅ ዋነኛ ሀብት ሙያ ስለሆነ የሙያ ባለቤት ለመሆን መትጋት ይጠበቅባቸዋል!›› በማለት ይመክራል።

ዋልተንጉሥ ከትንሽ ተነስቶ ዛሬ ለሚገኝበት ትልቅ ደረጃ መብቃቱ ‹‹የስኬት ጫፍ ላይ ደርሻለሁና ይበቃኛል›› ብሎ እንዲቀመጥ አላደረገውም። ድርጅቱን አሁን ካለበት የተሻለ የማድረግ ዓላማና ርዕይ አለው። ‹‹የወደፊት እቅዳችን ተጨማሪና የተሻሉ ማሽኖችን እንዲሁም መሬት በማግኘት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ የማምረት ኢንቨስትመንት ላይ በስፋት መሰማራት ነው ። ሰፊ ስራ ሰርቼ ሁሉም ሰው የሚጠቀምበትና አገር የሚለውጥ ድርጅት እንዲሆን ምኞቴ ነው›› በማለት ስለወደፊት እቅዱና ዓላማው ይናገራል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# ዘመናዊ እና ባህላዊ የመስኖ ዘዴዎች የሚተገበሩበት የወይቦ መስኖ ፕሮጀክት

መላኩ ኤርሴ

በኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት አመታት መንግስት ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል።አርሶ አደሩ ዝናብ ጠባቂ ብቻ ከመሆን እንዲወጣ እየተደረገ ባለው ርብርብ ለመስኖ እርሻ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ከመስኖ እርሻም በበጋ መስኖ ስንዴ በማልማት ላይ ርብርብ መደረጉን ተከትሎ ውጤት እየታየ ነው፡፡

ቀደም ባሉት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም እንኳን በወንዝ እና ሀይቅ አካባቢዎች መስኖ በዋናነት አትክልትና ፍራፍሬ እየተመረተ የቆየ ቢሆንም፣ ዋና ዋና ሰብሎችን በመስኖ በብዛት ለማምረት፣ በተለይም ስንዴን ለማምረት መጠቀሙ በስፋት ያልተገበረ አሰራር ነው። ከቅርብ አመታት ወዲህ ይህ ሁኔታ ተቀይሯል፡፡

መንግስት ለመስኖ ልማት በሰጠው ትኩረት የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴርን አቋቁሟል፡፡ ሚኒስቴሩም የመስኖ መሰረተ ልማቶችን በመገንባቱ ስራ ተጠምዷል፡፡ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትሯ ኢንጂነር አይሻ መሀመድ በቅርቡ የአምራችነት ቀን በተከበረበት ወቅት እንዳሉት፤ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ምሶሶ የሆነውንና ሰፊ የሰው ኃይል በመያዝም ድርሻ ያለውን የግብርና ሥራ በመስኖ መደገፍ ግዴታ የሆነበት ጊዜ ላይ ተደርሷል፡፡ መስኖ ለልማት እንዲውል በብዛት የመስኖ መሠረተ ልማት እንዲከናወን መንግሥት ጥረት አድርጓል፡፡

በ2013-2014 የምርት ዘመን የግብርናው ዘርፍ ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆን የመስኖ አገልግሎት ጥቅም ላይ መዋል አስተዋጽኦ ማድረጉን ጠቅሰው፣ ለእዚህም የቆላና የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ይጠቀሳል ሲሉ አስታውቀዋል፡፡ የግብርና ሥራ በመስኖ እንዳይደገፍ ማድረግ በግብርና ምርታማነት ላይም ሆነ ኢንዱስትሪዎች ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችልም ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ በስንዴ ልማት ራስን ከመቻል ባለፈ ለውጭ ገበያ በማቅረብም የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማግኘት እንደ አገር የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚጠበቅበትን ተልዕኮ በላቀ መልኩ ለመወጣት ወደ አንድ ሚሊየን ሄክታር መሬት የሚሆን የእርሻ ማሣ በመስኖ እንዲለማ ለማስቻል ዝግጁ ነው፡፡ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመሆን ተልእኮውን ይወጣል፡፡

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ የተጀመረው በቆላማ አካባቢዎች ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በመላ አገሪቱ ተስፋፍቷል፡፡ በሁሉም የአየር ንብረቶች ላይ ወንዞችን በመጥለፍና በመሳሰሉት መንገዶች ልማቱ እየተካሄደ ነው፡፡ በተጠናቀቀው 2014 በጀት አመት ብቻ ከ600 ሺ ሄክታር በሚበልጥ መሬት ላይ በተካሄደ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከ26 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ማግኘት ተችሏል፡፡ በተገኘው የስንዴ ምርትም አገሪቱ የአገር ውስጥ የስንዴ ፍላጎቷን ማሟላትና ለስንዴ ግዥ ይወጣ የነበረንም የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት ችላለች፡፡ ልማቱ የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንና ሌሎች ተቋማትን ትኩረት ሳይቀር መሳብ ችሏል፡፡

መንግስት የመስኖ እርሻዎችን ለማስፋፋት መስራቱን ቀጥሏል፤ በአገሪቱ በተያዘው 2015 በጀት አመት በበጋ መስኖ የሚታረሰውን መሬት ወደ አንድ ሚሊየን በማድረስ 40 ሚሊየን ኩንታል ስንዴ ለማምረት እቅድ ተይዟል፡፡ በዚህም የአገር ውስጥ ፍላጎትን ከማሟላት ባሻገር ወደ ጎረቤት አገሮች ለመላክ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ክልሎችም የየራሳቸውን እቅድ አዘጋጅተው በበጋ መስኖ ልማቱ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ የኦሮሚያ ክልል ብቻ በቅርቡ እንዳስታወቀው አንድ ሚሊየን ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ለማልማት አቅዷል፡፡ በክልሉ ለመስኖ ስራው የሚያስፈልጉ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች ለአርሶ አደሮች የማቅረብ ስራም እየተከናወነ ነው፡፡

በየክልሎቹ ስንዴ በመስኖ የማልማት ስራው ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፣ የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታዎችም እየተካሄዱ ናቸው፡፡ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴርም የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታዎችን በተለያዩ ክልሎች እያካሄደ ነው፤ ከእነዚህ ፕሮጀክቶቹ አንዱ በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን የሚገነባው ነው፡፡

የወላይታ ዞን በኢትዮጵያ ውስጥ ለመስኖ ምቹ ከሚባሉ አካባቢዎች መካከል የሚጠቀስ እንደመሆኑ የግድቡ መገንባት በርካታ ፋይዳዎች ይኖሩታል። ዞኑ በመስኖ ሊለማ በሚችል ለም የወል እና የአርሶ አደር ማሳ የታደለ ነው፡፡ በአካባቢው ወይቦ፣ ጋሞ፣ ሻፋ፣ ሶኬ፣ ቁሌ እና ዎተሬን ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ የማይደርቁ ብዙ ወንዞች ይገኛሉ፡፡ ይህም አካባቢውን ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ ያደርገዋል፡፡

አካባቢው ለመስኖ ልማት የሚሆን መሬት እና ውሃ የታደለ ቢሆንም፣ እስካሁን በመስኖ የለማው መሬት መጠን በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ከዞኑ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ በዞኑ ለመስኖ ያለውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከነዚህ ጥረቶች አንዱ በቆላማ አካባቢዎችና መስኖ ልማት ሚኒስቴር ባለፈው በጀት ዓመት ግንባታው የተጀመረው የወይቦ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ነው፡፡

ወይቦ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት በሁለት ነጥብ 44 ቢሊየን ብር በጀት፣ በባለግርማ ሞገሱ ወይቦ ወንዝ ላይ የሚገነባ ነው፡፡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታው በኅዳር 2014 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን፣ በሰኔ ወር 2017 እንዲጠናቀቅ የጊዜ ሰሌዳ ተቀምጦለታል፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ብዙነህ ቶልቻ እንደሚሉት፤ ፕሮጀክቱ ለአካባቢው አርሶ አደሮች ከፍ ያለ ፋይዳ የሚያስገኝ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ እየተገነባ ያለው በወላይታ ዞን በቦሎሶ ሶሬ ወረዳና በቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ መካከል ነው፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ በቦሎሶ ሶሬ ወረዳ በአራት ቀበሌዎችና በቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ ደግሞ በሰባት ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖሩ ከ12 ሺህ በላይ አርሶ አደሮችን በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ ለመስኖ ምቹ የሆነ መሬት እያላቸው በዓመት ዝናብ በመጠበቅ አንድ ጊዜ እያመረቱ ያሉ አርሶ አደሮች ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲያመርቱ ያስችላቸዋል፡፡

> **ፕሮጀክቱ እየተገነባ ያለው በወላይታ ዞን በቦሎሶ ሶሬ ወረዳና በቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ መካከል ነው፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ በቦሎሶ ሶሬ ወረዳ በአራት ቀበሌዎችና በቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ ደግሞ በሰባት ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖሩ ከ12 ሺህ በላይ አርሶ አደሮችን በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ያደርጋል። አርሶ አደሮች ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲያመርቱ ያስችላቸዋል**

እንደ አቶ ብዙነህ ገለፃ፤ ፕሮጀክቱ ሦስት ሺህ 371 ሄክታር መሬት ለማልማት ያስችላል፡፡ ከዚህ ውስጥም አንድ ሶስተኛው ፈሮ በሚባለው የመስኖ ዘዴ (በትንንሽ የመስኖ ቦዮች አማካኝነት) የሚለማ ነው፡፡ ቀሪው ሁለት ሶስተኛው ደግሞ በዘመናዊው የርጭት ዘዴ እንዲለማ ማድረግ ያስችላል፡፡ ይህም ፕሮጀክቱን ከሌሎች ፕሮጀክቶች ልዩ ያደርገዋል፡፡

የወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የግድቡ ርዝመት 660 ሜትርና ከፍታው ደግሞ 33 ሜትር ነው፤ በ630 ሄክታር መሬት ላይ ውሃው ወደ ኋላ የሚተኛ ሲሆን፣ ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ 60 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ የመያዝ አቅም አለው። ይህም ውሃው በአካባቢው ከመስኖ ባሻገር ለሌላ ተጨማሪ አገልግሎት እንዲውል እድል ይፈጥራል፡፡

ይህ ውሃ ከመስኖ ግብርና በተጨማሪ ለቱሪስት መስህብነትና ለዓሳ ምርት ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የወይቦ ፏፏቴ የቱሪስት መስህብ እየሆነ ይገኛል፡፡ ግድቡ ሲጠናቀቅ የሚፈጠረው ሰው ሰራሽ ሀይቅ ከፏፏቴው ጋር በመሆን አካባቢውን ይበልጥ የቱሪስት መዳረሻ ያደርገዋል፡፡

ፕሮጀክቱ እጅግ ግዙፍ ከመሆኑ ባሻገር የአካባቢውን ኢኮኖሚ የማነቃቃት እድል ስለሚኖረው ለሚገነባበት አካባቢ ህዝብ ጠቀሜታ እንደሚያስገኝ የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡

ግንባታው እየተካሄደ ባለበት በአሁኑ ወቅትም ቀላል የማይባል ጥቅም እያስገኘ ነው፡፡ ለ185 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል በመፍጠር የስራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ ለሚደረገው ጥረት የራሱን አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ወደፊትም ተጨማሪ የስራ እድሎችን የመፍጠር አቅም አለው፡፡

እንደ አቶ ብዙነህ ማብራሪያ፤ ወይቦ ፕሮጀክት ሁለት ሎቶች አሉት፡፡ ሎት አንድ ግድብ እና ተያያዥ ስራዎችን ያካትታል፤ ይህም በደቡብ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እየተገነባ ይገኛል፡፡ ሎት ሁለት ደግሞ ከመስኖ መሬት መዋቅር ዝግጅት ጋር ይያያዛል። ይህም የሚገነባው ከርስ ሳንድ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ጋር በሽርክና (ጆይንት ቬንቸር) በመቀናጀት ነው፡፡ ሎት አንድ ስድስት በመቶ የደረሰ ሲሆን፤ የሎት ሁለት አፈፃፀምም ተመሳሳይ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪ አካል የደቡብ ዲዛይንና ቁጥጥር ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

አቶ ብዙነህ፤ ፕሮጀክቱን እያጋጠሙ ካሉ ተግዳሮቶች መካከል የስራ ተቋራጩ የአቅም ውስንነት እና ከወሰን ማስከበር ጋር የተያያዙ ችግሮች ዋነኞቹ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በተለይም የልማት ተነሺዎች የተጋነነ የካሳ ክፍያ መጠየቅ እና የዲዛይን ማሻሻያ በማስፈለጉ የዲዛይን ማሻሻያ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ መጠየቁ ለፕሮጀክቱ መጓተት ምክንያት ሆነዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት የሎት አንድን አፈፃፀም ወደ 20 በመቶ እንዲሁም የሎት ሁለትን ደግሞ ወደ 41 በመቶ ለማድረስ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ብዙነህ፤ ፕሮጀክቱን ለማፋጠን ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡ ለችግሮቹ የመፍትሄ አማራጮች ተቀምጠውለት በዚያው መሰረት ክትትል እየተደረገ ነው ይላሉ፡፡

የወሰን ማስከበር ስራዎች እና የመስኖ ግንባታው ጎን ለጎን እየተሰሩ መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ ብዙነህ፤ የልማት ተነሺዎች ከቦታው የሚለቁት ተቋራጩ እና አማካሪው ለመስኖ ፕሮጀክት የሚውለውን ቦታ ካዩት በኋላ ነው፡፡ ካሳ ተከፍሎ የማስነሳት አሰራር እንደሚተገበርም ጠቁመዋል፡፡

ካሳ ከፍሎ መነሳት ያለባቸውን ነዋሪዎችን አስነስቶ ተቋራጩንና እና አማካሪን ወደ ቦታው የማስገባት ሁኔታ ከአሁን በፊት እንዳልተለመደ የሚያነሱት አቶ ብዙነህ፤ ለዚህም ዋናው ምክንያቱ የመስኖ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ አርሶ አደሩ መሬቱን መጠቀም አለበት የሚል እሳቤ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም መሰረት በቅድሚያ የተወሰኑ አርሶ አደሮችን በማስነሳት ግንባታው እንደተጀመረና በሂደት ሌሎች አርሶ አደሮችን የማስነሳት ስራ እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የወሰን ማስከበር ጉዳይ ሳይጠናቀቅ የሚጀመሩ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች የወሰን ማስከበር ችግር በተደጋጋሚ ሲያጋጥማቸው ይስተዋላል፡፡ የወሰን ማስከበር ችግሮችን ቀድሞ በማጠናቀቅ የፕሮጀክቶች ግንባታ ቢጀመር ከወሰን ማስከበር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች በዘላቂነት መፍታት ይቻላል፡፡ የወሰን ማስከበር ጉዳይ ሳይጠናቀቅ ግንባታው የሚጀመር ከሆነ ግን የወሰን ማስከበር ችግሮችን ለመፍታት አደጋች ይሆናል፡፡

እንደ መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መረጃ ለፕሮጀክቱ ሌላኛው ተግዳሮት እየሆነ ያለው ጉዳይ የተቋራጩ የአቅም ውስንነት ነው፡፡ አገር በቀል ተቋራጮችን ለማበረታታት ፕሮጀክቶች ለአገር በቀል ተቋራጮች መሰጠታቸው የሚበረታታ ነው፡፡ ነገር ግን የአገሪቱ የግንባታ ኢንዱስትሪ የልምድ እጥረት ያለበት እንደመሆኑ ለግንባታዎች ተግዳሮት ሲሆን ይስተዋላል። በመሆኑም የተቋራጮችን አቅም የማጠናከር ስራዎች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

የትኛውም ፕሮጀክት እውን እንዲሆን የአካባቢው ማህበረሰብ የነቃ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ የአካባቢው ህብረተሰብ በአጠቃላይ የሚሰጠውን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት በመገንዘብ ለፕሮጀክቱ መሳለጥ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ በቅርቡ ፕሮጀክቱን የጎበኙት የደቡብ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር እና ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ይገዙ አሳስበዋል።

የፕሮጀክቱ ግንባታ እስኪጠናቀቅ የዞኑ እና የወረዳው መንግሥት በቅርበት አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክቱ ግንባታ በተባለው ጊዜ እንዲጠናቀቅ መሃንዲሶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ፕሮጀክቱ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ፋይዳ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ልዩ ትኩረት እንዲሰጡም ጠይቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለትግራይ ሕዝብ ተጨማሪ እልቂት የደገሰው የአሸባሪው ትህነግ የክተት ጥሪ!

አሸባሪው ትህነግ ለግማሽ ክፍለ ዘመን የትግራይን ሕዝብ ለእኩይ ዓላማው በመገበር ህልውናውን ያቆየ ቡድን ነው፡፡ በዚህም አያሌ የትግራይ ልጆች ለቡድኑ ከንቱ ዓላማ በከንቱ አልቀዋል፤ ሌሎች አያሌዎችም በከንቱ አካላቸውን አጥተዋል፤ የቡድኑን ዓላማ የተቃወሙ በርካታ የትግራይ ልጆችም እንዲሁ በቡድኑ ሴራ በአጭር ተቀጭተዋል፤ ተሰነካክለዋል፡፡

ቡድኑ ለ27 ዓመታት ከቆየበት ስልጣን በኢትዮጵያውያን መራር ትግልና ብርቱ ክንድ መውረዱን ተከትሎም በተለያየ መንገድ አገርና ሕዝብ ማድማቱን ቀጥሏል፡፡ የትግራይ ሕዝብ አገራዊውን ለውጥ ተከትሎ በመጣው የፌዴራል መንግስት እንዲሁም በምርጫ ስልጣን በያዘው መንግስት ላይ እንዲነሳ፣ በተለይ ከትግራይ ሕዝብ ጋር በብዙ መልኩ የዘመናት ትስስር ባለው የአማራ ሕዝብ ላይ ጥላቻ እንዲያሳድር አልፎም ተርፎም የእሱን የጥፋት ዕቅድ እንዲፈጽም በሚያደርጋቸው ትንኮሳዎች፣ በሚያቀጣጥላቸው ግጭቶችና በሚከፍታቸው ጦርነቶች ሁሉ የትግራይን ሕዝብ መማገዱን ቀጥሎበታል፡፡

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ያጣውን ስልጣን በኃይል ለመቆናጠጥ የያዘውን ከንቱ ቅዠት ለማስፈጸም ሲነሳም ሆነ ጦርነት ሲከፍት የቆየው ታጣቂዎቹን በማሰለፍ ብቻ አይደለም፤ የትግራይን ሕዝብ ከህጻን እስከ አዛውንት ለጦርነት እየማገደም ጭምር እንጂ፡፡

በህግ ማስከበር ዘመቻው ተሸንፎና ወደ ዋሻው ተመልሶ በአገር ላይ የሚያደርሰው ጉዳት አልበቃ ብሎት የትግራይን ሕዝብ ባለህ መሳሪያ፣ ቢላዋም ሆነ አካፋ መከላከያን ተፋለም ብሎ ጥሪ ሲያስተላልፍ የነበረ ቡድን ነው፡፡

የሰው ሕይወት ምንም ግድ የማይሰጠው ይህ የሽብር ቡድን ህዝባዊ ማእበል በሚባል ያረጀ ያፈጀ የጦርነት ዘይቤ በትግራይ በህግ ማስከበር ስራ ላይ በነበረው የአገር መከላከያ ሰራዊት እንዲሁም በህልውና ዘመቻው ወቅትም ሊያሳድር የሞከረው የስነ ልቦና ጫና በቀላሉ የሚታይ አይደለም፤ ይህም ሁኔታ ለሕዝብ ትልቅ ዋጋ እየከፈለ የነበረውን የመከላከያ ሰራዊት ስራ በእጅጉ ፈታኝ አድርጎትም ነበር፡፡

መከላከያ የተናጠል የተኩስ አቁም አድርጎ ሙሉ ለሙሉ ትግራይን ለቆ ከወጣ በኋላም የአማራና የአፋር ክልሎችን የወረረው በዚሁ ሕዝባዊ ማዕበል በሚለው ኋላቀር መንገድ ነው፡፡ በዚህ ጦርነት ያሰለፈው የሰለጠነ ታጣቂ ቁጥር ስፍር የለውም፡፡ በዚህም ላይ በሕዝባዊ ማዕበሉ ህጻናትን፣ ነፍሰጡሮችን፣ አዛውንት ባልቴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን ጭምር ከፊት በብዛት በማሰለፍ፣ የሰለጠነውን ታጣቂ በማስከተል እኩይ ዓላማውን ለማሳካት ተንቀሳቅሷል፡፡

ይሁን እንጂ ያሰለፈውን ሕዝብ የጥይት እራት ከማድረግ ውጭ አንዱም ቅዠቱ አልተፈጸመም፡፡ አዲስ አበባን ከሩቅ እያማተረ፣ ሰሜን ሸዋ ላይ አይቀጡ ተቀጥቶና ብትንትኑ ወጥቶ ወደ ትግራይ ተመልሷል፡፡ በዚያ ጦርነት የረገፈውን የትግራይ ትውልድ ታሪክ አንድ ቀን ይፋ ይወጣል፡፡ የትግራይ እናቶች ልጆቻችን የት አሉ ብለው ወደፊት ሲጠይቁ የሚደረስበትም ይሆናል፡፡

ከዚህ ስህተቱ ያልተማረው ይህ አሸባሪ ቡድን በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ሁለቴ /የቡድኑ ለሶስተኛ ጊዜ ይሆናል/ እንደተወጋው ሞኙ አውሬ ለሶስተኛ ጊዜ በከፈተው ጦርነትም ዘንድሮም እንዳምናው ህጻናትን፣ አዛውንት ባልቴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ወዘተ. ከፊት ለፊት አሰልፎ ጦርነት እያካሄደ ይገኛል፡፡ መነኮሳትን አዛውንቶችንና አይነ ስውሮችን ቦምብ አስይዞ፣ ከጦርነቱ ፊት አሰልፏል፡፡

በዚህ ጦርነት በትጥቅ ትግል ወቅትም ይሁን ከዚያ በኋላ ያፈራውን የሰለጠነ ታጣቂ፣ ትምህርት ቤቶችን ዘግቶ የትግራይን ወጣትና ህጻናት በሙሉ አሰልፏል፡፡ ከአንድ ቤተሰብ አንድ ልጅ ወደ ግንባር መሄድ አለበት፣ ይህን ያላደረገ ቤተሰብ እርዳታ አይሰጠውም በማለትም ቢያንስ ቢያንስ ከእያንዳንዱ ቤት አንድ ሰው ወደ ግንባር እንዲሄድ አድርጓል፡፡ በዚህ ጦርነት ያልተሳተፈ የትግራይ ሀብት ተጋሪ እንደማይሆንና ልዩነት እንደሚፈጠርበት በማሳሰብም ወጣቶችን ለጦርነቱ አሰልፏል፡፡ ይህ ሁሉ በራሱ ትልቅ አሃዝ ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነው እንግዲህ ሕዝባዊ ማዕበል በሚል ስያሜ ውጊያ እያካሄደ የሚገኘው፡፡

አሸባሪው ቡድን ሰሞኑንም ለሶስተኛ ዙር በከፈተው ጦርነትም የትግራይ ሕዝብ በሙሉ ለጦርነቱ እንዲዘጋጅ ሌላ ክተት ጠርቷል፡፡ የትግራይ ሕዝብ አርሶ አደር፣ ወጣት ፣ህጻናት ፣ አዛውንቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ወዘተ በጦርነቱ ፊት ለፊት እንዲሰለፉ ተደርገው እያለ የክተት ጥሪው ማንን እንደሚጠራ ግልጽ ባይሆንም፣ የቡድኑ አረመኔያዊት አሁንም እየከፋ መምጣቱን ያመለክታል፡፡ የክተት ጥሪው ቤት የቀሩትም ቤት እንዳይቀሩ የሚያደርግ ዓይነት ነው፡፡ ቀዬ የሚጠብቁትን እናቶችን አባቶችን ሌሎች ህጻናትንም የሚምርም አይመስልም፡፡

በመሰረቱ አሸባሪ ቡድኑ ሁሌም ለጦርነት እየተዘጋጀ፣ ሁሌም ጦርነት እየከፈተ ያለ፣ በዚህም ሕዝቡን እንዳስጨነቀ የኖረ እንደመሆኑ ከክተት ጥሪ ውጭ ሆኖም አያውቅም፡፡

የክተት ጥሪው የቡድኑን ጭካኔ ጥግ የሚያሳይ፣ የጥፋት ዓላማውን ለማሳካት የሚከፍታቸውን ጦርነቶች፣ የሚፈጽማቸውን ታሪክ ይቅር የማይላቸው አሳፋሪ ድርጊቶችን ተከትሎ የሚደርሱበትን ምቶች ለመከላከል እንደለመደው በሕዝብ ውስጥ ተደብቆ እኩይ ዓላማውን ለማሳካት የሚያደርገው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ እኩይ ዓላማውን ለማሳካት ወደ ጦርነት እሳት ውስጥ የማይወረውረው ትግራዋይ እንደማይኖርም ይህ የክተት ጥሪም በሚገባ ያመለክታል፡፡

ይሁንና ከድሃ ጉሮሮ እየነጠቀ ለጦርነት ያዘጋጀው ልዩ ኃይል፣ የቀድሞ ታጋይ፣ ከየቤቱ አንድ ሰው በግድ ወደ ጦር ሜዳና፣ ህዝባዊ ማዕበልን በተደጋጋሚ የተጠቀመው ይህ የሽብር ቡድን አሁንም ሕዝብን ለአስከፊና ዓላማ ለሌለው እልቂት ከማደረግ ውጭ የሚያገኘው አንዳችም ትርፍ እንደማይኖር ይታወቃል፡፡ የያዘው የጥፋት ዓላማም ሆነ ይህን ለማስፈጸም የሚከተላቸው የትኛዎቹም መንገዶች የትም እንደማያደርሱትም የታወቀ ነው፡፡

የትግራይ ሕዝብ የዚህን ቡድን አረመኔያዊ አካሄድ ተገንዝቦ ይህ የሞት ጥሪው እንዲከሽፍ በሚችለው መንገድ ሁሉ ርብርብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የዘላቂ ሰላም ዋናው መንገድ ሰላማዊ አማራጭ መሆኑን የሚያምኑ አካላትም ሁሉ ቡድኑ ከያዘው ሕዝብ ጨራሽ ተግባሩ እንዲቆጠብ ለማድረግ መስራት ይኖርባቸዋል!

---


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


---

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የጦርነት ሱስ የተጠናወተው አሸባሪው ትህነግ

**ፌኔት ከብርጭቆ**

በየጦር ግንባሮች ሽንፈት ሲደርስበት ሰላም ፈላጊ መስሎ ሕዝቡን ለማታለል ብቅ ብሎ ይዘላብዳል፡፡ እየጠየቅኩ ያለሁት «ሰላም ብቻ ነው¡» እያለ ይለፍፋል፡፡ በዚህ መሀል ሌላ የጦርነት ዕቅድ ለማዘናጋት ይሞክራል። ደግሞ ባዘጋጀው ስልት በተቃራኒው ጊዜ ገዝቶ በድጋሚ ወደ ጦርነት ይገባል፡፡

ሰላም ወዳድ አስመሳዩ፤ ነገር ግን የጦርነት ሱሰኛው አሸባሪው ትህነግ የትግራይ ህዝብ እልቂት አያሳስበውም። ያሸነፈ ሲመስለው «የሰላም አማራጭ ከመጀመሪያውም የማይሆንና የትግራይን ሕዝብ ጥያቄ ፈፅሞ የማይፈታ መሆኑ የታመነበት ነው » እያለ በአደባባይ ይናገራል፡፡ በአንድ እራስ ሁለት ምላስ የሽብር ቡድኑ መለያ ነው፡፡ ነገሩ ሁሉ መያዣ መጨበጫ የሌለው ሙልጭልጭ ነው፡፡

የሽብር ቡድኑን አምኖ ለመወያየትም ሆነ ለመደራደር ዕቅድ ማዘጋጀት እና ቀጠሮ መያዝ አዳጋች ነው፡፡ ዛሬ ፈቃደኛ መሆኑን ገልጾ፤ ሳይውል ሳያድር ያለውን እንደገና ይክዳል፡፡ የሚገባው ቃል ሁሉ በቅጥፈት የታጀበ ነው። ቡድኑ በቅርቡ የጦርነት ማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድ ብሎ በነደፈው እና ሾልኮ የወጣው ሰነድ ፤ «በጦርነት ሂደት ውስጥ የመረጃ ልዕልና ለማግኘት እና በርካታ ሃይሎችን ከጎን ለማሰለፍ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች አንዱ፤ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ቁርጠኝነት እንዳለ አስመስሎ ራስን ማቅረብ ነው» ይላል።

ይህ በግልፅ እንደሚያሳየው የሽብር ቡድኑ የሰላም ፍላጎቱን እንደሌለው፤ ስለሰላም የሚያወራቸው ወሬዎች ሁል ከልብ ያልሆኑ ዓለም አቀፉን ህብረተሰብ ማዘናጊያ እንደሆኑ ነው፡፡

«ሰላም እፈልጋለሁ» የሚለው ደጋፊ ለማግኘት እንጂ የቡድኑ የሁልጊዜም ምርጫው ጦርነት መሆኑ ለማንም የተደበቀ አይደለም ማወቅ ለሚፈልግም ብዙ ሳይደክም የተወሰነ ያለፈ ታሪኩን ማየት ብቻ በቂ ነው። በቀደመው ዘመን፤ ወደ ስልጣን ከመጣና ከስልጣን ከተወገደ በኋላ የለኮሳቸው ጦርነቶችን ማየት በራሱ ስለቡድኑ ጦረኝነት የሚለው ብዙ አለ ፡፡

ቡድኑ የጦርነት ማጠቃለያ ምዕራፍ በሚል ባሰናዳው ሰነድ በግልፅ እንደተብራራው፤ «በአማራ ክልል በተወሰነ መልኩም ቢሆን ፊቱን ወደ ልማት ያዞረ ገበሬ እየታየ ነው። ይህ ወደ ልማት ፊቱን ያዞረ ሃይል የማያዳግም እርምጃ ሊወሰድበት ሲገባ የተፈጠረውን ጊዜያዊ ክፍተት (ሰላም) በመጠቀም ፊቱን ወደ እርሻው መልሷል፤ ይህ ሃይል የእርሻ ውጤቱን ወደ ቤቱ እንዲያስገባ ልንፈቅድለት አይገባም » ሲል የትግራይ ወጣት የአማራ ክልል ገበሬን ለመውጋት እንዲነሳ እየገፋፋ እና እያበረታታ በህዝቦች መካከል ግጭቶችን መፍጠር እንደ አንድ ስትራቴጂ የሚጠቀምበት መሆኑን አሳውቋል፡፡

ከዚህ ባለፈም "ኢትዮጵያውያን ለጦርነት ባልተዘጋጁበትና መንግስት በሰላም ጥሪ በተዘናጋበት ጊዜ አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል" ሲል በዋናነት ምርጫው ሰላም ሳይሆን ጦርነት ብቻ መሆኑን በሰነዱ ላይ አሳይቷል፡፡

የሽብር ቡድኑ «የእርሻ ዘርፉ እንዲደናቀፍ በየአካባቢው ግጭት በመቀስቀስ እና ግጭት ለመቀስቀስ የሚያስችሉ ሃይሎችን በማገዝ እረፍት በመንሳት፣ መንግስት የልማት ስራዎችን ትቶ እሳት ማጥፋት ላይ እንዲጠመድ ማድረግ አለብን » በማለት አገርን ለማዳከም ሕዝቡ የሚበላውን ለማሳጣት ልማትን ማደናቀፍ እና ለውጭ ጠላቶች መሳሪያ መሆን እንደዋነኛ ውጊያ የመጠቀም ፍላጎት እንዳለው በግልፅ አሳይቷል፡፡

የሽብር ቡድኑ ጦርነቱን በመሳሪያ በዓውደ ውጊያ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም መዋጋት ሥራው እንደሚሆንም አስቀምጧል፡፡ ጠላት ይቀባል ጥላሸት እንደሚባለው አገሩን የሚጠብቀውን፤ በተለያዩ አገራት ሰላም ለማስከበር ወጥቶ በድል የሚመለሰውን፤ የአገር ኩራት የሆነውን መከላከያን፤ እንዲሁም አገር በተሻለ መንገድ እንድትሔድ እየሠራ ያለውን መንግስት የሁለቱንም ስም በተለያዩ መንገዶች ማጥፋት የየዕለት ተግባሩ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ እርሱ እንዳረጋገጠው ይህ ተግባሩም አንዱ የጦርነት ሱሱን የማስታገሻ መንገዱ ነው።

«መንግስት እና መከላከያ የትግራይን ሕዝብ ሊፈጁ አቅደዋል፡፡ መከላከያ ከጎረቤት ክልሎች ጋር ሆኖ የትግራይን መሬት በሃይል እየወረረ ነው፡፡ መከላከያ ሰብል እያቃጠለ፣ ንብረት እየዘረፈ፣ ሴቶችን እየደፈረ ነው፡» ከሚለው የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ጀምሮ የተለያዩ ወሬዎችን በመንዛት በተግባር በውሸት መንግስት እና አገርን በመውጋት የሽብር ቡድኑ የጦርነት ሱሱን በማስታገስ ላይ ይገኛል።

ቡድኑ በተለይ ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም በተለያዩ አካባቢዎች ምክንያት የሌለው ግጭቶች በመፍጠር በአገሪቱ በዘላቂነት ሰላም እንዳይሰፍን የማድረግ ሥራን በመስራት በኩልም ተወዳዳሪ አልተገኘለትም፡፡ አገሪቱን ወደ የማያቋርጥ ጦርነትና መከራ ለማስገባት ተደጋጋሚ ሙከራዎችን በተለያዩ አካባቢዎች አድርጓል።

በአደባባይ ጦርነት ከማወጅ በተጨማሪ ባይሳካለትም ተልዕኮውን ያነገቡ ሰዎችን በማሰማራት አገሪቱ በጦርነት እንድትታመስ ብዙ ሰርቷል፡፡ ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ከሚንቀሳቀሰው ሸኔ ጋር በመሆን በኦሮሚያ የጥፋት ተልዕኮ ለመፈፀም ሲሰራ መቆየቱን በመረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በስትራቴጂው ላይ ይህንን እየሠራ ስለመሆኑም በዝርዝር አብራርቷል፡፡

በተጨማሪ ጦርነቱን ሲያካሂድ የኢትዮጵያን ዕድገት ከማይፈልጉ የውጭ ሃይሎች እና ከአጎራባች ሃገሮች ጋር በሚስጢር ግንኙነት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶችም የሽብር ቡድኑን ሰራዊት ከማሰልጠን በተጨማሪ በአገሪቱ ላይ የተለያዩ ጫናዎችን ለመፍጠር መሞከራቸው አልቀረም፡፡

የሽብር ቡድኑ በዚህ በኩልም አገሪቱን ወደማያባራ ጦርነት ብቻ ሳይሆን፤ መቋጫ ወደሌለው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውስ ሊያስገቡ የሚያስችሉ ስራዎች በመስራት በተለያዩ መንገዶች አገሪቱን የከፋ ችግር ውስጥ ለመክተት እየታተረ መሆኑን በሾለከው ሰነድ ታይቷል።

ይህ ሁሉ ሲታይ ቡድኑ የተገነባበት ማንነት ሙሉ ለሙሉ በግጭት /በጦርነት/ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ለማወቅ አያዳግትም፡፡ በተጨማሪ ጦርነት በዘላቂነት እንደ ዋነኛ ሱስ የተጠናወተው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ከመነሻ እስከ ዛሬ ጊዜውን በጦርነት ለማሳለፍ ቆርጦ የተነሳው ይህ ቡድን የአንድ መንግስት ጠላት ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያውያን ጠላት ሆኖ ለመቀጠል የወደደ መሆኑን እያንዳንዱ ዜጋ ማወቅ አለበት፡፡

ምንም እንኳን አንዳንድ የትግራይ ተወላጆች በቅጡ ባይገባቸውም፤ የሽብር ቡድኑ በዋናነት የትግራይ ሕዝብ ጠላት መሆኑን በተደጋጋሚ ለዓለም አሳይቷል። ያለውን የማታለል ስልት ሁሉ በመጠቀም በክልሉ ሕዝባዊ ተቀባይነቱን ለማስቀጠል ቢሞክርም ሕዝቡን ከመጥቀም ይልቅ አሁንም ድረስ እየሠራ ያለው ሕዝቡን መሳሪያ አድርጎ እየተዋጋበት ነው፡፡ ህዝቡን እንደሰው ሳይሆን እንደመገልገያ ዕቃ እየተጠቀመባቸው ይገኛል፡፡

«የትግራይ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ መወሰን የሚያስችለውን መብት ለማግኘት ረጅምና መራራ ትግል የሚጠይቀው መሆኑን ባለፉት አመታት በተካሄደ ትግል ተምሯል » የሚለው የሻለከው ሰነዱ፣ ይህ ቡድን በምንም መልኩ ፍላጎቱ ዕድሜ ልኩን የትግራይ ህዝብን መጠቀሚያ በማድረግ የማያባራ ጦርነትን ማስጀመር ብቻ ሳይሆን ማስቀጠልንም ታሳቢ ያደረገ ነው።

የዚህ ቡድን አገርን ወደማያባራ ጦርነት የመክተት ቅዠቱ ፍፁም እውን ሊሆን አይገባም፡፡ እርሱ የሚሠራውን ሴራ ለማክሸፍ ከዚህ በላይ እንዳያደክም እና ሌላ ተጨማሪ ዋጋ እንዳያስከፍል የጦርነት ሱሱን እንዲያቆም በዋናነት የትግራይ ሕዝብ ለቡድኑ እምቢተኝነቱን በመግለጽ እራሱን ነጻ የማውጣት ትግል መጀመር ይኖርበታል፡፡

የትግራይ ህዝብ ነቅቶ የጦርነት ሱስ የተጠናወተውንና መቼም የማይለቀውን ይሄንን ቡድን «አንቅሮ ሊተፋው እና መጠቀሚያ አታደርገኝም፡» ሊለው ይገባል፡፡ ይህንን ለማለት ሽርፍራፊ ደቂቃዎችን ማባከን አይጠበቅበትም። ለሁሉም ጊዜው አሁን ነው!።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፣ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# «ቢያንስ የእኔ መከራ በልጆቼ አይደገም.....»

እፀገነት አክሊሉ

መልክና ቁመናዋን ላስተዋለ ኑሮ አብዝቶ የፈተናት መሆኑ በግልጽ ያስታውቃል። ገጽታዋ ለቅሶና ሃዘን የበዛበት ይመስላል፤ ጠይሙ ፊቷ ብዙ ይናገራል፡፡ ጥቂት ላሰበ በወይዘሮዋ ውስጥ የተዳፈነ ችግር ስለመኖሩ መገመት አያስቸግርም፡፡ በየአፍታው በዓይኖቿ የሚመነጨው ዕንባ በሕይወቷ ብዙ መከራ ማለፏን ያሳያል፡፡

ወይዘሮ ትርሲት ሸዋ ውልደትና ዕድገቷ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ ወትሮም ቢሆን ኑሮ ምቹ ሁኔታን ያልፈጠረላት ወይዘሮ ትርሲት ከደሃ ቤተሰብ መወለዷ ነገሮች ገና በጠዋት እንዲፈትኗት ምክንያት ሆኗል፡፡ ኑሮዋ ዛሬ ላይ ይበልጥ ከፋ እንጂ ለችግርና መከራ አዲስ አይደለችም፡፡ ኑሮ ከውልደቷ ጀምሮ ፊቱን ያዞረባት እንጂ እናት፣ አባት፣ እህትና ወንድም ነበሯት፡፡ በሕይወት አለመግባባጠም እናትና አባቷ እሷን ጨምሮ የወለዷቸውን ልጆች በቅጡ ሳያሳድጉ ነው የተለያዩት፡፡ ትርሲት ሕይወቷን ከአባቷ ጋር ነው የገፋችው፡፡

ቀን ስራን እየሰሩ የሚያስተዳድሯት አባቷ ከእለት እለት እድሜያቸው እየጨመረ የኑሮ ጫናን ብቻቸውን መቋቋም እያቃታቸው ሲሄድ ትርሲት እኔም ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ? ከኔም ምን ይጠበቃል? ብላ ማሰቧ የእለት ተእለት ግዳጇ ሆነ፡፡

በዚህ አስከፊ የኑሮ ሁኔታ ምክንያት ትምህርቷን በአግባቡ መማር ያልቻለችው ትርሲት ገና ከጅምሩ ትምህርቷን አቋርጣ እሷንና አባቷን ሊያኖር የሚችል ሌላ አማራጭ ማማተር ጀመረች፡፡ ብዙ አሰበች አወጣች አወረደች ምን ብትሰራ እሷና አባቷ ቢያንስ የዕለት ጉርሳቸውን ሊያገኙ እንደሚችሉ አወጣች አወረደች መልሱን ማግኘት ግን ቀላል አልሆነላትም፡፡ ይህ ደግሞ በትምህርቷ ብቻ ሳይሆን በጤናዋ ጭምር መቃወስን አስከተለ፡፡ መኖር አስጠላት ደካማ አባቷ ተሯሩጠው የሚያመጡትን መብላት የኮሶ ያህል መረራት፡፡ እና ምን ላድርግ ብላ አሰበች፤ አሁንም ለራሷ በቂ መልስ አጣች፡፡ ከእናቷ ጋር ያሉት እህት ወንድሞቿ ከሷ የተሻሉ ባለመሆናቸው «እንረዳዳ» ለማለት እንኳን አትችልም፡፡ ሌላ በሕይወቱ ተሳክቶለት እነሱን ሊደግፍ የሚችል ዘመድም ሆነ ጓደኛ አልያም የቅርብ ሰው የለም፤ ብቻ ለትርሲት ኑሮ ጠመመባት ፡፡

አንድ ቀን በአጋጣሚ ፒያሳ አካባቢ ሴቶችን ለስራ ወደአረብ አገር የሚልክ ደላላ መኖሩን ሰማች፤ በአስከፊ የሕይወት አጣብቂኝ ውስጥ ያለችው ትርሲትም ይህን እድል በከንቱ ማባከን ወይም አጋጣሚውን ማለፍ አልፈለገችም፤ እናም ወደተባለበት ቦታ በፍጥነት በመሄድ ተመዘገበች፡፡ ክፍያ ያለመኖሩ ደግሞ ይበልጥ አጓጓት፤ ደስም አላት፡፡

በፍጥነት ጊዜ ሳታጠፋ ወደተባለው ቦታ አመራች፡፡ የሰማችው እውነት ነበር፤ እሷና መሰሎቿን ወደአረብ አገር በነጻ ለመላክ ደላላው ተፍ ተፍ ይላል፡፡ አሁን በሕይወቷ ትንሽ ተስፋ የፈነጠቀ መሰላት፡፡ ያ ከውልደቷ ጀምሮ ሲጫወትባት የኖረውን ድህነት ድል እንደምትነሳው አይነት ስሜት ተሰማት፡፡

ደላላው ያስፈልግሻል ያላትን ሁሉ እንደምንም በማሟላት ለጉዞ ዝግጁ ሆነች፡፡ ተጠርታ ለእሷ የተስፋ ምድር ወደምትሆናት ቤሩት እስክትገባ ድረስ አንዱ ቀን ሁለት እየሆነ ቆጠረችው፡፡ ያቺ በጉጉት የተጠበቀችው ቀን አልቀረችም መጣች፡፡ ትርሲትም ደካማ አባቷን ከቤት ትታ ለራሷም ለእሳቸውም ቀን አወጣለሁ ስትል ተመኘች፡፡ ያሰበችው አልቀረም የስደት መንገዷን በአውሮፕላን ጉዞ አንድ ብላ ጀመረች፡፡

ከቤቷ ከወጣችበት ቀን ጀምሮም ሰርታ አባቷን ለመጦር ለእሷም ቅርስ የሚሆን ነገር አድርጋ በአገሯ ላይ በሰላም መኖር ሃሳብ ህልሟ ሆነ፡፡ የሰው አገር ግን እንደ አሰበችው ያልተቀበላት ወይዘሮ ትርሲት አንገፍግፏት የሄደችው መከራና ስቃይ በሚገርም ሁኔታ ባህር አቋርጦም ተከተላት። አሁን ትርሲት ቤሩት ደርሳለች ቀጣሪዎቿም ከአውሮፕላን ማረፊያ መጥተው ወስደዋታል፡፡ እሷም አዲሱን የሕይወት መንገዷን ልትጓዝ ሰርታ ልታገኝ ሽማግሌ አባቷን ልትጦር ብዙ እቅድ ላይ ነች፡፡ ከዛ ሁሉ በላይ ደግሞ ጥሩ ተመግባ ጥሩ ኑሮን መኖር ትልቁ ህልሟ ነበር፡፡

የትርሲት ህልም እንዳሰበችው እየሄደ አይደለም፤ እንደውም በሚገርም ሁኔታ ከነበረችበት ችግር የባሰ



ወይዘሮ ትርሲት ሸዋ

ሆነባት፡፡ የስራው መብዛት፣ እረፍት የለሹ ድካም የምግብ በቂ አለመሆንና አለመስማማት የአሰሪዎቿ ቀጭን ትዕዛዝና ቁጣ የደመወዝ በጊዜው አለመከፈል፤ ኧረ ! ምኑ ቅጡ ሁሉም ነገር ግራ አጋባት፡፡ይህ ነው እንዴ የቤሩት ኑሮ? ሰው እንዲህ ሆኖ ነው ሰርቶ የሚለወጠው? የሚሉት ጥያቄዎች ደግሞ ተመላልሰው ወደአእምሮዋ እየመጡ አስጨነቋት፡፡

እነዚህና ሌሎች ጭንቀቶች በአንድ ፊት አገሯ ላይ ጥላቸው የሄደችው ነገ ሰርቼ ገንዘብ ልኬ የእርጅና ዘመኑን በተሻለ ይኖራል ስትል ያሰበችላቸው አባቷ አሳሰቧት። ከምንም በላይ ደግሞ አባቷ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ለማወቅ የምትችልበት መንገድን ማጣቷ ከስራውና እረፍት ማጣት ጋር ተደማምሮ ህመም ሆነባት፡፡

አሁን ያለችው ሰው አገር ባህር አቋርጣ ብዙ ማይሎችን ተጉዛ ነው፤ በቃ አልፈልግም አገሬ ልግባ ብላ ብድግ የምትልበት ዕድል የለም፡፡ በዚህ መካከል የጤናዋ ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ ከችግር እየገባ መታመም ይዛለች። ምንነቱን የማታውቀው በሽታ ስቃይዋን እያሳያት ነው፡፡ እንዳትታከም የሰራችበት በወቅቱና በአግባቡ አይከፈላትም፤ ወደቤሩትም የገባችበት መንገድ ህጋዊ ባለመሆኑ እንደልቧ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አትችልም፡፡ ይህ ተደራራቢ ችግር መፈጠሯን እንድትጠላ አደረጋት፡፡

ትርሲት በዚህ ሁኔታ መቀጠል አልቻለችም፡፡ እናም የሆነ ነገር መወሰን እንዳለባት ተሰማት፤ ከምትሰራበት ቤት ደመወዟን እንኳን ሳትወስድ መጥፋትን ብቸኛው አማራጯ አደረገች፣ በዚህ ብቻ አልቆመችም ከምትሰራበት ቤት በድንገት ተሰወረች፣ ጠፋች፡፡

ትርሲት ከምትሰራበት ቤት ትጥፋ እንጂ ሌላ አማራጭ ኖሯት አይደለም፡፡ በእጇ ላይ አምስት ሳንቲም የላትም።ብቻ ካለችበት ፈታኝ ሁኔታ ለመውጣት ስትል ነው የጠፋችው፡፡

ተደራራቢ ስራ፣ እረፍት ማጣት፣ በወጉ አለመመገብ አስመርሯት ከአሰሪዎቿ ቤት ጠፍታ የወጣችው ትርሲት አሁንም ነገሮች አልጋ በአልጋ አልሆኑላትም፤ እንደውም ይባስ አስጨናቂ አስፈሪ ቀናትን ማሳለፍ አስገዳጅ ሆነባት፡፡

ከአንዱ ጓደኛ ወደሌላ እየተዘዋወረች ማደር ያገኘችውን ከፖሊስ እየተደበቀች መስራትና የእለት ጉርሷን መቻል ብቻ ሆነ አላማዋ ከአገሯ ስትወጣ ሰንቃው የነበረው ተስፋና ህልሟ ሁሉ አሁን አብሯት የለም፡፡ ከዛ ይልቅ እንዴት ከፖሊስ አምልጣ ዛሬን ማደር እንደምትችል ማሰላሰል ሆነ ስራዋ፡፡ የትርሲትን ችግር ተረድተው ያስጠጓት የነበሩት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ብቻ አይደሉም፤ ፊሊፒንስና ሱዳናዊ ዜግነት ያላቸው ሰዎች ጭምር እንጂ፡፡

ወይዘሮ ትርሲት ወትሮውንም ቢሆን በጤናዋ ላይ ሙሉነት አይሰማትም ነበር፤ በተለያዩ ጊዜያት ጎሽም እያደረጓት የሚያልፉ ህመሞችም አልጠፉም፤ ነገር ግን በዚህ የችግር ጊዜዋ ውስጥ ሆና ድንገታዊ የሆስፒታል አልጋ የሚያስይዝ ህመም አጋጠማት፤ ህጋዊነትን ባልያዘችበት አገር ከጎኗ የእኔ የምትለው ሰው ሳይኖራት መታመሟ አሳዛኝም አስደንጋጭም ሆነባት፡፡ “ሳይደግስ አይጣላም” እንዲሉ ወይዘሮ ትርሲት በህመሟ ምክንያት ከፍ ያለ ጭንቀት ውስጥ ብትገባም ህጋዊ ወረቀቱን ተጠቅሞ ወደሆስፒታል የሚወስዳት አሳክሞ የሚያድናት ደግ ሱዳናዊ አገኘች፡፡ ይህ አጋጣሚ ፈጣሪ የተላከላት እንደሆነ አሰበች። የሆነው ሁሉ ሆነ፡፡ ለእኔ ልትገልጽልኝ ያልፈለገችውን ህመም በሰው አገር በኦፕሬሽን አውጥታ ታክማ አገገመች።

አሁን ወይዘሮ ትርሲት ከበሽታዋ አገግማ በአካል ጎልብታለች፡፡ ዛሬም ግን ከጎኗ የሚሆን ዕንባዋን የሚያብስ ዘመድ የላትም፡፡ አባቷንም በተለያዩ ጊዜያት በተለይም አመት በዓል ሲሆን ያላትን ታካፍላቸው እንጂ እንደ ልጅ ያሳበችውን ያህል ልታግዛቸው አልቻለችም፡፡ ማንም እንደሌላት የምታውቀው ወጣት አጋር እንደሚያሻት ልቧ ሹክ እያላት ነው፡፡

ትርሲት በህመሟ ምክንያት ድንገት ካወቀችው ሱዳናዊ ጋር መግባባት ይዛለች፡፡ ሱዳናዊው እንደእሷ እንጀራ ፈልጎ ከአገሩ የተሰደደ ወጣት ነው፡፡ ስደት ቢያመሳስላቸውም እሱ ህጋዊ ነው፡፡ እሷ ደግሞ ህገወጥ ስደተኛ መሆኗ ያለያያቸዋል፡፡ ህክምናዋን በእሱ አማካይነት ካደረገች በኋላ አብረው መዋል ማደር ጀምረዋል፤ እሱን ባገኘችው ቁጥር ጎዶሎዋ የሞላ፣ ቀኗ የፈካ ይመስላታል፡፡

ዓይኑን የጣለባት ሱዳናዊ በዚህ ብቻ አላበቃም፤ ልቧን ተረክቦ ልቡን አስረከባት፡፡ የሁለቱ ግንኙነት ፍቅር ቢያሸንፍ ቁምነገር አሰቡ፡፡ ትዳር ይዘው ጎጆ ቀልሰው መኖር ጀመሩ፡፡

ጥንዶቹ በትዳር ዘልቀው ቤት ሲያቀኑ መተሳሰባቸው ነገን የሚያሻግር ሆነ፡፡ የአብሮነታቸቸው መስመር ጠንክሮ ዓመታትን በአንድ ኖሩ፡፡ ፍቅራቸው በመኖር ብቻ አልተጋመሰም፡፡ ሁለቱን በአንድ የሚያጣምር፣ ሕይወት ኑሯቸውን የሚያሳምር ፍሬ አገኙ፡፡ ትዳራቸው በልጅ በረከት ታደሰ፡፡ የመጀመሪያ ልጃቸውን በፍቅር እያዩ አቅፈው ሳሙ፡፡ ወይዘሮ ትርሲትም ዳግም ነገ የመኖር ተስፋዋ ለመለመ፡፡ አሁን የምኖርለት ከጎኔ ሆኖ ችግር ደስታዬን የሚካፈለኝ የእኔ ሰው አለኝ ማለት ጀመረች፡፡

ትርሲት ከልጇና ከባለቤቷ ጋር ሕይወትን ቀጥላለች። ምንም እንኳን የስደት መንገዷ በዚህ መልኩ ይሆናል ብላ ባታስብም በተለይ ልጇን ስታይ ደስ ይላታል፡፡፡፡ ተስፋዋ ይለመልማል፡፡ ነገ የተሻለ እንደሚሆን ታስባለች፤ ብቸኛ የሆነችባቸው ዓመታት አሁን በእጥፍ የደስታ ቀናት እያጣጣመቻቸው ነው፡፡ ዛሬ ልጇና ባለቤቷ ጎዶሎዋን ሞልተዋል፣ ዓለሟን አሳምረዋል፣ ዕንባዋን አብሰው ፈገግ ታዋን መልሰዋል፡፡

ወይዘሮ ትርሲት በአንድ ልጅ አላበቃችም ከአመታት ቆይታ በኋላ ሁለተኛ ልጅ ደገመች፡፡ አሁን የእሷም ሆነ የሱዳናዊው የትዳር አጋሯ ደስታ ከፍ ብሏል፡፡ በልጅ በረከት መባረኳ ልዩ ስሜትን ፈጥሮባታል፡፡

አሁን ላይ ትርሲት እንደሌሎች ሰዎች ወጥታ አትሰራም ባለቤቷ ሰርቶ የሚያመጣውን እየተቀበለች ልጆቿን ነው የምታሳድገው? ስለጤናቸው አመጋገባቸው ብቻ በየሰዓቱና በየደቂቃው ስላላቸው ሁኔታ ከመከታተል በእነሱ ውስጥ ነገን አሻግራ ከማየት የዘለለ ሃሳብም ስራም የላትም፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው አንድ በሕይወቷ ያጋጥመኛል ብላ ያላሰበችው ዱብ እዳ ወደቤቷ ገባ፡፡ ወይዘሮ ትርሲት በጣም አዘነች አብቦ የነበረው ተስፋዋ እንደጉም ሲበን እንደጤዛ ሲረገፍ ተሰማት፤ እሷን ካለችበት የጤና ችግር አላቆ አሳክሞና አድኖ በትዳር ይዞ የሁለት ልጆች እናት ያደረጋት ሱዳናዊው ባሏ በድንገታዊ ህመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡ እጅግ ከባድ ጊዜ ሆነባት፡፡ እድሜዋን ሙሉ ችግር እየተከተለ ለምን እንደሚያሳድዳት አልገባ አላት። የሁለት ህጻናት ሴት ልጆቿ ነገ አስጨነቃት ምን ላድርግ ምን ልሁን ብላ አሰበች፡፡ ለጊዜው ከማልቀስ በቀር ይህ ነው የሚባል መፍትሔን ለራሷ መንገር ሳትችል ቀረች፡፡

ሆድ ቀን አይሰጥም፣ በተለይ ምኑንም የማያውቁት ህጻናት ስለችግር ቢነግሯቸው፣ በያባብሏቸው አይገባቸ ውም፡፡ ወይዘሮ ትርሲት ልጆቿን ለማብላት ስትል የተወቸውን እዚህም እዚያም የማለት ስራ ጀመረች፡፡ እሱም ቢሆን ቀላል አልነበረም፡፡ ልጆቿ ላይ ቤት ዘግታ በየሰው ቤት በመዞር ጽዳትና ያገኘችውን ስራ እየሰራች የእለት ጉርሳቸውን ለማሟላት ጣረች፡፡

“የአገሬው ሰው መልካም ነው ፤ ይህንን ያልኩበት ዋናው ምክንያቴ ልጆቼ እንዳይራቡ ሁሌም የሚችለውን ያደርግ ነበር ትምህርት ቤትም አስገብተውልኝ ይማሩም ነበር በዚህ በጣም አመሰግናቸዋለሁ” ትላለች ስለነበራት ቆይታ ስታስታውስ፡፡

“የሰው ቤት ቢያምሹበት አያድሩበት” ነውና ወይዘሮ ትርሲትም ምንም እንኳን ከአገሯ ተሰዳ የሄደችበት አላማ ግቡን ባይመታም ሁለት ልጆችን ግን አግኝታለች። እረዳሃለሁ ብላ ትታቸው የሄደቻቸው አባቷም በችግር ምክንያት በገቡበት የአረጋውያን መጦሪያ ማዕከል ውስጥ ሕይወታቸው ማለፉን ሰምታለች፡፡

ችግርና ሃዘን ሕይወቷን ሙሉ የሚያሳድዷት ትርሲት የአባቷን ሃዘን በሰው አገር ልትወጣው ግድ አላት። ሃዘኗን ከጨረሰች በኋላ ግን ቤሩት ላይ የሚያቆያት አንዳች ምክንያት አጣች፡፡ ልጆች ጥላ እንደልቧ መስራት አልቻለችም፡፡ ልጆቿን የሚይዝላትም አላገኘችም፤ በመሆኑም አገሯ ገብታ የሆነችውን ለመሆን ወሰነች፡፡

አገሯ ስትገባም የት አርፋለሁ የሚለው ጉዳይ አንዱ አሳሳቢ ጉዳይ ሆነ፡፡ አባቷ በሕይወት ዘመናቸው የኖሩባት አንዲት ክፍል የቀበሌ ቤት እንዳለች ታውቃለች፡፡ ቢያንስ ልጆቼን ይዤ አንገቴን አስገባበታለሁ ብላ በማሰብ ደጋግ ኢትዮጵያውያን ከነልጆቿ ወደአገሯ እንዲልኳት ለምና ወደትውልድ አገሯ ተመለሰች፡፡

ወይዘሮ ትርሲት አገሯ መድረሷ ቢያስደስታትም ሽብ ረብ ብሎ የሚቀበላት እንደማይኖር ታውቃለች፡፡ በእጇ ኢትዮጵያውያኑ አዋጥተው ከሰጧት ጥቂት ገንዘብ በቀር ምንም የለም፤ ከአውሮፕላን ወርዳ ወደዛች የምታውቃት የአባቷ አንድ ክፍል የቀበሌ ቤት አመራች፡፡ ያየችውን ማመን አልቻለችም፡፡ ቤቱ ተተኪ የለውም በሚል በወረዳው አካላት ታሽጓል፡፡ ሌላ ንዴትና ተስፋ መቁረጥ ውስጧ ገባ። ያሳደጓት የሚያውቋት ጎረቤቶቿ ግን ከነልጆቿ ሰብስበው ቢያንስ የመንገድ ድካሟን አራግፋ ወደቀጣዩ የሕይወት መስመር ትገባ ዘንድ አገዟት፡፡

ዋል አደር ብላ ወረዳው ጽህፈት ቤት ሄዳ ልጅነቷን በመናገር ቤቱ እንዲከፈትላት ጠየቀች፤ እነሱም መልካም ፈቃዳቸው ሆነ፡፡ ቤቱን በመክፈት ወይዘሮ ትርሲት ለአገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ የሆኑ ልጆቿን ማሳረፍ ቻለች፡፡

ትርሲት አመታትን በችግር በገፋችበት የስደት ሕይወት ያተረፈችው ነገር ቢኖር ልጆቿ ብቻ ናቸው፡፡ በልጆቿ ተስፋ ታደርጋለች፡፡ ዛሬም በአንዲት ክፍል ቤቷ ውስጥ ልጆቿ የማያውቁትን ባህልና የችግር ኑሮ ይኖሩ ዘንድ ፈርዳባቸው አብረዋት እየተኮራመቱ ነው፡፡ ብርድና ውርጩ ያስቸግራታል፡፡


የልጆቿ አባት አሁን ከእሷ የለም፡፡ ልጆቹም አባታቸው ያደርግላቸው የነበረውን ነገር ዛሬ ላይ ማግኘት አይችሉም፡፡ ይህ ደግሞ በጣም ያስከፋታል፡፡ መፈጠሯንም እንድትጠላ ያስገድዳታል፡፡ የትናንትናው ሁኔታ ዛሬ አብሯት የለም። ቢያንስ የሚበሉት የማያጡት ልጆቿ በደጋጎች እርዳታም ቢሆን ጥሩ ትምህርት ቤት ይማሩ የነበሩት ልጆቿ ዛሬ ላይ ሳይበሉ ለማደር ተገደዋል፡፡ አፍ መፍቻቸው ባልሆነ ቋንቋ እየተቸገሩ ከእናታቸው እቅፍ ለመውጣት ሲቸገሩ ስታይ ሁሉም ነገር ከባድ ይሆንባታል፡፡

የቀደመ ታሪኳን የሚያውቁና ችግሯን የተረዱ አንዳን ዶቹ በማጽናናትና በምክር እንዲሁም የሚችሉትን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ ያግዟታል፡፡

ትርሲት አገር ቋንቋ የማያውቁ ልጆቿን የመንግስት ትምህርት ቤት አስገብታለች፤ ከሁኔታዎች ጋር ተስማምተው ኑሮን ይገፉ ዘንድ ትጥራለች፡፡ ነገር ግን ብዙም ጤንነት ስለማይሰማት እንደልቧ ያገኘችውን ሰርታ መኖር እየከበዳት ነው፡፡ «የእኔስ ይሁን እነዚህን ህጻናት ግን ምን ላድርጋቸው? ስትል ትጠይቃለች፤ ማንነቷን የተረዱ የወረዳ ስራ አስፈጻሚዎች አሽገውት የነበረውን የአባቷን ቤት ከፍተው ስላሳረፏት ምስጋና ታቀርባለች፤ ነገር ግን ጣሪያ ግድግዳ እንጀራ ሆኖ አይቆረስ ወጥ ሆኖ ፈሰስ አይደረግ ነገር ሆኖባት ከልጆቿ ጋር ተፋጣለች፡፡

ነገን ከልጆቿ ጋር በጤና ለመኖር ዛሬ ላይ ደጋግ ኢትዮጵያውያን በእኔ አቅም የሚሰራ ስራን ቢሰጡኝ ሰርቼ ልጆቼን ባስተምር እኔ ባለፍኩበት ባያልፉ ስትልም ትማጸናለች፡፡

# ስፖርት



## ከ23 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ከባድ የመልስ ጨዋታ

ቦጋለ አበበ

በሞሮኮ አዘጋጅነት በሚካሄደው የአፍሪካ ከ23 ዓመት በታች ዋንጫ ለመሳተፍ የመጀመሪያ የማጣሪያ ጨዋታውን ከዲሞክራቲክ ኮንጎ ጋር ያደረገው የኢትዮጵያ ከ23 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በአቻ ውጤት ተለያይቷል። ከትናንት በስቲያ በአዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስቴድየም የተከናወነው ጨዋታ ካለ ግብ 0ለ0 የተጠናቀቀ ሲሆን በአሰልጣኝ አጥናፉ አለሙ የሚመራው የኢትዮጵያ ከ23 አመት በታች ብሔራዊ ቡድን በሜዳው ግብ የማስቆጠር ችግር ጎልቶ ታይቶበታል። አሰልጣኝ አጥናፉ አለሙም “ግብ ያለማስቆጠራችን አንዱ ደካማ ጎናችን ነው” ሲሉ የቡድናቸውን ችግር ተናግረዋል። ይህም በመልሱ ጨዋታ ከባድ ፈተና እንዲገጥመው አድርጓል። በአንጻሩ ቡድኑ በሜዳው ግብ አለማስተናገዱ በመልሱ ጨዋታ ያለውን ተስፋ እንዳይጨልም ያደረገ ሲሆን ወደ ቀጣዩ ዙር ለማለፍ ግን የማሸነፍ ወይም ግብ አስቆጥሮ አቻ የመለያየት ግዴታ ውስጥ ከቶታል።

የሁለቱ ቡድኖች የመልስ ጨዋታ የፊታችን ሰኞ ኪንሻሳ ላይ ይካሄዳል። በአቻ ውጤት ከተጠናቀቀው ጨዋታ በኋላ ለሶከር ኢትዮጵያ አስተያየት የሰጡት አሰልጣኝ አጥናፉ “ቡድኑ የምንችለውን ሁሉ አድርጓል። ተጋጣሚያችንም ጥሩ ነው ምክንያቱም ከሜዳ ውጭ ያለውን ውድድር በሙሉ ያለውን ዕድል ተጠቅመው እዚህ ዘግቶ ለመሄድ የመጣ ነው። በዚህ አደረጃጀት የመጀመሪያው አጋማሽ ላይ ተጭነው ለመጫወት ወይም የአየር ንብረታችንን ከፍታ ተጠቅመው በጣም ተጭነውን ለመጫወት ሞክረዋል፤ ያንንም ተቋቁመን ተጫውተናል። በዚህ አጋጣሚ የተለያዩ ዕድሎችን ፈጥሯል ጥሩ ሆኖ ለማቀናጀት ችሏል። በእንቅስቃሴው መሠረት እንግዲህ ሁለተኛው አጋማሽ ላይ ባሉብን ክፍተቶች ሁሉ ተጫዋቾቹን በበለጠ ዕይታ ኖሯቸው ወደፊት እንዲጫወቱ በማድረጋችን ብዙ ዕድሎችን ፈጥረናል፤ ግን ግብ ማስቆጠር አልቻልንም፤ የሚፈጠር ነው። በተሻለ እንቅስቃሴ በሁለተኛውን አጋማሽ ቡድኑን እንቅስቃሴ ውስጥ በመክተት ከሜዳ ውጭ ዘግቶ የመጫወት ዕድላቸውን በማስከፈት የተለያዩ ሙከራዎችን አድርገናል። እንዳያችሁት ግብ ያለማስቆጠራችን አንዱ ደካማ ጎናችን ነው። ከዚህ አንጻር ለሚቀጥለው ባሉን ድክመቶች ዙሪያ ሰርተን የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ጥሩ መልስ ሆኖናል እንቅስቃሴው። ተጫዋቾች ነገ ለዋናው ብሔራዊ ቡድን የሚሆኑ ተስፋ የሚጣልባቸው ናቸው ፤ ከዚህ አንጻር ተወዳዳሪ ቡድን ነው” በማለት ተናግረዋል።



የመጀመሪያውን ጨዋታ በሜዳው ካለ ግብ ያጠናቀቀው የኢትዮጵያ ከ23 አመት በታች ብሔራዊ ቡድን በመልሱ ጨዋታ ከባድ ፈተና ይጠብቀዋል፣

በጨዋታው የተሻለ ሊባል የሚችል ውጤት ይዘው የወጡት የዲሞክራቲክ ኮንጎ አሰልጣኝ ኪሞቶ ፒፓ በበኩላቸው፣ “ውጤቱ በጣም ጥሩ ነው ፤ ተጫዋቾቼ ጥሩ አድርገዋል። ጨዋታውን ኪንሻሳ ላይ እንጨርሰዋለን ብዬ አስባለሁ” በማለት በውጤቱ እንዳልተከፉ ተናግረዋል።

በጨዋታው የኢትዮጵያ ተጫዋቾች ወደነሱ ሜዳ እስኪመጡ መጠበቅ እና ኳሱን ሲያገኙ በፍጥነት ወደፊት መሄድ በመልሶ ማጥቃት ለመጫወት አቅደው እንደነበር የገለጹት አሰልጣኙ፣ በመልሱ ጨዋታ ኪንሻሳ ላይ ቡድናቸው ጥሩ ይጫወታል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል።

“ስለ ዳኞች ማውራት አልፈልግም፤ አፍሪካ ውስጥ ነው ያለነው። ቡድናችን ላይ ነው ትኩረት የማደርገው እና ቡድናችንም በጣም ጥሩ ተጫውቷል። በመልሱ ጨዋታ በጣም ጥሩ እንጫወታለን ብዬም አስባለሁ፤ እና ከዳኞች ምንም አልጠብቅም። ሁሉም ሥራውን ነው የሚሠራው እኛም ሥራችን ላይ እናተኩራለን ጠንክሮ የሰራ ደግሞ ጥሩ ውጤት ያገኛል።” ሲሉም አሰልጣኙ አክለዋል።

ስለ ተጋጣሚያቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በሰጡት አስተያየትም “የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በጣም ጥሩ ቡድን ነው ፤ አድንቄያቼዋለሁ። መስመሮቹን ዘግተን ለመጫወት ሞክረናል። የመጀመሪያው አጋማሽ ለኛ ጥሩ ነበር አንድ ሁለት የግብ ዕድሎች ነበሩን ግን ይሄ እግር ኳስ ነው። ለመዘጋጀት አራት ቀናት አሉን ጨዋታው ገና አላለቀም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ጥሩ ነው ለእነሱ ጥሩ ስሜት ነው ያለኝ። የመልሱን ጨዋታ ደግሞ ኪንሻሳ ላይ የምናየው ይሆናል” ሲሉ ተናግረዋል።


## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ የእንስሳት ሐኪሞች ማኅበር (Ethiopian Veterinary Association) በሶስት ብሔራዊ ክልሎች (አማራ፣ ኦሮሚያ እና ሶማሌ) የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮግራሞችን ለማጎልበትና የዘርፉን ምርታማነት ለማሻሻል ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

ማኅበሩ የክልሎቹን የማስፈጸም አቅም ለመገንባት በያዘው ዕቅድ መሠረት፤ ጥራት ያላቸው የICT ቁሳቁሶችን (Desktop computers, Printers, UPS, Dividers, Standby Generator, website Server rack, etc.) በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ሕጋዊ አቅራቢዎችን አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡ በዚህም መሠረት የሚከተሉ መሥፈርቶችን የሚያሟሉ ሕጋዊ ድርጅቶች በጨረታው እንዲወዳደሩ በአክብሮት ይጋብዛል፡-

1 . የታደሰ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድና የዘመኑን ግብር ስለመክፈላቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
2. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸውና በተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ስለመመዝገባቸው የምስክርነት ወረቀት ማቅረብ የሚችል፣
3. በመንግስት ግዢ፣ ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በዘርፉ አቅራቢነት መመዝገባቸውን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ ሰነድ ማቅረብ የሚችል፣
   ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 የተዘረዘሩ መሥፈርቶችን የሚያሟሉና የተጠየቁ ሰነዶችን ማቅረብ የሚችሉ ተወዳዳሪዎች በጨረታው ለመሳተፍ ይችላሉ
4. ፍላጎት ያለው ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ 100 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 14 (አሥራ አራት) ተከታታይ የሥራ ቀናት የጨረታ ሰነዱን በማኅበሩ ዋና መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 303/306 ዘወትር በሥራ ሰዓት ከ2:30 እስከ 10:30 ድረስ ቀርበው ሰነዱን መግዛት ይችላል፡፡
5. ተጫራቾች ማህበሩ ባቀረበው የዋጋ መሙያ ሰነድ ላይ በተገለጸው ዝርዝር (Specification) ዋጋቸውን ከVAT በፊት እና በኋላ በግልጽ ሞልተው ሰንዱንም ኤንቨሎፕ ውስጥ በማሸግ ለድርጅቱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ 2% በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክ ቼክ ወይም CPO ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፣ ጨረታውን ያላሸነፉ ተወዳዳሪዎች ለጨረታው ዋስትና ያስያዙት ገንዘብ አሸናፊ ድርጅት እንደተለየ ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል፡፡
7. ጨረታው በ15ኛው ቀን ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ላይ ተወዳዳሪዎች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በይፋ ይከፈታል፡፡ ሆኖም የተጫራቾች ወይም የወኪሎቻቸው አለመገኘት የጨረታውን መክፈት ሂደት አያስተጓጉልም
8. አሸናፊው ድርጅት በራሱ ትራንስፖርት ዕቃዎቹን እስከ ማኅበሩ ጽ/ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅበታል።
9. መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

**ለተጨማሪ መረጃ፡-** በስልክ ቁጥር +251-115-525-020፣ 09-52-67-77-94
ወይም 09-40-08-61-94
ደውሎ ዝርዝር መረጃ መጠየቅ ይቻላል።

**አድራሻ፡-** ከእንግሊዝ ኤምባሲ (British Embassy) ፊት ለፊት 600 ሜትር ገባ ብሎ ወደ School of Tomorrow በሚወስደው መንገድ፣ ይመናሹ ሕንጻ አጠገብ እንገኛለን፡፡

**የኢትዮጵያ የእንስሳት ሐኪሞች ማህበር**



ETHIOPIAN

## የጨረታ ማስታወቂያ

### ጨረታ መለያ ቁጥር፡- ESLSE/UM/NCB/09/2015

የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ከጅቡቲ ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ ወደ ተለያዩ መዳረሻዎች የአፈር ማዳበሪያ ጭነት የማጓጓዝ አገልግሎት ግዥን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ማግኘት ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ በዘርፉ የተሰማራችሁ የጭነት ትራንስፖርት ድርጅቶች የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት እንድትሳተፉ እንጋብዛለን፡፡

1. በዘርፉ የተሰማሩ ሁሉም ድርጅቶች ከትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር/ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የታደሰ የጭነት አገልግሎት የደረጃ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የታደሰ የተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ፣
2. የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የታደሰ ንግድ ፍቃድ፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት
3. የንግድ ትራንስፖርት ድርጅት ጊዜው ያላለፈበት ጨረታን ለመሳተፍ የሚያስችል የግብር አከፋፈል ምስክር ወረቀት ማስረጃ /Tax Clearance Certificate/
4. ተጫራች ድርጅቶች የንግድ፣የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ሰነዶች በተለያዩ ፖስታ ማቅረብ አለባቸው።
5. ተጫራች ድርጅቶች የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ብር 50,000.00/ሃምሳ ሺ ከ00/100/ በ’CPO’ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና ‘ETHIOPIAN SHIPPING & LOGISTICS SERVICES ENTERPRISE’ በሚል ስም በማሰራት ከቴክኒካል ፖስታው ጋር ወይም ለብቻው ጨረታው ሳይከፈት በማቅረብ መጫረት ይችላሉ፡፡
6. ተጫራች ድርጅቶች የጨረታ ሰነዱን ለመግዛት ለገሃር በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት 3ኛ ፎቅ የፋይናንስ ክፍል የማይመለስ ብር 150.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን 10ኛ ፎቅ በግዥ መምሪያ ከሀገር ውስጥ ግዥ ዋና ክፍል መውሰድ ይችላሉ፡፡
7. ጨረታው አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ለገሃር፣ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ዋና መሥሪያ የቤት ሁለገብ ሕንፃ 10ኛ ፎቅ ግዥ መምሪያ አዳራሽ ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ዕለት 8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው ይከፈታል፡፡
8. ከጨረታ መክፈቻው ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ በከፊልም ሆነ በሙሉ ጨረታውን የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር፡- 011-5-54-97-86/011-5-54-97-81**

**የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት**